
በፍቅር፣በሰላም፣በአንድነት
ተከባብሮ ለመኖር
መደማመጥ፣
መቻቻል

ኢትዮጵያዊ የቤተሰብና የመዝናኛ መጽሔት በአማርኛ

መስከረም ፲፱፻፹፰

በየሁለት ወር የሚታተም ፬ኛ ዓመት ቁጥር ፩ $2.75

# ላንዳፍታ



## ዓመት ዓመት ያድርሰን!



## እንቁጣጣሽ በያመቱ ያምጣሽ!!

## ፲፱፻፹፰

# LANDAFTA

*An Ethiopian Cultural Bi-monthly Amharic Magazine*

*(Amharic is the official language of Ethiopia)*

September/October 1995
Vol. 4. No. 1

- ልብ ወለድ
  "የኮለምበስ ጉዞ"
- ፖለቲካና ባላገር
- ኑሮ በአሜሪካ
  "እልፍ ሲሉ እልፍ ሊገኝ!"
- አዳምና ሔዋን
  "ዕጣዬ"






# ETHIO VILLAGE

## CAFE & RESTAURANT

**3462 N. Clark St.**
**Chicago, IL 60657**
**(312) 929-8300**

CATERING AND CARRY OUT AVAILABLE



ቀይ ወጥና ዝግኑ ዶሮ ወጥ አልጫው፤
አትክልት ከሥጋ ጋር ምንቸት አብሽ ክትፎው።
የአበሻ ዳቦና ቆንጆ የማር ጠጅ፤
ሽታው ግቡ ይላል ሳይገቡ ከደጅ።
ቆርጠው በሩን ከፍተው ገባ ሲሉ ገና፤
አገር ቤት የገቡ ያስመስላልና።
የሰኞ ዕለት ዱለት የበግ ወጥ ፍትፍቱ፤
ረቡና ዓርብ ዕለት የጾም በያይነቱ።
በስምንት ዓመት ልምድ የሙያ ክምችት፤
ፍጹም ኢትዮጵያዊ በሆነ ዝግጅት፤
ኢትዮ ቪሌጅ ይምጡ ሲያሻዎት መደሰት።

# ማ ው ጫ

# CONTENTS


2 ከአዘጋጁ

3 እንቁጣጣሽ (ግጥም) ግርማ ዘገዬ

4 ሰላምታ ከአገር ቤት (ወርቃየሁ)

7 ሰላምታ ከባህር ማዶ (ይግለጡ)

11 እንዲህ ሆነ (ዜና ከአገር ቤት)

13 ጥንቅር - ከዚህም ከዚያም

16 የአትላንታ ቅድስት ማርያም ቤ.ክ. በዓል

18 ልብ ወለድ
"የኮለምበስ ጉዞ" ክፍል 4 (አብዩ)

27 ስፖርት
የሲያትሉ ዳሽን የዓመቱ ሻምፒዮና

28 ኑሮ በአሜሪካ
"እልፍ ሲሉ እልፍ ሊገኝ!" (አትናትዮስ)

32 የቦክስ መድረክ . . .
ከጃክ ጆንሰን እስከ መሀመድ አሊ (ሰይፉ መኩሪያ)

33 አዳምና ሔዋን
ዕጣዬ (አብርኸት)

36 ፖለቲካና ባላገር (ሂርጳሳ አንዱዓለም)

47 ስንጠረዥና ጨዋታ




የአትላንታ ቅድስት ማርያም ቤ.ክ. በዓል



የሲያትሉ ዳሽን የዓመቱ ሻምፒዮና

ላንዳፍታ
አምስተኛ
ዓመቷን
ያዘች።

ሽፋን


"ላንዳፍታ" የግል መጽሄት ናት። የሚወጡ ጽሁፎች በሙሉ የአዘጋጆቹን አመለካከት ወይም እምነት ያንጸባርቃሉ ማለት አይደለም። ጽሁፎቹን በሬዲዮ፣ በቴሌቪ ዥን ሆነ በተመሳሳይ መንገድ በከፊልም ሆነ በሙሉ አባዝቶ ለማሰራጨት የጸሃፊውንና የአዘጋጁን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል። በተለይ የገጠመኝና የፈጠራ ድርሰት ጽሁፎች ህጋዊ መብታቸው የተጠበቀ መሆኑን እንገልጻለን።

© COPYRIGHT LANDAFTA 1995

ላንዳፍታ
መስከረም ፲፱፻፹፰
፬ኛ ዓመት ቁጥር ፪
LANDAFTA
Sept/Oct 1995 V. IV- No.2

አዘጋጅና አሳታሚ
መኮንን ገሠሠ

**Publisher/Editor**
*Mekonnen Gessesse*

**Assistant Editors:**
*Workayehu* (pen name)
*Girma Zegeye*

**Contributors:**
*Seifu Mekuria*

**Editorial Advisors**
*Dr. Abera Molla*
*Solomon Melesse*
*Dawit Deres*

**Distribution**

Atlanta, GA
California Mart
Sweet Auburn Grocery
H & B Tailoring

Chicago, IL
Ethio-Village Rest.

Daton, OH
Rainbow Cafe

Dallas, TX
Maru Grocery
ET. Beauty Supply

L.A., CA
Merkato
Damera

Oak Land, CA
Albo-African Shop

San Jose, CA
St. Claire news Stand

Seatle, WA
Addis Cafe

St. Louis, MO
A & Z Liquor

St. Paul, MN
Merkato

Tampa, FL
Ibex Ethiopian restaurant

Washington D.C.
Addisu Gebeya
Family Food Market
Merkato Market
Nini Market (Alex.)
Tana (Silver Spring)

Windsor, Ontario
Tewodros Zewdu

Landafta
P.O.Box 49301
Atlanta, GA 30359
Phone/Fax
(404)728-9122
E-MAIL
mgessesse@aol.com

# ከአዘጋጁ

እንኳን ለአዲሱ ዓመት በሰላምና በጤና አደረሳችሁ እንላለን። አዲስ ዓመት ሲገባ አዲስ ዕቅድ አዲስ ተስፋ መያዙ የተለመደ ነውና አንባቢዎቻችን ጥሩ ተስፋችሁና በጎ ዕቅዳችሁ እንዲሳካ ከልብ የመነጨ ምኞታችንን እንገልጻለን። ላንዳፍታም የመጀመሪያ እትሟን በመስከረም ፲፱፻፹፬ ዓ.ም. (Sept. 1991) አውጥታ ከተጀመረች አራት ዓመት አገባድዳ አምስተኛውን መያዟ ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ አስራ ሰባት እትሞችን ያወጣች ሲሆን ለዕድገቷ ውድ አንባብያን ያደረጉትን አስተዋጽዖ ታደንቃለች። ምስጋናችንን የምንገልጽበት ቃላት ያጥሩናል። በተጨማሪ በመጽሔቷ ላይ ማስታወቂያዎችን በማውጣት ድጋፍ በመሆን፣ መጽሔቷንም በማከፋፈል ለረዳችሁን ድርጅቶችና ግለሰቦች ጥልቅ የሆነ ምስጋናችንን እናቀርባለን። በመጽሔቷም ላይ እንዲወጣ ክፍያ ሳትጠይቁን ጽሁፎችን የላካችሁልንን ሁሉ ከልብ የመነጨ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

በብዛት ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በማተኮር፣ "በፍቅር፣ በሰላምና በአንድነት ተከባብሮ ለመኖር መደማመጥ፣ መቻቻል" የሚለውን መርሆዋን በማስተጋባት ብዙ ብዙ ብላለች። አሳውቃለች፣ አስተዋውቃለች፣ አስተምራለች፣ አዝናንታለች፣ አጽናንታለች። ከሁሉ በላይ በአማርኛ ቋንቋ ብቻ ለዚህን ያህል ጊዜ በመታተም መውጣት መቻሏ ከኢትዮጵያ ውጪ የመጀመሪያዋ እንደሆነች ይነገራል።

ብቅ ብላ ሳትጠፋ ይህን ያህል ጊዜ በመቆየቷ ደግሞ ችግር አልገጠማትም ማለት አይደለም። በአዘጋጅዎችዋ በኩል ያሉብንን ችግሮች ለአንባብያን ለመግለጽ እንወዳለን። !ኛ. የመጽሔቷ ቋሚ ደምበኞች ቁጥር በጣም አነስተኛ በመሆኑ ምን ያህል ማሳተም እንዳለብን ትልቅ ችግር ሆኖብናል። 2ኛ. ለመጽሔቷ ማከፋፈል የምንጠቀምባቸው ኢትዮጵያውያን ድርጅቶችና ግለሰቦች በአብዛኛው ሽያጩን በወቅቱና በሰዓቱ ሲልኩልን አንዳንዶቹ በጣም ያዘገዩብናል። ጭራሹኑ ዝም ያሉንም አልጠፉም። 3ኛ. በአንዳንድ ቦታዎች ደግሞ አከፋፋይ ለማግኘት አልቻልንም። ይህ እንግዲህ ዕድገት ለማሳየት የምናደርገውን ጥረት ከፉኛ አደናቅፎብናል። እንግዲህ በአማርኛችን እየታተመች እዚህ የደረሰችውን መጽሔት የበለጠ እንድታድግ "እባካችሁን ተባበሩን" የሚል መልዕክታችንን ዛሬ አምስተኛ ዓመታችንን በምንይዝበት ወቅት እናስተላልፋለን። ችግር አለብን ብለን ደፍረን ለመግለጽ የተገደድነው የችግሩ ስፋት መቋቋም ከማንችልበት ደረጃ እንዳያደርሰን በመፍራት ነው።

በዝግጅቷ በኩል ደግሞ እንዲሻሻል የምትፈልጉትን ነገር ጠቁሙን። እንግዲህ በአዲሱ ዓመት ተስፋችን የበለጠ እንዲለመለምና ላንዳፍታም የበለጠ እንድታድግ የሁላችሁንም ዕርዳታ ትሻለች። ቋሚ ደምበኛ ይሁንዋት።

የላንዳፍታ መጽሄት ዝግጅት ክፍል
LANDAFTA
P.O.Box 49301, Atlanta, GA 30359
(404) 728-9122
E-MAIL- mgessesse@aol.com

*Landafta is an independent magazine published bi-monthly in Amharic.*
*. Views expressed do not necessarily represent that of its editors and advisors.*

## እንቁጣጣሽ በያመቱ ያምጣሽ።

**እንኳን ከዘመን ወደ ዘመን በሰላምና በጤና አሸጋገራችሁ።**
**መጪው ዘመን የሰላም፤ የደስታና የብልጽግና ይሁንላችሁ።**

## እንቁጣጣሽ

ከግርማ ዘገዬ

ከርመሽ መጣሽ እንቁጣጣሽ
　　　ቃል ኪዳንሽን ሳታከብሪ፤
ለህዝብ እንባ ለሀገር ለቅሶ
　　　ድል ፈንጥቀሽ ሳታበስሪ።
አደይ አበባ ቄጠማሽን
　　　በህዝብ እንባ ልታረጥቢው
ያበሻን ዘር ልቡን ነጥቀሽ
　　　በተስፋ ቃል ልትሸኚው።
ርጉም መርተሽ ሠይጣን ሾመሽ፣
　　　በአዲስ ዘመን ልትረግሚው።
አጋር የለሽ ደሀውን ህዝብ
　　　እንደትቢያ ልትበትኚው።
ለዲያብሎስ እኩይ ፈረስ
　　　ኃይል ጉልበት ልትሰጪው።
አይ መስከረም
እንቁጣጣሽ በያመቱ አሳዘንሺን
　　　ተስፋ ሰጥተሽ ላታከብሪው።
በየአውዳመት አስለቀስሺን።
　　　እስቲ በቃ ኀዘን ይሙት
ተስፋ ይለምልም ብለሽ በይን፤
　　　ተናፋቂ አዲስ ዓመት
ለምለም ሆነሽ ለምለም አርጊን፤
ፍቅር ሰላም አጋር ተገን
　　　ወገን ጥላ ምሽግ ሁኚን።
ከረመጡ ወደሳቱ መገላበጥ በቃ ብለሽ
ስደት ሞትን ገድለሽ ሽረሽ
　　　የዘር ፈረስ ጉልበት ሰብረሽ
በለምለምሽ ቸብ አድርጊን
　　　ዘንድሮ እንኳን ቀና ብለሽ።

# ሰላምታ ከወደ አገር ቤት

## እንደምን አላችሁ?

እንደምን ከርማችኋል? እንደምን አላችሁ? ኑሮና ብልሃቱ እንዴት ይዞአችኋል? ቸርነቱ የማያልቅበት መድኃኔያለም ክብሩ ይስፋ እኛ በጣም ደህና ነን። ክረምቱን ደህና ተያይዘነዋል። ሐምሌን ጨርሰን ነሐሴን ደግሞ አገባደናል። የክረምቱ ብርድና ቁር አይጣል ነው። ዶፍ ይወርዳል። ዘንድሮ ዝናቡ ከባድ ነው። ቅዝቃዜም አለው። ሁሉም እንደአቅሙ ክረምቱን ለመውጣት መፍጨርጨሩን ተያይዞታል። ደራሽ ጎርፍ የወሰደው፣ ውኃ የበላው፣ በረዶና ነጎድጓድ ቀላቅሎ በጣለ ዝናብ የጠፋው በየዕለቱ በሬዲዮ ይነገራል። እንዲህ በሚባል ወረዳ በዚህ በዚህ ዕለት ነፋስ ቀላቅሎ በጣለው ኃይለኛ ዝናብ ማነው የሚባል ሰው ሙቶ፣ ይህን ያክል ሄክታር አዝመራ ጠፍቶ፣ ይህን ያህል ነዋሪ ተፈናቀለ ይባላል። በዚህ በዚህ ጎዳና ማንትስ ወደሚባል ከተማ ይጓዝ የነበረ የመንገደኞች አውቶቢስ በጎርፍ ተወስዶ ይህን ያህል ሰው ሞቶ ይህን ያህል ቆሰለ እየተባለ ዜና ይቀርባል። አንዳንዱም ግራ ነው። ለመረዳት ያስቸግራል። አሁን በዚያን ሰሞን ወደ ኢሉባቡር አንድ ድንጋይ የጫነ ገልባጭ መኪና በመገልበጡ ሃያ ስንት ሰው ሞቶ ሰላሳ የሚሆኑት ከፉኛ ቆስሉ ተብሎ ሲነገር ነበር። ድንጋይ የጫነ መኪና ቢገለበጥ ይህ ሁሉ ሙትና ቁስለኛ ከየት መጣ ትሉ ይሆን? ነገሩ ወዲህ ነው። . . . ድንጋይ በጫነው መኪና ላይ ከቁልል አናት ያ ሁሉ ተሳፋሪ መንገደኛ ተኮልኩሎ ነበር ማለት ነው። እዚህም አዲሳባ ፍልውኃ ግድም፣ ወደቄራ አካባቢ ኃይለኛ ጎርፍ ደርሶ የብዙ ሰዎች መኖሪያ ቤቶችን ፈነቃቅሎ ኮተታቸውን ለቃቅሞ ብዙ ጉዳት አድረሰ። እንዲያውም በሐምሌ ወር መጨረሻ ግድም የጣለው ኃይለኛ ዝናብ ባስከተለው ጎርፍ የሰው ሕይወትም ጠፍቷል።

. . . ሐምሌ ውስጥ አንዱን ቀን መሸትሸት ሲል የጀመረው ዝናብ እንደጉድ ይወርዳል። ሰው ሁሉ ከዋለበት ወደየቤቱ፣ ወደየማደሪያው ተሰብስቧል። ወደ ቄራ አካባቢ ቡልጋሪያ ማዞሪያ ሠፈር ከበግ መሸጫው ማዶ ያለው ነዋሪም በየቤቱ ገብቶ የቀን ውሎውን ከፉውን ደጉን እያነሳ ይጫወታል። ሰፈሩን ድሮም ጎርፍ የሚያጠቃው ቢሆንም መከላከያ ግንብ ስለተበጀለት ሁሉም ያለአንዳች ጥርጣሬ ከየቤተሰቡ ጋር ተሰብስቦ ያወካል። ድንገት ሳይታሰብ የመከላከያ ግንቡን ጥሶ የመጣው ኃይለኛ ጎርፍ የየቤታቸውን ግድግዳ ሲደረምስ ሰፈርተኛው በድንጋጤ ከየቤቱ ተዛዝሎ ወጣ። በዚያ ምሽት ዓይን ያዝ ባደረገው ጨለማ ፀጥታ የነበረው ሰፈር በጩኸትና በእሪታ ተሞላ። የተረፈው ተረፈ።

ያላለትም ወደ አቃቂና ቃሊቲ ግድም በድኑ ተገኘ። በዚህ የጎርፍ አደጋ ከ200 በላይ ቤተሰቦች ክፉኛ የተጎዱ ሲሆን 32 ቤቶች በጎርፉ ተወስደዋል። ስምንት ሰዎችና አንዲት ህፃን ሕይወታቸውን አጥተዋል። መስከረም እስኪጠባ ነሐሴ እስኪያልፍ ድረስ ያገኘው ብርድልብስ ያላገኘም ጆንያ ለብሶ ከአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ተጠልለዋል። . . . እንግዲህ ክረምቱ እኛ ዘንድ እንዲህ ይመስላል። የሚያንጠረጥረውን የክረምቱን ብርድ ለመቋቋም፣ በብርዱ ሳቢያ አሁንም አሁንም አምጡ እያለ የሚሞረሙረውን ሆድ ለመሙላት ሁሉም በየፊናው በየመንደሩ በየሥርቻው ውስጥ መሸቀሉን ተያይዞታል። የንግዱ ዓይነት ብዙ ነው። ገበያው ዝቆሽም ባይሆን በባዶ አንጀት በብርድ ተኮራምቶ ተኝቶ ላለመሞት ይሆናል። የንግዱ ዘዴም በትንሽ ፍራንክ የሆነውን ገዝቶ በየመንደሩ ውስጥ ድምፅን ከፍ አድርጎ መጮህ ብቻ ነው የሚጠይቀው! ልብ ብሎ ላዳመጠው አይነቱ ብዙ ነው!

አሮጌ ቆርቆሮ፣ ብልቃጥ ጠርሙስ ያለው .
. . ቆርቆሮ ያለው!
ፍራሽ አዳሽ! ፍራሽ አዳሽ!
አሮጌ ፍራሽ አዳሽ!
እጃ! ሱፍ! ሱፍ!
ገብስ! ገብስ! እጃ ፈላጊ!
ልዋጭ! ልዋጭ! ልዋጭ!
አሮጌ ልብስ አሮጌ ጫማ ያለሽ! ልዋጭ!
ከሰል ፈላጊ! ከሰል ፈላጊ! ከሰል ያለቀበት!
መወልወያ! መጥረጊያ! መወልወያ! መጥረጊያ!
መወልወያ ፈላጊ! መጥረጊያ ፈላጊ!
እሸት እሸት በቆሎ እሸት! በቆሎ እሸት ፈላጊ! .
. . ብዘረዝረው አያልቅም።

የንግዱ ዓይነት ብዙ ነው። አንዱ ሲያልፍ ሌላው ይመጣል። ደግሞ እየጮኸ ያልፋል። ትምህርት ቤት ተዘግቶ ፋታ ያገኘው የመንደር ኩታራ ደግሞ ተሰብስቦ ትንሽዬ የፍራንክ ሳጥን ይዩዝና እያንኮሻኮሹ ጋሼ ለስፖርት ዕርዳታ! . . . ማሊያ መግዣ . . ያሎትን አስር ሳንቲምም ብትሆን . . ያልዎትን ዕርዳታ እያሉ መንገደኛውን ይለምናሉ። የየገጠሩ ሰው በከባድ የአዝመራ ስራ ተጠምዷል። በአብዛኛው ቦታ አሁን ዋናው የዘር የአዝመራ ጊዜ ነው። ልጅ አዋቂው እማሳ ላይ ከአፈር ጋር ሲታገል፣ አረም ሲያርም፣ ሲጎለጉል፣ ሲዘራ፣ ሲኮተኩት ይውላል። ላስቲክ ጎጆው ከየጥጋጥጉ የፈረሰበት ተፈናቃይ ደግሞ የክረምቱ ዶፍ ዝናብ እየወረደበት ባዶ አንጀቱን ጭብጥ ኩርምት ይላል። ደህና ጥግ ፈልጎ የላስቲክ ጎጆው ሰርቶ መጠለል የለም። ትናንት ቀረ።

ለብዙ ተፈናቃዮች የላስቲክ ጎጆው It belongs to the good old days. አዲሶቹ ምልምል ፖሊሶች ባልወለደ አንጀታቸው እየቀጠቀጡና እየነረቱ ያባርሩታል። ባለጊዜዎቹ ፖለቲከኞቻችን ደግሞ ከሽግግር መንግሥትነት ወደ ቋሚነት ለመሸጋገር ሸብ እረብ አለች ምድሪ ይዘፈናል። ሽር ጉድ እያሉ ነው። በፌሽታ በፍንደቃ ከረምቱን አገባደው ሰሞኑን ከስብሰባ ላይ ተጥደዋል። ቀደም ሲል የየክልሉ ምክር ቤቶች ስብሰባ ተሰይመው ረጃጅም ዲስኩሮች ተደርገዋል። ቱባ ቱባው ሹም የየራሱን ገድል በአለፉት አራት ዓመታት ለድሃው የተትረፈረፈለትን ዲሞክራሲ የተገኘውን ብልጥግና ነግሮናል። አርጋጅ አስረጋጁ፣ ቶስቷሳ ወሬኛው ደግሞ የአጉራሽ፣ የአልባሾቹን፣ የጌቶቹን የአመራር ብልህነትና አዋቂነት የሚቀጥሉትን ዓመታት ብሩህነት እያሞካሸ አሞጋገሰ። ለሆዱ ያደረ ከርሳም ጆሌ ደግሞ ግዳይ እንደጣለ ጀግና ቅብርር ውጥርጥር እያደረገው በል ያሉትን፣ ተናገር የተባለውን እየተንጠራራ እየተሳደበ ቀባጠረ። የልብ ልብ የተሰማው ደንቆሮ እብሪተኛም "አዳሜ ወደድሽም ጠላሽም ወደ አገዛዝ መጥተናል። ለሰላሳና ለሃምሳ ዓመታት የታገልንለት የትግላችን ውጤት ነው" እያለ ደነፋ። ከበሮ ድለቃው፣ ሆያ ሆዬውና ዲስኩሩ ጋብ ሲል የሥልጣን ርክክቡ፣ ቃለ መሃላው፣ ሹመቱና አዋጁ ይጎርፋል። ስልጣን አስረካቢዎቹም ተረካቢዎቹም ያው ቀድሞውኑ በስልጣን ላይ ያሉ በወንበሩ ላይ የተቆናጠጡ ናቸው። ይህቺን ዓይነቷን የፖለቲከኞቻችንን ድራማ በደንብ እናውቃታለን።

. . . የዛሬ አስራ ስንት ዓመት ገደማ ይህን ጊዜ ኮሎኔል መንግስቱና ጓዶቻቸው አሁን እየተደረገ ያለውን የሚመስል ስብሰባ ተሰይመው ነበር። የአገር መሪዎችና እንግዶች ተጠርተዋል። ኮሎኔል መንግስቱ ስድስት ሰዓታት የፈጀ ንግግር አድርገው የአብዮቱን ድሎች፣ የአመራራቸውን ብልህነት፣ የሕዝቡን ብልፅግና፣ የአገሪቷን ዕድገትና የሰፈነውን ዲሞክራሲ ዘርዝረው ዘርዝረው ካድሬውን ሁሉ አስጨበጨቡት። ትላልቁ ትላልቁም ሹም እኔም አለሁበት በሚል ስሜት ልቡን ነፍቶ በኩራት ትከሻውን አሳበጠ። ግልገል ግልገሉም ካድሬ እንደአቅሙ ፈነጠዘ። ያኔ የፍርድ ሚኒስትር የነበሩት (የኤርትራው ተወላጅ ?) ጓድ አማኑኤል አምደሚካኤል ብድግ አሉና የጓድ መንግስቱን አመራር ብልህነትና ቆራጥነት አድንቀው አሞካሽተው "ጓድ መንግስቱ የኢሠፓ ናቸው። ኢሠፓም የጓድ መንግስቱ ነው።" አሉና ያንን ሁሉ ወፈሰማይ ካድሬ ወሽመጡን ቆረጡት። ኢሠፓ ኢሠፓዬ እያለ ያዜም የነበረው ቶስቷሳ ግልገል ካድሬ ቅር አለው። ልፋቱ ትግሉ መና የቀረበት መሰለው። ጓድ መንግስቱ የኢሠፓ ይሁኑ ኢሠፓ ግን እንዴት የእርሳቸው ይሆናል ሲል በሆዱ አጉረመረመ። እርሳቸው የአብዮቱ አንጡራ ሀብት ናቸው ይባል እንጂ እንዴት አብዮቱ የእርሳቸው አንጡራ ሀብት ይሆናል በማለት ቅር አለው። መከላከያ ሚኒስትር የነበሩት ጄኔራል ተስፋዬ ገ/ኪዳን በተራቸው ተነሱና ረጅም ዲስኩር አደረጉ። በኋላም "ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት ለኢትዮጵያ ሕዝብ በገባው ቃል ኪዳን መሰረት ዛሬ ጳጉሜ 5 ቀን 1976 ዓ.ም ከቀኑ በ9:15 ላይ እነሆ ስልጣኑን ለሕዝብ አስረክበናል" አሉ። ኮሎኔል መንግስቱ በሕዝብ ተመረጡና የአገሪቱ መሪ ሆነው ቃለመሃላ ፈፀሙ። ዕልልታው ጭብጨባው ቀለጠ። የጉባኤ አዳራሽ በፈንጠዝያ ተሞላ። ሬድዮና ቴሌቭዥኖች ሰፊው ሕዝብ ስልጣን መረከቡን አበሰሩ። የምስራቹን አስተጋቡ። ከአድማስ አድማስ አሰራጩ። የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ስልጣን ተረከበ። ሪቺት ተተኮሰ። ለሥነሥርዓቱም ግዳመቂያ ከአውሮፓ በመርከብ ተጭኖ የመጣው ውስኪና ሻምፓኝ ተከፈተ። በየቀበሌው ድግሱ ጠፈ። ለወራት የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ተዘግተው ሰልፍ ሲለማመድ የነበረው ሠራተኛ ደስታ ፈንቅሎት በየአደባባዩ ተመመ። ወታደሩ ጠመንጃውን እንዳነገበ ብረት ለበስ ታንክና ሮኬት ተኳሹን እየነዳ ለሰልፍ ወጣ። የአብዮቱን ድሎች የሕዝቡን የሥልጣን ባለቤትነት የሚያንፀባርቁ ኤግዚቢሽኖች ተከፈቱ። ትርዒቶች ታዩ። የደስታ መግለጫው ተዝጎደጎደ። ነገር ግን ከጥቂት ኪሎ ሜትሮች ርቀት ላይ የመንግሥት ፖሊሶች አካባቢውን ለቀ ወደ አዲስ አበባ ከሚጎርፈው ረሃብተኛ ጋር ተፋጠው ነበር።

ዘንድሮም ያን መሰል ትርዒት እየተደገመ ይሁን በእውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ደግሞ ስልጣን መረከቡ ብቻ በሌላ ዙር የስልጣን ርክክብ ምድር ቁና ሆናለች። ያልወለድኩት ልጅ አባባ ቢለኝ አፈን ዳባ ዳባ አለኝ ይላል የአገሬ ሰው!! ዋናው ትርዒት አራት ኪሎ ተጀምሯል። ይህን መሰሉን ትርዒት ለመስራት የሚወጣው ሀብትና የሚባክነው ገንዘብ እንዲህ የዋዛ አይደለም። ውስኪ ከአውሮፓ በመርከብ መምጣቱን ባንሰማም 20 ካዲላክ መካናዎች በብዙ ሚሊዮን ብር መገዛታቸውን ጆሮአችን ሰምቷል። እንደያኔው የአገር መሪዎች ባይጋብዙም የትግል አጋሮች ግን የክብር ስፍራቸውን ይዘዋል። የአገር መሪዎች ቢጋብዙም እንኳ መምጣታቸው የሚመስል ነገር አይደለም። ባለፈው ሰኔ ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመሪዎች ስብሰባ የመጡት እንኳ ነፍስ ግቢ ነፍስ ውጪ ጭንቅ ሆኖባቸው ከርመው ነው ወደአገራቸው የተመለሱት።በነገራችን ላይ የግብፁ ፕሬዚዳንት ሙባረክ ለትንሽ ተረፉ። CNN ወሬውን እንዳጠገባችሁ ይሰማኛል። ጨዋታን ጨዋታ ያመጣዋል እንዲሉ አንድ ወቅት ፕሬዚዳንት ሙባረክ እንዲህ አሉ ይባላል።

ኮሎኔል መንግስቱ በአፍሪካ ግዙፍ የተባለለትን የጦር ኃይል ባደራጁበት ዘመን አድሃሪ የአረብ መንግስታትና ጎረቤቶቻችን እያሉ እንዳንዴ ይዝቱ ስለነበር አንድ ጋዜጠኛ ፕሬዚዳንት ሙባረክን "ይሄ የኮሎኔል መንግሥቱ ግዙፍ ጦር ለግብፅ አያስጋትም ወይ?" ብሎ ጠየቃቸው አሉ። ፕሬዚዳንት ሙባረክም ሲመልሱ "የኮሎኔል መንግስቱ ጦር የሚያስፈራው ቀዳሚ ዒላማው ለሆነችው አሜሪካ እንጂ ለግብፅ አይደለም። እርግጥ አሜሪካንን ድል አድርጎ ሲመለስ እግረ መንገዱን ግብፅን እንዳይወራት እንሰጋለን" በማለት በለበጣ መለሱለት አሉ። አያድርገውና መኪናቸውን የጨረፈች ጥይት አግኝታቸው ቢሆን ተወረው ሳይሆን በገዛ ራሳቸው መጥተው አዲስ አበባ ላይ ሊቀሯት ነበር። የሚገርመው ግን የተሳለ ቢላዋ እንኳን በየቤታችሁ እንዳይኖራችሁ በተባለበት አዲሳባ ያ ሁሉ ጉድ የጦር መሳሪያ በገፍ ገብቶ መገኘቱ ነው።

ከሞላ ጎደል እኛ እንዲህ እንመስላለን? ለመሆኑ እናንተስ እንዴት ናችሁ? ወዳጄ ይግለጡ እንዴት ነህ? በመልክ በቁመና ባንተዋወቅም እንደምን አላችሁ? ለሚለው ሰላምታዬ በሰጠሽኝ ምላሽ አወኩህ። ስለ አሜሪካ የፃፍከውን በጣም ወደድኩት። እውነትም ይግለጡ! ስምን መልአክ ያወጣዋል አሉ። በተለይ ሽፍትነት በአሜሪካ እንዴት እንደሚስተናገድ የዘረዘርከው ያስገርማል። ወዳጄ ይግለጡ! ፈረንጅ ግን መልቲ ነው። ምላጭ! በአገራቸው አምርሮ ጫካ የገባውን መሳቂያ መሳለቂያ የሚያደርጉትን ያህል እዚህ እኛ ዘንድ ሲመጡ የሚያደርጉት ደግሞ ተቃራኒውን ነው። ምን እነግርሃለሁ? ታውቀዋለህ። ጭራሽ ለሌላውም ሞዴል ትሆናላችሁ። የዓለም መሪ ትሆናላችሁ እያሉ ያሞኙናል።

ለነገሩ የእናንተ መጨረሻና የሀገሪቱ ዕጣ ፈንታ ምን ይሆን አልከኝ? አንተኑ መልሼ ልጠይቅህና የእናንተስ መጨረሻ? . . . እኛስ ያደሩበት ጭቃ ከጭድ ይሞቃል ሆኖ ሁሉን ችለነው አለን። የእኛ ነገር ካለየለት እናንተስ ብትሆኑ እንደወጣችሁ መቅረታችሁ አይደል?

ወዳጄ ይግለጡ! እስቲ ስለ አገር ወሬ ትንሽ ላጫውትህ!! ይኸውልህ! የኢትዮጵያ ሕዝብ 57 ሚሊዮን ይሆናል ይባላል። የሕዝቡ ብዛት በ3.2% ፍጥነት እያደገ ሲሆን በዓመት ከ2 ሚሊዮን የሚበልጥ የሕዝብ ቁጥር ይጨምራል። በዚህ አካሄድ አሁን ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር በ2000 ዓ.ም መጀመሪያ ግድም ወደ 115 ሚሊዮን ይደርሳል ተብሎ ይገመታል። አንዲት ሴት በወሊድ ዘመኗ የምትወልደው የልጆች መጠን በአማካይ 8 ያህል ይደርሳል። በኢትዮጵያ የሚመረተው የእርሻ ውጤት ለእያንዳንዱ ዜጋ በቀን 600 ግራም እንዲዳረስ ቢደረግ እንኳ ማዳረስ የሚቻለው ለ2/3ኛው ሕዝብ ብቻ ነው።ለአንደኛ ደረጃ የትምህርት ክልል ዕድሜያቸው ከደረሱት ልጆች መካከል የትምህርት ዕድል የሚያገኙት ከ20% ያነሱቱ ሲሆን ያለው የጤና አገልግሎት ሊዳረስ የሚችለው ከ40% ለማይበልጥ ሕዝብ ነው። በዚህ ላይ ከቀን ወደቀን እየጨመረ የሚሄደው የኤድስ ሕሙማን ቁጥር ሲጨመር የጤና አገልግሎቱ ከዚህም ሊያንስ እንደሚችል መገመት አያዳግትም። እስከ ሚያዝያ 1987 ዓ.ም ድረስ በ57 ሆስፒታሎች 18,042 የኤድስ ሕሙማን መገኘታቸው ታውቋል።

በሥራ ዕድል ረገድ የአገሪቱ ኢኮኖሚ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ስራ አጦቿን ወደ ስራ ለማሰማራት በመቶ ሺ የሚቆጠሩ ለስራ ለደረሱ ዜጎቿ የስራ ዕድል በር ለመክፈት፣ በመቶ ሺ ለሚቆጠሩ የጎዳና ተዳዳሪዎችና ተፈናቃዮች መጠለያ ለመስጠትና ለመመገብ ገና የትየሌሌ ነው። በዚያው አንፃር ለማገዶ፣ ለቤት መስሪያና ለግጦሽ የሚጨፈጨፈው ደን ከመቶ ዓመት በፊት ከነበረው 40% ወደ 3.6% ደርሷል። ይህቺ የቀረችዋም በስንት ጊዜ ከዜሮ እንደምትደርስ ባለሙያ መጠየቅ አያስፈልግም። "እንጓይ ፍስስ" እየዘፈኑ ግንድላና አጠና ወደ አሥመራ ቀን ከሌሊት የሚያመላልሱትን የከባድ መኪና ሹፌሮች መጠየቅ ይበቃል። አያጡትም።

የኑሮ ውድነቱ በእጅህ የያዝከውን የሚነጥቅ ብቻ ሳይሆን በአፍህ ያደረከውን እንኳ ከመንጋጋህ አላቆ የሚያወጣ ያህል ከፍቷል። ይሁን እንጂ ሁሉም እንደአቅሙ በልቶ ያድራል። እንደነዛየር inflation 8500% አልደረሰም። ብዙ ተስፋ አስቆራጭ ነገር ቢኖርም ይህ ሕዝብ ሁሉን ቻይ እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ ጎጆውን ትዳሩን ለማሸነፍ ኑሮውን ለመለወጥ ብዙ ይደክማል።

እንግዲህ ወዳጄ ሆይ! ብዙ እምለው ነበረኝ። ነገሬን አልጨረስኩም። በአሜሪካ አደበባይ ስለወጣው የተመሳሳይ ጾታ ግኑኝነት ሲነሳ እዚህም እኛ ዘንድ በየስርቻው ያቆጠቆጠውን የሰዶምን ብልግናና ነውር የረሳሁ እንዳይመስልህ!! በምድረ አሜሪካ ወንዶች በሴቶች ላይ የበላይነት ለማሳየት የማይሞክረውን ያህል በዚህ በእኛው አገር ደግሞ አካላቸውን በስለት ሳይቀር በመዘልዘል በባህልና በልማድ በሴቶች እህቶቻችን ላይ የሚደረገውን የከፋ ድርጊት እመለስበታለሁ።

እስከዚያው በቸር ያቆየን!!
ወርቃየሁ — ከኢትዮጵያ

# ሰላምታ ከወደ ባህር ማዶ

## ከይግለጡ ለወርቃየሁ

ያገር ልጅ ወርቃየሁ ባለፈው መልዕክቴ በአሜሪካ ኑሮ ላይ ባነጣጠሩ ጥቂት ነጥቦች ላይ አንዳንድ አስተያየቶችን ለማቅረብ ሞክሬያለሁ። ግን ያልጨረስኩት የህብረተሰብ ጠንቅ የሆነ ልምድ ላይ መቋጠሪያ ፈልጌለት ወደ ሌላ ርዕስ ለማምራት ልሞክር።

ይኼውልህ አሜሪካ የደረጀ የፈጠራ ሥራ፣ የጠነከረ አንድነት፣ የፈረጠመ ጉልበት ያላትን ያህል ባለፈው መልዕክቴ መጨረሻ ላይ እንደገለፅኩት ለማመን የሚያስቸግር፣ ለመስማት የሚቀፍ ተግባር የሚፈፅሙ የህብረተሰብ አረሞች በየጊዜው የሚበቅሉባት አገር መሆኑንም አትዘንጋ። ከጅምሬ ልነሳልህ። ይህ የተመሣሣይ ፆታዎች ለወሲብ መፈቃቀድ መቼ እንደተጀመረ በውል ባይታወቅም ከመጽሐፍ ቅዱስ መረጃነት ስንነሣ በዚህ ተግባር የተሰማሩትን ሰዎች ለመቅጣት ሰዶምና ገሞራን እግዚአብሔር በእሳት እንዳጠፋት ታሪክ ምስክርነቱን ይሰጣል። የአሁኑ ዘመን ሉጢዎች ግን ይህንን ልምድ እንዴት እንዳገኙት ሲናገሩ እግዚአብሔር በመሳሳት ወንድ አድርጎ ፈጠረን እንጂ የውስጥ አካል ሲስተማችን የሴት ነው ባይ ናቸው። ለምን? ወይም እንዴት? የሚል ጥያቄ ማቅረብ የለብህም። የምትጠይቅ ከሆነ ግን መልሳቸው አንተ በእኛ እንትትን ምን አገባህ "This is America, a free country" ይሉሃል።

ለመሆኑ የእነዚህ ዓይነቶች መሰል አበሻ አለ ወይ? የሚል ጥያቄ ታቀርብ ይሆናል። በቅርቡ ከወደ ዋሽንግተን በእስር ጣቶቹ ቀለበት ያደረገ፣ የጥፍር ቀለም የተቀባና እንደሴት እየተቅለሰለሰ በሴት ድምፅ የሚያናግር አበሻ መታየቱን ሰማንና እንግዲህ ሊቀውስ ነው ብለን ታዝበን አልፈናል። ስለማንነቱና ስለድርጊቱ ብዙ የተረጋገጠ ነገር ስላልሰማን በሽታው ከፀናበት ኑዛዜውን ከእሱ እንጠብቃለን። በተረፈ ዘና ብሎ በድንገትና በስህተት ከኋላው ቸብ ቢያደርጉት ?? ብሎ መፈናጠሩን አሁንም አልተወም። ከዚህ ሳልወጣ የሉጢዎች (ግብረ ሰዶማውያን) መብት በህግ አይደንገግ እንጂ በራሳቸው ህግ ማህበር የማቋቋም፣ የራሳቸውን መዝናኛ መፍጠር፣ በህግ የመጋባት መብታቸውን ለማስጠበቅ ደፋ ቀና ሲሉ ይታያሉ። ሰውየው ሙከት ሊገዛ ወደ በግ ተራ ብቅ ይልና አንዱን ፈርጠም ያለ በግ በእጁ እየዳበሰ ይሄ ስንት ነው? ብሎ ይጠይቃል። አራት መቶ ብር። በዋጋው ይደነግጥና በዚህስ ዋጋ ሁለት ጠብደል አህያ አልገዛም እንዴ? ቢለው ሻጩ በትዝብት አይን ወደ ሰውየው እየተመለከተ እንግዲህ የሚጣፍጥዎን እርስዎ ያውቃሉ አለው አሉ። እኔ ኩነኔው ታይቶኝ እንጂ በሰው ሀያኒ ምን ጥልቅ አድርጎኝ ብለህ።

ይልቅስ ደግ ደጉን ላውጋህ–አሜሪካን እንዲህ አይነት አገር ናት ብሎ ለመደምደም አስቸጋሪ ገፅታ አላት። ለምን መሰለህ ሁሉም አሜሪካንን የሚተረጉማት ከራሱ ህይወት ጋር እየዛመደ ነው። ቀን ከሌት ሲደክም ከርሞ በገቢው ያልተደሰተና ህልሙ ያልሞላለት የእርግማን ናዳ ሲያወርድባት፣ በትንሹ ሰርቶ ያሰበው የሞላለት፣ ኪሱ ያበጠለት ደግሞ "Great America" የሚል የሙገሳ ስም ይሰጣታል። የእኔ ትችት የሚያተኩረው ግን ከሁለቱም ወገኖች አማካይ አመለካከት የመነጨ እንጂ ወደ አንድ ወገን ያደላ አይሆንም።

ለቤተሰብ ከሚሰጠው ትልቅ ስፍራ ወይም ከቤተሰብ ክብርና ዋጋ (family value) ልነሳልህ። አብዛኛው የአሜሪካ ህዝብ ቤተሰብ ለመመስረት የሚወስነው በቅድሚያ የረጅም ጊዜ እቅድ አውጥቶ ነው። ከጋብቻ በኋላ ምን ይመጣል? ትዳሬን እንዴት እጠብቀዋለሁ? ያለን ገቢ ለመኖር በቂ ነወይ? የሚሉት ጥያቄዎች በሁለቱም ወገን በቅድሚያ ይጠናል። እነዚህን ጥያቄዎች መመለስ ካልተቻለ ግን ያለህጋዊ ጋብቻ በአንድ ቤት በፍቅረኛነት መኖር የተለመደና በስፋት የሚታይ ነው።

ከጋብቻ በኋላ ልጅ ለመፍጠር፣ የሰፈ ቤተሰብ ባለቤት ለመሆን ቅድመ ዝግጅቱ ከልጅ መምጣት በፊት ይከናወናል። ቤተሰብ እየሰፋና እያደገ ሲመጣ የልጅ እንክብካቤ ትልቁን ስፍራ የሚይዝ ይሆናል። አንድ ህፃን ከተወለደበት ጊዜ እንስቶ 18 ዓመት እስኪሞላው ድረስ እንክብካቤ የማድረግ ግዴታ የሚወድቀው በወላጆች ላይ ነው። ምን አዲስ ነገር ተፈጠረ ታዲያ የእኛስ አገር ህፃናት የቤተሰብ እንክብካቤ እንደየአቅሙ መች ተለያቸው ትለኝ ይሆናል። ነገሩ ዱባና ቅል ነው። በሀገሬ የሚወለዱት ህፃናት በአብዛኛው ከውልደታቸው ቀን እንስቶ የሚደረግላቸው ክታብ "ልጅ በዕድሉ ያድጋል፣ ፊትና ልጅ አይበርደውም" ሌላም ሌላም ተገቢ ያልሆነ ፍርድ ገና በጨቅላነታቸው እየተሰጣቸው የዚህን ዓለም ኑሮ በችግር ወይም የህፃንነት ወግና ደንቡን ሳይቀምሱ ያድጋሉ። የእነዚህ ግን ለየት ይላል ጭራሽ አይገናኙም። ለመሆኑ በሀገራችን ሳይገረፍ፣ ሳይኮረኮም፣ "ሳይቆነጠጥ ያደገ" ከሚለው ተረት ጋር እንዳታጋጭብኝ። ሳይቆነጠጥ ያደገ የሚለውን አባባል ለማስተላለፍ የሚፈልገው መልዕክት ቢኖር "ከሥነሥርዓት ውጭ የሆነ፣ ባለጌ" ወይም የቤተሰብ ቁጥጥር የጎደለውን ለማመልከት ሲሆን የግድ ህፃናትን በሥነሥርዓት ለማሳደግ ቁንጥጫና ኩርኩም ወይም አለንጋና ልምጭ የግድ በሥነሥርዓት አስከባሪነት ከህፃናት እድገት ጋር መተሳሰር አለባቸው ለማለት እንዳልሆነ ግልፅ መሆን አለበት።

እኔም ለዚህ ብዬ ነው ይህንን አባባል በአጭሩ ለማብራራት የሞከርኩት በአሜሪካ ላይ ግን ህፃናትን በርግገው እስኪያመልጡ ወይም እያባረርኩ እገርፋለሁ ብለህ ብትሞክር በካቴና ተጠፍረህ ወህኒ መውረድህን አትዘንጋ።

ይህም ብቻ አይደል በጊዜያዊ ንዴት የገረፍከውንና በጣም የምትወደውን ህፃን ዳግመኛም ላታየው ትችላለህ። ለእንደዚህ ላሉ የቤተሰብ መጎሳቆል ለሚያገኛቸው ህፃናት የተዘጋጀ ጥሩ ስፍራ አለና። አንተ ወደ ወህኒ ስትወርድ ልጅህ ባልወለዱት ነገር ግን ህግ መብት በሰጣቸው ተንከባካቢዎች ጥላ ስር ተገቢውን እንክብካቤ እንዲያገኝ ለዚህ ወደተዘጋጀው ስፍራ ይሄዳል። የእግዚአብሔር ፍቃዱ ካልሆነና የአንተ ጠባይ ለመታረሙ ምልክት ካላሳየህ ልጅህን የመጎብኘት መብት እንኳን አይኖርህም። ምን ጉድ ነው በራሴ ልጅ ምን አገባቸው? እንዳትል የወለዱትን ልጅ የመቀጥቀጥ፣ የማጎሳቆልና መበደል ያለህግ የተፈቀደው እዛው ከእኛ ሰፈር እንጂ እዚህ የማይሞከር ነው። ቤት ጠብቅ ብለኸው የሄድከው ህፃን ከሄድክበት ስትመለስ ከስፍራው አታገኘውም። በምትኩ ቤትህን ከበው የአንተን መመለስ በናፍቆት የሚጠብቁ ህግ አስከባሪዎች እያዋከቡ እግር ከወርች አስረው የተከሳሽነት ቃልህን ወደምትሰጥበት ስፍራ ይወስዱሃል። እንግዲህ ከዚያ በኋላ አንተና ልጅህ ወላጅና ልጅ ሳትሆኑ ከሳሽና ተከሳሽ መሆናችሁ ነው።

ይህ ህግ በስራ ላይ ከዋለ ዘመናት ያስቆጠረ በመሆኑ የዛሬው አሜሪካዊ ትውልድ እንደህግ ሳይሆን ልጅን በአግባቡ ተንከባክቦ ማሳደግ ባህሉ አድርጎታል። አሜሪካ ለህፃናት ብቻ ሳይሆን ህጉ ለሴቶችም የሚሰጠው ክብርና ስፍራ ለየት ይላል። በየሰፈሩ የባልና ሚስት ፀብ፣ ኡኡታና ንትርክ አይሰማም። በባለትዳሮች መካከል የከረረ ፀብ ከተነሳ እየተሯሯጡ መናረት፣ ለጎረቤት ግልግል ማስቸገር፣ አካባቢ ፀጥታ መንሳት ቦታ የማይሰጣቸው ሲሆን እንደዚህ ያለ ችግር በባለትዳሮች መሃል ከገባ ነገሩ ሳይከር ጉዳዩን መርምሮ ፍቺ የሚያስፈፅም አካል ጣልቃ እንዲገባበት ይደረጋል። ከዚህ ውጭ ግን በወንድነቴ ሚስቴን አገጪን አንገጫግጬ፣ አይነስቧን አጥፍቼ የመጣው ይመጣል ብለህ ብታስብ ወይም በሚስትህ ላይ ይህን ብትፈፅም ግማሽ ዕድሜህን ወይም ከዚያ በላይ ከርቸሌ መከረምህን አትርሳ። ሚስትን እየደበደቡ ከቤት ማስወጣት፣ አብራ የለፋችበትን ሳያካፍሉ በነፃ ማባረር ቦታ የላቸውም። እንዲያውም ህጉ ሙሉ በሙሉ ለሴቶች ያደላ ነው። በአንድ ቤት አብሮ ለመኖር ፈቃደኛ ያልሆነው እንጂ የግድ ወንድ በወንድነቱ ብቻ ሚስቱን የማባረር መብት በፍፁም የማይሞከር ነው። አሜሪካንን ትኩር ብሎ ላያት በተለይ መብትን በተመለከተ እንኳን የህፃናትና የሴቶች መብት ቀርቶ የእንስሳት መብት በህግ የተከበረ ነው። የቤት እንስሳትን ወደብደብ፣ ከቤት ማባረር፣ በአግባቡ አለመያዝ በህግ ያስቀጣል። እንስሳት የተስማማቸውን ምግብ ብቻ መርጦ መስጠት፣ ሲታመሙ በሚገባ ማሳከም፣ የሚጠለሉበትን ከሰው ባላነሰ መልኩ ማዘጋጀት ህግ ብቻ ሳይሆን ልምድም ጭምር ነው። ለዚህም ይመስላል የአሜሪካ ህዝብ በእንስሳት ላይ ያለው ፍቅር ከፍተኛ ከመሆኑ አልፎ በልምድ የቤት እንስሳ የሆኑትን ውሻና ድመት ብቻ ሳይሆን የዱር አራዊትንም በማላመድ ወደ ቤት እንስሳነት በመቀየር ላይ የሚገኘው። ለዚህም ጥሩ ማስረጃና ምሳሌ ለማቅረብ ያህል እባብና አይጥን መጥቀስ ይበቃል።

አይጥ በንብረት አጥፊነት የታወቀች ትንሽ እንስሳ ብትሆንም በአሜሪካ ምድር ላይ ግን ህፃናትን በማጫወት ከአዋቂዎች ጋር በመላፋት በፍቅር ዓይን የምትታይና በምቶት ለመኖር የታደለች እነስተኛ ፍጡር ለመሆን በቅታለች። እባብ በተናዳፊነት የሚታወቅ በደረቱ የሚሳብ አስቀያሚ እንስሳ ቢሆንም በዚህች ምድር ቦታ ተሰጥቶት ከሰው ጋር በአንድ አልጋ ላይ እስከመተኛት የደረሰ ተወዳጅ ፍጡር ሆኗል። ከዚህ ባለፈ በየጎዳናው በጭነት ወገቡ የተለመጠ አህያ፣ በዱላ እየተነረተ የሚሄድ በቅሎ ወይም ሌላ የጭነት እንስሳ በአሜሪካ ጎዳናዎች ላይ አይታዩም ። በተለይ አህያ እንደብርቅ እንስሳ በእንስሳት ክልል (Zoo) ውስጥ ከገባ ፃመታት አስቆጥሯል። ታዲያ ይህን ስመለከት በድሃይቱ አገሬ የሚኖሩ እንስሳት ያሳዝኑኛል። በየስርቻው የወደቀ ደረቅ አጥንት የሚለቅሙ፣ ተላላፊው ሁሉ ድንጋይ እየወረወረ የሚያስበረግጋቸው ውሾች፣ ካለአቅሙ ተጭኖ እያቃሰተ በዱላ ኃይል ወደመሩት የሚጓዘው አህያ ምነው ከእኔ አገር ተፈጠሩ ያሰኙኛል።

በእኛ አገር ውሻ ወይም አህያ መባል ትልቅ ስድብ ነው። ግን የአህያን ያህል ማገልገል ብንችል የት እንደምንደርስ አለማወቃችን ይገርመኛል። ለመሆኑ አህያን የስንፍና ምልክት ያደረጋት ማን ይሆን? ከዚህ ሳልወጣ በአሜሪካ የተፈፀመ አንድ ታሪክ ላጫውትህ:-

በአንድ ድርጅት የሚሰሩ አንድ አበሻና አሜሪካዊ መሐከል አለመግባባት ይነሳና የኃይለ ቃል መሰነዛዘር ይመጣል። በዚህ መሃል አሜሪካዊው አበሻውን "you are a dog" ይለዋል። በዚህ የተናደደውና የተንቋሸሸ የመሰለው አዲስ መጥ አበሻ ማመልከቻ ጽፎ በህግ ይከሳል። ጉዳዩ የቀረበላቸው ዳኛ ፋይሉን እያገላበጡ የከሳሽን ቃል መቀበል ይጀምሩና ምንድነው የክስህ ጭብጥ ይሉታል። አበሽ ፉቱን ደም አስመስሎ "ውሻ" ብሎ ሰደበኝ ይላቸዋል 'that is it?' ይሉታል። አዎ ማለት በነገሩ ይገረሙና ታዲያ ውሻ መባል ስድቡ ምኑ ላይ ነው? ሌላ ተጨባጭ ነገር ካለህ አቅርብ አሊያ ግን ጊዜ መግደል መሰለኝ ይሉታል ሳቅ እያፈናቸው።

አበሽ በማታውቀው ነገር ተዘፍቃ ጭንቅ ይይዛታል። "በቃ ይሂው ነው" ይላል ቁና ቁና እየተነፈሰ በችሎቱ የነበረው አድማጭ በሳቅ ማጉረምረም ሲጀምር

"ምን ዓይነት አገር ነው። ዚህ በላይ ምን እንዲለኝ ፈለጉ፣ እስኪገለኝ መጠበቅ ነበረብኝ" እያለ አበሽ ለራሱ ማጉረምረም ሲጀምር ዳኛው ችግሩ ይገባቸውና "ለአሁኑ ፋይሉን ዘግቻለሁ ነገር ግን ያለአግባብ የተከሳሽን የስራ ጊዜ በማባከንህ ኪሳራ መክፈል ይገባህ ነበር" ብለው እየሳቁ ያሰናብቱታል። እና ውሻ መባል ወይም በእንስሳ ስም መጠራት ሙገሳም ባይሆን ከስድብ አይቆጠርም።

ከላይ በአንዳንድ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ባተኮሩ አንዳንድ ነገሮች ላይ አጠር ያለ አስተያየት ለመስጠት ሞክረያለሁ። ነገር ግን እነዚህ ሁሉ አለአንዳች እንከን ይከናወናሉ አለማለቴ ይታወቅልኝ። ሁሉም የየራሳቸው ችግር አላቸው በተለይ ጋብቻ፣ የልጅ አስተዳደግና ሌሎችም መጥፎ ገፅታም ይኖራቸዋል በእነዚህ ላይ በሌላ ጊዜ እመለስበታለሁ። ይህንን እዚህ ላይ እንጠልጥዬ ልተወውና እስኪ በአሜሪካ ስለሚኖሩት ኢትዮጵያውያን አንዳንድ ሁኔታዎች ልንገርህ።

በአሜሪካ ቁጥራቸው ይህን ያህል የሚደርስ ኢትዮጵያውያን ይኖራሉ ብሎ ማስቀመጥ ባይቻልም በግምት ከመቶ ሺህ የማያንሱ እንደሚኖሩ ይገመታል። እንግዲህ ይህንን ግምት ወደፊት አንዳንድ መረጃዎችን በማሰባሰብ የተጠጋጋ ትክክለኛ ቁጥር ለመስጠት እሞክራለሁ። የአበሻ ዘር ሁሉም እንደአቅሙ እድሉ በጠራው ችሎታው በፈቀደለት ቦታ የሰጡትን እየሰራ ወይም በጥቂቱ የራሱ የግል ስራ እያከናወነ ይኖራል። ስለኢትዮጵያውያን የአሜሪካ ኑሮ ከተነሳ ከየት እንደምጀምር እቸገራለሁ። እኛም የሀገራችን ህይወት ነፀብራቅ ነንና እንደእናንተው ተመሳቅለናል። የኑሮ መመሳቀል ሳይሆን የመንፈስ መዘባረቅ ይዞናልና ሁሉንም በአንድ ላይ ለመተርጎም፣ ለመተቸትም ሆነ አስተያየት ለመስጠት እፈራለሁ። ከዚህ ይልቅ አንድ ሃሳብ መጣልኝ ይህንን በተመለከተ ራሱን በቻለ አርዕስት በሰፊው እስከምመለስበት ድረስ በቅርቡ በተፈፀመ አንድ አስቂኝ ገጠመኝ ላውጋህ። ለመሆኑ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ለምን ከአገሩ መውጣትና በተለይ አሜሪካ መምጣት ይፈልጋል? መልሱ አጭርና ግልፅ መሰለኝ።

አገሪቱ በኢኮኖሚ እያሽቆለቆለች በመሄዷ በቂ የስራ መስክ አይገኝም። የሰብዓዊ መብት በተገቢው መንገድ ስለማይጠበቅ ህዝቡ በሀገሩ ላይ የመኖር መብቱ በፍራቻ የተዋጠ ነው። እድገትና ቴክኖሎጂ ለሃገሪቱ ባዳ በመሆናቸው የህዝቡ ፍላጎትና የመንግስት ፍቃደኝነት ሁለት የተለያየ አቅጣጫ ያላቸው ናቸው። መራብ፣ መጠማት፣ መታረዝ፣ ቤት የለሽ መሆን በየጊዜው እያደጉ በመምጣታቸው እነዚህን ለመሸሽ የግድ ካገር መውጣት እንደመፍትሔ ይታያል። በሁሉም አይምሮ ውስጥ "ምንም ቢሆን ከዚህ የማይሻል የለም" የሚል ግምት አለ። ይህንንና በመሳሰሉት ምክንያት ህዝቡ ሳይፈልግ አገሩን ሸሽቶ የተወለደበትን መሬት ወደ ኋላ ጥሎ እግሩ ወደጣለው መጓዝ ከተለመደ ትንሽ ዓመታት አስቆጠረ።

አንዳንድ ከሀገራችን የተገኙ የመረጃ ምንጮች እንደሚጠቁሙት በየቀኑ በአማካይ ከአምስት መቶ የሚያንሱ ኢትዮጵያውያን በህገወጥ መንገድ ድንበር ጥሰው ወደ ጎረቤት አገሮች እንደሚሰደዱ ይገምታሉ። እነዚህ በህገወጥ መንገድ ቤት ንብረታቸውን ጥለው፣ ቤተሰባቸውን ተለይተው ከቤት እንደወጡ የሚቀሩትን እንጂ በህጋዊ መንገድ ተሸኝተው በቦሌ በኩል እንደወጡ የሚቀሩትን ቁጥራቸው በርካታ የሆነ የህብረተሰብ ክፍሎችን አይጨምርም።

በተለይ በአሁኑ ወቅት ከአገር ለመውጣት እድል ማግኘት እንደመጽደቅ የተቆጠረበት ዘመን ሆኗል። ለምን ቢባል ከላይ ከጠቀስኳቸው ምክንያቶች ሌላ ሁሉም በግሉ የየራሱ የሆነ ምክንያት አለው። "አገሩን ለጉልበተኞች ትተን ሰላም ብናገኝ ብለን አገራችንን ለመልቀቅ ተገደናል" የሚል መልስ ቢሰጥህ እንዳይገርምህ። የአብዛኛውም መልስ ከዚህ አያልፍምና። የቀናው እግሩ ያረፈበት አገር ጥሩ መስተንግዶ ይገጥመዋል። ከእሳት ወደ ረመጥ የሆነበት ደግሞ በየስደተኛው ካምፕ ከእስረኛ ያልተለየ ኑሮ ይቀበለዋል። ግን ይህም ሆኖ ወደ ሐገሩ የመመለስ ሃሳብ በፍፁም አይኖረውም። እንደወጡ መቅረት፣ በየስደተኛው ጣቢያ ሬሳው ያለ ቤተሰብና ያለ አልቃሽ እየተጎተተ በየሜዳው አፈር ለብሶ የቀረ ስንት የአገር ልጅ በድን የባዕድ አፈር እንደበላው ቀርቷል መሰለህ።

የአገር ልጅ ወርቃየሁ ከዚህ ሳልርቅ አገር ቤት የተፈፀመ ታሪክ ላጫውትህ። አንዱ የአገር ልጅ በአሜሪካ ውስጥ ያሳለፈው የረዥም ጊዜ የብቸኝነት ኑሮ ያንገፈገፈውና እዚህ ያልተነካካችውን ያገር ልጅ ፍለጋ ወደ አገር ቤት ይጓዛል። ይታይህ በዜግነቱ አሜሪካዊ የሆነ ኢትዮጵያዊ ከረዥም ዓመታት ቆይታ በኋላ አገር ቤት ሲገባ የሚደረግለትን አቀባበል።

መድረሻው አዲስ አበባ ነበርና ከቅርብ ዘመዶቹ ቤት እረፍት በማድረግ የመጣበትን ዋነኛ ጉዳይ ለሚቀርቡት ወንድምና እህት ያዋያል። ዜናው ወዲያው ይናፈስና ቆነጃጅት እየተሽቀረቀሩ እሱ ባረፈበት ቤት መዘዋወርና የአካባቢ ጎረቤት እየመሰሉ ከግቢውም ጎራ ማለት ይጀምራሉ። አንድ ሰሞን ያ ሰፈር የቆነጃጅት ኮረዳዎች አካልና መልክ መወዳደሪያ መስሎ ይከርማል። ይሄ ሁሉ ትርምስ በማያውቁት ባል፣ ካለመዱት ሰው በጋብቻ ተሳስሮ ከአገር ለመውጣት እንጂ በእርግጥ ሰውየውን ወደውት እንዳይመስልህ። እንዲያውም እጣ ፈንታ ሆኖበት ከሴቶች እድል የለውም። ምናልባት ሴቶች ቀድመው የሚያዩት በሬ የመሰለ ፊቱንና ሸፋፋ እግሩን በመሆኑ በአሜሪካ ምድር ሴትን በፍቅር ለመጣል አልታደለም ነበር። አሁን ግን በለስ ቀንቶት አወዳድሮ ለማግባት ዕድል በማግኘቱ በእጅጉ ተደስቷል።

ምርጫው ቀን አስቆጠረና አንዷ ላይ ልቡ ይወድቃል። የቤተሰቧ የኑሮ ደረጃ፣ አስተዳደጓና የትምህርት ደረጃዋ ይጠናና ለጋብቻ ትመረጣለች። ለመተዋወቅ ይባልና አንድ ሁለት ቀን ይጋብዛታል። ስርጉ ብዙም አልቆየ ከ2 ሳምንት በኋላ እንዲደረግ ይወሰንና በእጅጉ የማያቃትን ልጅ በጋብቻ አስሮ ወደ አሜሪካ ለመመለስ ዝግጅቱን ያጠናቅቃል። እንግዲህ አስቂኙ ትርዒት የተጀመረው እዚህ ላይ ነው።

ልጃቸው የአበሻ አሜሪካዊ አግብታ ከአገር ለመውጣት በመብቃቷ በእጅጉ የተደሰቱት የሙሽሪት አባት ወደ አዲሱ አማቻቸው ጠጋ ይሉና አንድ ትልቅ ውለታ እንዲሰራላቸው ይጠይቁታል። ልጄ ይኸውልህ የባለቤትህ ታናሽ እህት ትምህርቷን ጨርሳ እቤት ከዋለች ሶስት ዓመት ሞላት። ምናለ እሷንስ ይዘሃት ብትሄድ? ይሉታል። ድንገተኛው ጥያቄ ያስደነገጠው ሙሽራ ከአንድ ሰው በላይ እንደማይችል ለማስረዳት ይሞክራል። አዛውንቱ ግን ውትወታቸውን በመቀጠል ስለ ትንሿ መልከ ቀናነት እያሞገሱ ትቷት እንዳይሄድ ይማፀናሉ። እዛው ወስደህ እንዳሻህ አድርጋት ከእህቷ እንድትነጠል አልፈልግም። ደግሞም በሃሳብ ትረዳሃለች፣ ደግሞም ተመልከት እያሉ ወደ ትንሿ ልጃቸው ጣታቸውን በመቀሰር "ይህቺን ትተህ ብትሄድ እግዜርም አይወድም" ይሉታል። አፋቸው አውጥቶ ለመናገር ዕፍረት ይያዛቸው እንጂ ዋናው መልዕክታቸው "ይህቺንም አግባና ይዘሃት ሂድ" ነው ነገሩ። "ትልቋን ካገባህ ትንሿን እመርቅልሃለሁ" "Buy One Get One Free" እንደሚሉት ዓይነት፤ አጅሬ በነገሩ ይቸገርና ሌላ አማራጭ እንደሚፈልግ ቃል ገብቶ ቆንጂትን አንጠልጥሎ አሜሪካ ገባ እልሃለሁ። እንዲያው ለነገሩ ይህንን አልኩህ እንጂ ዓረብ በባልንት ተመርጦ ስንቱን ቆነጃጅት እየጫኑ ባህር እንደሚያሻግር ያልሰማሁ እንዳይመስልህ።

ገና ብዙ የምለው አለና እስከዚያው በቸር ያቆየን።
ይግለጡ ነኝ - ከነፋሻዋ ከተማ

---

## የቦክስ መድረክ . . . (ከገጽ 46 የዞረ)

Jungle!" ብሎ የጠራው ይህ ግጥሚያ በታዋቂው የእንግሊዝ ጋዜጠኛ ዴቪድ ፍሮስት "Live Via Satellite .. from ZAIRE!" በሚል ቃል ብርቅ እና ገና አዲስ የሆነውን የሳተላይት communication ዕድገት በተደጋጋሚ እየለፈፈ ዓለም አቀፍ ተመልካችን ለግጥሚያው አፍርቶ ነበር። ዴቪድ ፍሮስትን ለዚህ ስራው የቀጠረው ገና በቦክስ ዓለም ውስጥ በከባድ ሚዛን ዝግጅት ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ አዘጋጅ "promoter" ለመሆን የበቃው ፀጉረ ጨፍራራው ዳን ኪንግ ነበር። የሳተላይት ግኑኝነት (transmission) በዛየሩ ግጥሚያ ዘመን ገና አዲስ ቴክኖሎጂ ስለነበር ለአሁኑ አህጉራዊ የቴክኖሎጂ ግኑኝነት ቀዳሚና በር ከፋች ነበር። በተጨማሪም አፍሪቃን አህጉር በዚሁ የሳተላይት መገናኛ የስፖርት መረብ ውስጥ እንድትዋቀር ያደረጋት ግጥሚያ መሆኑ የማይዘነጋ ነው። ግጥሚያው 62ሺ ተመልካቾች በተገኙበት አዳራሽ ውስጥ በOct, 1974 ተካሄደ። በዛን ወቅት በየቦታው ይነገር የነበረው ኒክሰን ከፕሬዚዳንታቸው ተገደው መውረዳቸው ስለነበረ ይህንን አጋጣሚ ለተለመደው "ውርጅብኝ" አሊ እንዲህ ሲል ተጠቅሞበት ነበር፤ You think the World was shocked when Nixon resigned? Wait till I whup George foreman's behind! በመጀመሪያ ዙር ላይ እየደነሰ ያጠቃ የነበረው አሊ ከሁለተኛው ዙር ጀምሮ መከላከልን መረጠ። ገመዱ ላይ ደገፍ እያለ የፎርማንን ቡጢ ይቀበል ጀመር። ፊቱንና ጭንቅላቱን ብቻ በጓንቶቹ መሃል እያሾለቀ የቲቪውን ካሜራ በአይኑ ይቀጥስ ነበር። አንድ ያቀደው ነገር ያለ ይመስል አንድ ዙር ባለቀ ቁጥር ወደ ተመልካቹ እየዞረ ስሙን "አሊ አሊ አሊ" እያሉ እንዲጮሁ በማድረግ የፎርማንን ሞራል (ምናልባትም የኢላጃ መሀመድንም) ለመስበር ሞከረ። በስምንተኛው ዙር ላይ ከተደበቀበት "Rope a dope" መከላከል ወደ አጥቂነት እመር ብሎ በመውጣት እንከን የማይወጣላቸው ሃይለኛና ተደጋጋሚ ግራ ቀኝ ምቶችን በማሳረፍ ፎርማንን ሪንግ ውስጥ ዘረረው። የአሊ ሻምፒዮናነት እንደገና ያለአንዳች ጥርጥር ተረጋገጠ። የማይወዱት ወገኖችም ጭምር አሊ እውነትም 'The Great' ቦክሰኛ መሆኑን አመኑ። በዛን ወቅት በቬትናም ጦርነት ሳቢያ እርስ በእርስ መከፋፈል ላይ የነበረውን የአሜሪካ ህዝብ በአንድ ብሔራዊ ስሜት ጥላ ስር ለማምጣት በተካሄደው የአገር አቀፍ ዕርቅ ሂደት National Reconcilation ከፕሬዚዳንት ጄራልድ ፎርድ በተላከለት ጥሪ መሰረት መሀመድ አሊ በነጩ ቤተ መንግስት (The White House) የክብር እንግዳ ሆነ። የመጀመሪያው ጥቁር ሻምፒዮና ጃን ጃክሰን "ግብረገብ የለሽ" በሚል ሰበብ ሊከሰስ ሲፈለግ አገሩን ጥሎ ከተሰደዱ ጊዜ ጀምሮ የተፈራረቁት ሻምፒዮኖች የሄዱት ውጣ ውረድ በመሀመድ አሊ የዋይት ሀውስ የክቡር እንግድነት አሳረገ። ለቡጢ ብቻ ሳይሆን ለሚያምንበት ነገር ብዙ ችግሮችን ቻል አድርጎ በመጨረሻ አሸናፊነቱን በቦክሱም ሆነ በተቀረው እምነቱ በመንግስት ደረጃ ታውቆለት ዓለም አቀፋዊ ዝነኛ ለመሆን መብቃቱ የመሀመድ አሊን ትልቅነት ያሳያል። በተጨማሪም የአንድ ስፖርት አጭር ታሪክ በሚካሄዱበት ህብረተሰብ ውስጥ ከሚታየው ከዘር፣ ከፖለቲካና ከኢኮኖሚ ውጥንቅጦች ጋር ውስብስብነት እንዳለው በመጠኑም ቢሆን ለመለየት ያስችላል።

# እንዲህ ሆነ

## በኢትዮጵያ የላንዳፍታ ወኪል የተጠናቀረ

### የፌዴራላዊ መንግስት ምስረታ ተካሄደ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ርዕሰ ብሔር ሆኑ

የሽግግር መንግስት የሥልጣን ዘመን ማክተሙንና በምትኩም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ (ኢፌዲሪ) መመስረቱን ሰሞኑን የተሰየመው የእንደራሴዎች ምክር ቤት አስታወቀ። ከ90℅ በላይ የሚሆነውን መቀመጫ ኢሕአዴግ የያዘው ይህ ምክር ቤት ለሪፑብሊኩ ርዕሰ ብሔርነት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳን ፕሬዚዳንት አድርጎ መርጧል። ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በወለጋ ክፍለሐገር በደንቢዶሎ ከአንድ የፕሮቴስታንት ወንጌላዊ ቤተክርስቲያን መሪ ከነበሩ አባት የተወለዱ፣ በክልሉ ለረዥም ጊዜ የኖሩ የኦሮሞ ተወላጅ መሆናቸው ተገልጿል። ቀድሞ የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር (ኦነግ) አባል እንደሆኑ የሚነገርላቸው ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በጀርመን ለ20 ዓመታት መኖራቸውንና የኢሕአዴግ አባል ድርጅት በሆነው የኦሮሞ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦሕዴድ) በማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነትና በሽግግሩ መንግስት ውስጥ በሚኒስትርነት ሲሰሩ ነበር። የዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ለፕሬዚዳንትነት መመረጥ ኢሕአዴግ አብዛኛውን የአገሪቱን ሕዝብ ቁጥር የያዘውን የኦሮሞን ሕዝብ አመኔታ ለማግኘት ነው ሲሉ የፖለቲካ ታዛቢዎች ይናገራሉ። በሕገ-መንግስቱ ፕሬዚዳንቱ ምንም ስልጣን የላቸውም።

የሽግግር መንግስቱ ፕሬዚዳንት አቶ መለስ ዜናዊ የተወካዮች ምክር ቤት ሊቀመንበርነታቸውን ለአቶ ዳዊት ዮሐንስ፤ የርዕሰ ብሔርነቱንም ስልጣን ለዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ሲያስረክቡ የነበረውን ሥነሥርዓት የአገሪቱ ሚዲያዎች ሙሉ ቀን ሲያስተላልፉ ውለዋል። የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ተዘግተው ሠራተኛው ሥነሥርዓቱን እንዲከታተል ተደርጓል።

በሌላ በኩል አቶ መለስ ዜናዊ የሪፑብሊኩ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው በመመረጥ ቃለመሃላ ፈፅመዋል። በስራ ላይ የዋለው አዲሱ ሕገመንግስት ሙሉ ሥልጣን የሚሰጠው ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በመሆኑ የአቶ መለስ ጠቅላይ ሚኒስትርነት ከብዙ ጊዜ በፊት በሕዝብ ዘንድ ሲወራ እንደነበር ታውቋል።

በሕገ-መንግስቱ መሰረት ጠቅላይ ሚኒስትሩ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥነት ስልጣን ይኖራቸዋል። በቀጣይ በተደረገው ስብሰባም ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የካቢኔ አባሎቻቸውን አቅርበው ያስፀደቁ ሲሆን በዚህም የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ታምራት ላይኔ ም/ጠቅላይ ሚኒስትርና የመከላከያ ሚኒስትር ሆነው ተሹመዋል። መከላከያ፣ የውጭ ጉዳይና የመሳሰሉት ቁልፍ ቦታዎች በኢሕአዴግ አባላት ተይዘዋል።

የመንግስት ምሥረታውን አስመልክቶ የአማራጭ ኃይሎች ም/ቤት ባወጣው መግለጫ ከአስመሳይ ዲሞክራሲያዊነት ወደ ግልጽ አምባገነንነት የተደረገ ሽግግር በማለት አገሪቱ በጥቂት አምባገነን ግለሰቦች በሚመራ ድርጅት መዳፍ ስር ወድቃለች ሲል ኢሕአዴግን ኮንኗል።

### በምሥራቅ ኢትዮጵያ አለመረጋጋት ይታያል

በምዕራብና ምሥራቃዊ ሐረርጌ እንዲሁም በድሬዳዋ ዙሪያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አለመረጋጋት መከሰቱንና በሰላማዊ ዜጎች ላይ ግድያ ዘረፋና ድብደባ መካሄዱን ከአካባቢው የሚደርሱ ዜናዎች ይጠቁማሉ። በሌላ በኩል ሰሞኑን በመካሄድ ላይ በነበረው የምክር ቤት ስብሰባ ላይ አቶ መለስ ዜናዊ ባደረጉት ንግግር "የኦሮሚያ ሙጅሀደኖች"ካሏቸው የኦነግና የኦእነግ ሰራዊት ጋር የኢሕአዴግ ሰራዊት እስካለፈው ሰኔ ድረስ ሲፋለም እንደነበር አምነዋል። ኬር ኢንተርናሽናል የተባለው መንግስታዊ ያልሆነ የዕርዳታ ድርጅትም ለመንግስት ባለስልጣኖች በፃፈው ደብዳቤ በሐረርጌ ጋራሙለታ ከፍተኛ የሆነ የኦነግ ወታደራዊ እንቅስቃሴ በመታየቱና የአካባቢው ፀጥታ በመደፍረሱ በክልሉ የሚያደርገውን የስራ እንቅስቃሴ ለማቋረጥ መገደዱን አስታውቋል።

በተያያዘ ሌላ ዜና ከኮምቦልቻ ወደ ሐረር ይጓዙ በነበሩ ሁለት የነዳጅ ማመላለሻ ቦቴዎች ላይ ባልታወቁ ሰዎች በተከፈተ ተኩስ 5 ሰዎች ሞተው 13 መቁሰላቸው ተዘግቧል። ከሟቾቹ ሁለቱ በስለት ታርደው የተገደሉ ሲሆን የትግራይ ተወላጆች ሳይሆኑ እንደማይቀሩም ተጠቅሷል።

## በውጭ አገር ዜጎች
## ላይ ጥቃት ደረሰ

በተለያዩ ጊዜያት በውጭ አገር ዜጎች የሚደረገው ጥቃት እየተበራከተ መምጣቱን የዜና ምንጮች አስታወቁ። በባሌ ፓርክ በሶፍኦመርና በመሳሰሉት የቱሪስት አካባቢዎች ታሪካዊ ስፍራዎችን በመጎብኘት ላይ የነበሩ ሁለት አውስትራሊያውያን ሴቶች ላይ ማንነታቸው ያልታወቁ ታጣቂዎች ባደረሱት ጥቃት አንደኛዋ መገደሏንና ሌላኛዋ መቁሰልዋን የታመኑ ምንጮች አረጋግጠዋል። አደጋው የደረሰው በመንግስት የፀጥታ አስከባሪዎችና በክልሉ በሚንቀሳቀሱ አማፂ ድርጅት መካከል በተካሄደው የተኩስ ልውውጥ መሆኑንም ዜናው ጨምሮ ገልጿል።

በሊላ በኩል ናዝሬት ውስጥ በአንድ ሆቴል ውስጥ ሲዝናኑ በነበሩ አራት የፖላንድ ዜጎች ላይ በተወረወረው ፈንጂና በተከፈተው ተኩስ አራቱም የፖላንድ ዜጎች ከፍተኛ የመቁሰል አደጋ የደረሰባቸው መሆኑን ተያይዞ የደረሰው ዜና ያስረዳል። በውጭ ዜጎች ላይ የሚካሄደው ጥቃት መበራከት ምዕራባውያን መንግሥታት በኢሕአዴግ መራሹ መንግስት ላይ ያላቸውን ዕምነት ለማፍረክረክ ሳይሆን እንደማይቀር የፖለቲካ ታዛቢዎች ይገምታሉ።

## ሐሪ ጆንስተን
## በኢትዮጵያ ጉብኝት አደረጉ

የፍሎሪዳ ሕዝብ ተወካይ የሆኑት የአሜሪካው ም/ቤት አባልና የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ አባል ለአራት ቀናት በኢትዮጵያ ቆይታ ያደረጉ ሲሆን አዲስ አበባ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ የመንግስት ባለስልጣኖች ፊታቸውን እንዳዞሩባቸውና ሜዲያዎችም ተገቢውን ትኩረት እንዳልሰጧቸው ታውቋል።

ሚ/ር ሐሪ ጆንስተን የመንግስት ባለስልጣኖችን ለማነጋገር የተለያዩ መሰናክሎች እንዳጋጠሟቸውና አቶ መለስ ዜናዊን ለማነጋገር ጠይቀው ፈቃደኛ ሳይሆኑ መቅረታቸውን ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጠቁመዋል። የትኞቹን የመንግስት ባለስልጣኖች እንዳነጋገሩም ከመንግስት የተሰጠ መረጃ የለም። ሐሪ ጆንስተን የሽግግሩን መንግስት በሰብአዊ መብት አያያዝ፣ የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን በማሳደድ፣ ጋዜጠኞችን በማሰርና በፍርድ አሰጣጥ ጣልቃ ገብነት ሲወቅሱ እንደነበር ይታወሳል።

* * *

## ስፖርት....(ከገጽ 27 የዞረ)

(ከገጽ 27 የዞረ)

በመጨረሻዎቹ 2ት ቀናት ከባድ መጨናነቅ ይታያል። የአንዳንድ ዕቃዎች ዋጋ መናር፣ በተለይም ደግሞ ሕጋዊነት የሌላቸው የሙዚቃና የድርሰት ስራዎች ቅጂ መሸጥ፣ በአንድ Booth ሁሉን ነገር መሸጥ፣ (መጠጥ፣ መጽሐፍ፣ ቲ–ሸርት፣ መሸጫ ቦታዎቹን መለስተኛ ዲፓርትሜንት እስቶር ማስመሰሉ) ወደፊት ሊሻሻል የሚገባ ነገር ነው እንላለን። በሜዳው አካባቢ የነበረችው የቡና መሸጫ መደብር የማን ናት? ለየት ማለቷ በብዙ ሰው ዘንድ ጥርጣሬ አሳድራለች።

3. ከፌዴሬሽኑ ቁጥጥር በሆነ ሁኔታ በአንዳንድ ነጋዴዎች የተደረጉ ሥነሥርዓት የጎደላቸው ዘረፋዎች ማዕቀብ የሚደረግበት መንገድ ቢፈለግ ሰውን ከማስመረር ያድናል። በማሪየት ሆቴል አካባቢ ባለ አንድ በአጭር ጊዜ ኪራይ ቤት የተዘጋጀው የምሽት መዝናኛ ለምሳሌ ሊጠቀስ ይችላል። ምግብ ብቻ ለመብላትም ይሁን ለመዝናኛ ወደዚህ ቦታ ለመግባት $10.00 መግቢያ ይጠየቃል። ጣዕም የሌለው ምግብ $7.00፣ ቢራ $5.00 ይሸጣል። በዚህ ላይ ደግሞ ለዘፋኞቹ መሸለም አለ። የአገር ውስጥ ቢራ በ$5.00 ያውም የመግቢያ ዋጋ $10.00 ተከፍሎ ሲሰጥ ምናልባትም በታሪክ የመጀመሪያ ይሆናል። ይህ እንግዲህ ዓይን ያወጣ ስግብግብነት ነው ቢባል ስህተት አይሆንም። በእርግጥ ፌዴሬሽኑ ይህን ለመቆጣጠር ቢያዳግተውም እሱን ብሎ የመጣው ኢትዮጵያዊ ለዚህ ዓይነቱ ዘረፋ እንዳይጋለጥ መግለጫና ምክር ቢሰጥበት ጥሩ ነው።

በዘንድሮው በዓል ፌዴሬሽኑ ያለፈውን ዓመት ገቢና ወጪ በይፋ ማሳወቁ፣ በተጨማሪም እስፖርት ክለቦችን መደጎሙ ጎሽ የሚያሰኝ ነው። የመጨረሻው ቀን ምሽት ፕሮግራምም ሥርዓት ባለው መንገድ የተሳካ ነው። በርቱ እንላለን። እንግዲህ የዓመት ሰው ይበለን!!

ከዝግጅት ክፍሉ

# ጥንቅር ከዚህም ከዚያም

## (በሀገር ውስጥ ከታተሙ የግል ጋዜጦች የተጠናቀረ)

* ያን ጊዜ ድሮ አለባበስ እንደ ፍቅረስላሴ ወግደረስ፣ ፈገግታ እንደፍስኃ ደስታ ነበር የሚባለው። አሁንስ?
● አሁንማ ጊዜው ፊቱን ስላዞረባቸው አከራከስ እንደ ፍቅረስላሴ ወግደረስ ውትወታ እንደ ፍስኃ ደስታ ማለት ተጀምሯል።
* * *

* እነዚህ ሰዎች አሽጋገሩን አይደል?
● ከዬት ወደዬት?
* ከምድጃ ወደ እሳት።
● እውነት ከእንግዲህ አምስት ዓመት ሙሉ ወያኔ ይመራናል?
* ይነዳሃል እንጂ ምን መምራት ብቻ።
* * *

* ለመሆኑ ኤርትራ የት ያመረተችውን ቡና ነው ለዓለም ገበያ የምታቀርበው?
● ዕድሜ ለአቶ ኢሳይያስ ላቦራቶሪ ውስጥ ማምረት ጀምራ ይሆናላ!
* * *

* በጅጅጋ ከተማ የምርጫው ሰሞን የድምፅ መስጫ ኮሮጆ መጥፋቱን ሰማችሁ?
● ሰራቂዎቹ ዕጩዎቹንና ታዛቢዎቹን በኮሮጆው ውስጥ ከተው አለመጥፋታቸውም ደጎች ናቸው።
* * *

* እንዲያው በሞቴ ብፁዕ ወቅዱስ ዶክተር አባ ጳውሎስ ስልጣናቸውን በፈቃዴ አለቃለሁ ቢሉ ምን ይውጠናል?
● አይወጣቸውም? ቢሉም እንኳ ተጋዳላይ ጎይቶምንና አባ ዘርአጽዮንን በአማላጅነት እንልክባቸዋለን።
* * *

* በየክልሉ ባንዲራና ብሔራዊ መዝሙር እንዲኖር ሲወሰን ለምን ዝም ትላላችሁ። የደግ ይመስላችኋል?
● አኮበኮበ ጎፍ ጫማዋ ደረሰ መሂጃዋ እንዳንል የአቃቤ ሕግ ክስ እንፈራለን። በአንድ ሆኖ ከችግር ከመውጣት ይልቅ ተበታትኖ ችግር መጥራት መሆኑን ድሮ ተናግረናል።
* * *

* ልጃገረድና ፈንጣጣ ከአገር ጠፍቷል በተባለበት ዘመን የዚህ ሁሉ ወይዘሪት የጋብቻ ከንዋኔ አባባሉን ሀሰት አያደርገውም ትላላችሁ?

ወ/ሪት ትዕግስት ግዛቸው – ከመርቲ

● የሌሎቹን ተይና የራስሽ እንዴት ነው?
* * *

* የአንድ መንግስት አምባገነንነትና ኃይለኛነት ገደቡ የት ድረስ ነው?

ቶኩማ – ከአምቦ

● እራሱን በራሱ እስኪያጠፋው ድረስ።
* * *

* እያየኋት የምታስቀኝ ሚስት አግብቼ ጧት ማታ ስራዬ ማስካካት ሆኗል። አልጥምም?

ማሙሸት ኃይሉ – ከልደታ

● ኡኡቴ! ድንቄም መጣም!
* * *

* የጉና ው ሚካኤል ይይላችሁና በፕሬዚዳንታችን ላይ መቀለድ ጀመራችሁ አይደል?

በርሄ – ከመቀሌ

● ስንት በአገርና በሕዝብ የሚቀልድ እያለ የእርሳቸው ብቻ ምነው ቆጨህ? ለነገሩ እሳቸው መች ቀልድ ያውቁና!
* * *

* አንድ ሰሞን አስከንፋኝ የነበረች ገርል ፍሬንዴ እየደበረችኝ መጥታለች። በምን ልገላገላት?

ጌታነህ አባይ – ከቦሌ

● አይ የወንዶች ነገር! አንድ ሰሞን መክንፍ ወዲያው ደግሞ መደበር። እስቲ የንስኃ አባትክን አማክራቸው። መገላገያህን ይነግሩህ እንደሆን!
* * *

* በልመና ሥራ የተሰማሩ ዜጎች በዝተዋልና የሥራ ፈቃድ አስፈላጊ ይመስለኛል። እናንተስ ምን ትላላችሁ?

ግርማይ ከቂራ

● እንኳን ፈቃድ ሊሰጥ መንግስት ራሱስ ቢሆን የሚለምነው የሥራ ፈቃድ ይዞ ነው?
* * *

* ምድረ–ጎረምሳ ሸንኮራ ነሽ ስኳር ነሽ ይለኛል። እውነታቸውን መሆኑን እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

ቻሂ – ከአብነት

● አኝከው ሲተፉሽ!
* * *

* ምድረ ኳስ ተጫዋቾችና ሙዚቀኛ አሜሪካ ምን ቀረውና ነው ወደዚያ የሚጎርፈው?

ሻረው – ከሐረር ሰንፈል።

● እንጀራ ነዋ ጌታዬ!
* * *

* የአዲሱ መንግሥት የምሥረታ በዓል መቼ ቢከበር ደስ ይላችኋል?
ሰንዱ ታምራት - ከሜክሲኮ
● አንድ ዓይነት መሆናቸው ካልቀረ መስከረም ሁለት ቢሆን ደስ ይለናል።
* * *

* በየጊዜው እየናረ የሚሄደውን የቤት ኪራይ መክፈል ቋቅ እያለኝ ነው። ምን አባቴ ባደርግ ይሻለኛል?
ጌ.ብ - ከ4 ኪሎ
● በአምስት ብር ላስቲክና በሶስት ብር ሽምበቆ ጥቁር አንበሣ ሆስፒታል አጥር ላይ ለምን የራስህን መጠለያ አትቀልስም? አዲሶቹ ፖሊሶች ሌሊት መጥተው እስኪያፈርሱብህ ድረስ በነፃ ትኖራለህ።
* * *

* እኔ ከወንድ ጋር ተኝቼ አላውቅም። አሁን በቅርቡ ክብረ-ንጽህናዬ ጠፍቶ አገኘሁት። የምን ጉድ ነው እናንተ?
እ.ሽ - ከመካኒሳ።
● እንኳንም ጠፍቶ አልቀረ!
* * *

* አንዴ ያወጣሁትን ወንድ ዳግመኛ ዞር ብዬ ማዬት አልወድም። እንዲህ ሆኜ እስከመቼ እዘልቃለሁ?
ማ. እሸቱ - ከአዲስ አበባ
● የሚያስታምምሽ ሁነኛ ዘመድ ካላገኘሽ ምኑን ዘለቅሽው?
* * *

* ጨካኝና አረመኔ የሆኑትን ሰዎች መግደል ለመጀመር ወስኛለሁ። ከማን ልጀምር?
ተገኝ ፍስሀ - ከናዝሬት
● ከራስህ።
* * *
* ስራ የለኝም። በአውቶቢስ መጓጓዝ ያስጠላኛል። ታክሲ ከዘመድ አዝማድ የማገኛትን ገንዘቤን ጨርሶብኛልና ምን ትመክሩኛላችሁ?
ተፈራ ቀጭኑ - ከውቤ በረሃ
● የትራፊክ ፖሊስነት ለምን አትቀጠርም። እነርሱ እኮ አይከፍሉም።
* * *

* አዲሱ መንግስታችን እነሆ ሊመሰረት ነው። ጭራሽን ስትቆይ የነበርሽ አዳሜ ከእንግዲህ ምን ታደርጊያለሽ?
መሳፍንት - ከውጭ ጉዳይ
● ማነው አዳሜ? እርስዎን ይጨምራል?
* * *

* እዚህ አገር ውስጥ ምነው እንጀራ አልወጣልሽ አለኝሳ?
የሺወርቅ - ከአምቦ
● እስቲ ወጥ ሞክሪ። እጣ ክፍልሽ እሱ ቢሆን።
* * *

* ኧረ! እናንተው! እንደተልባ ስፍር እየተንሸራተተች ላስቸገረችኝ አንዲት ፍቅረኛዬ ምን ስንኝ አላችሁ?
ኃይሌ ፀጋ - ከኮተቤ
● ልብስን አያስጡት እጨንጊት ላይ፣
መውደድን አይጀምሩት እማይሆን ሰው ላይ፣
ያላቃቂ ያለህ ያሰኝ የለም ወይ።
ብንልልዎትስ?
* * *

* የልጆቼ እናት ሚስቴ እቅርባችን ከሚገኝ ከአንድ ወንደላጤ ቤት ሱክ እያለች ተቸገርኩላችሁ። ማንን ልግደል? እሷን ወይስ እሱን?
መንክር - ከመሳለሚያ
● እርስዎ ለምን ከሚች ሊስት ወጡ?

## አንድ ጥያቄ አለኝ

(ዕውቁ ጋዜጠኛ ጳውሎስ ኞኞ በ1960ዎቹ አንድ ጥያቄ አለኝ በሚለው አምዱ ከአንባቢዎቹ ለቀረቡለት ጥያቄዎች የሰጠውን መልስ በማጠናቀር አቅርበንላችኋል።)

* ጥሩ ስዕል እስላለሁ። ደንቆሮ መሳል አቃተኝ። ምን ትመክረኛለህ?
አደም እድሪስ
● ማንኛውም ስዕል ስለህ ደንቆሮ ነህ በለው። ደንቆሮ ይሆንልሃል።
* * *

* አስናቀች ወርቁ ስትዘፍን:-
ውሻ ነህ ውሻ ነህ በጣም ቅቤ በላ፣
ወዲት አደርስከው ያንን ሁሉ መላ። ትላለች እኔ ስለማልጸም ሰደበችኝ ማለት ነው?
ዘላለም ደስታ
● አዎን! ሙልጭ አድርጋ ሰድባሃለች።
* * *
* ብብት ሲነካ አንዳንዱ ይስቃል። አንዳንዱ ደግሞ አይስቅም። ለምንድነው?
በላቸው ይርጉ
● ነርቭ አለች። ያቺ ስትነካ ያስቃል። አንዳንዱ ነርቭ-ቢሱ አይስቅም።

# ወይዘሮ ተዋበች ወልደሚካኤል



1929 - 1987

እናታችን ወይዘሮ ተዋበች ወልደሚካኤል ከእናቷ ከወይዘሮ ወለተማርያም ተሠማና ከአባቷ ከአቶ ወልደሚካኤል ገብረወልድ በ ሬርጌክፍለሀገር በጨርጨር አውራጃ በቁልቢ ከተማ መስከረም 15 ቀን 1929 ዓ.ም. ተወለደች። ወላጆቿ በ1931 የመኖሪያ ሥፍራቸውን በመቀየር ድሬ ደዋ ከተማ ገንደቆሬ ተብሎ በሚጠራው ሠፈር በማድረጋቸው በዚሁ ቦታ ዕድሜዋ ለትምህርት እንደደረሰ በሕጻናት ትምህርት ቤት ፊደል በመቁጠር በከዚራ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ ያለውን ትምህርት ተከታትላለች። ከዚያም አባታችንን ልጅ ዘገየ ይግለጡን በህግ አግብታ አራት ልጆች አፍርታለች። የአባታችን በድንገተኛ አደጋ በሞት መለየት በኑሮዋ ላይ ከፍተኛ ውጤት በማስከተሉና የህግ ባሏን ባጣችበት ሥፍራ ላለመኖር በመወሰኗ አራት ልጆቿን ይዛ ወደ አዲስ አበባ በመጓዝ በወቅቱ እቴጌ እጅ ጥበብ ተብሎ በሚታወቀው አነስተኛ ኢንዱስትሪ ውስጥ በሠራተኛነት ተቀጥራ ራሷንና ልጆቿን በመደገፍ ለ8 ዓመታት አገልግላለች። ከዚያም ከ1960 ዓ.ም. ጀምሮ በትዳርና በግል ሥራ በመተዳደር ራሷንና ቤተሰቦቿን ስትረዳ የቆየች ጠንካራ እናታችን ነበረች።

እናታችን በሕይወት በነበረችበት ወቅት ሃይማኖቷን የምታጠብቅ፣ ከሚያውቋት ጋር ሁሉ በጥሩ ሥነ ምግባሯ የምትደነቅና በአቅሟ የተቸገረን በመርዳት የሚያስመሰግን ታላቅ ባህርይ ነበራት። በተለይ በአፍላ የወጣትነት ዘመንዎ ካፈራቻቸው ልጆች መሀ ል ሆና ስትታይ ታላቅ እህት እንጂ ወላጅ እናት ስለማትመስል ያጣነው እናታችንን ብቻ ሳይሆን እህትና ጓደኛችንንም ጭምር ነው።

እናታችን ባደረባት ሕመም ከሦስት ወራት በላይ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል በህክምና ስትረዳ ቆይታ ሐኪሞች ህይወቷን ሊያተርፉ ባለመቻላቸው በተወለደች በ58 ዓመቷ ሰኔ 2 ቀን 1987 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይታናለች። የቀብሩም ሥነ ሥርዓት ሰኔ 3 ቀን በቅርብ የሚገኙ ልጆቿን፤ ወዳጅ ዘመድ በተገኘበት በአዲስ አበባ ከተማ በቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ቅጽር ግቢ ተከናውኗል።

እታብዬ የሰባት ወንዶችና የአምስት ሴቶች ልጆች እናትና ልጆቿን ከምንም ነገር በላይ የምታፈቅር ግን በአንድነት ሰብስባ መሐ ላቸው ለመሆን ያልታደለችና ይህንንም ቀን በተስፋ እንደናፈቀች የእግዜር ፈቃዱ ሳይሆን በመሃሉ ያጣናት ብርቅዬ እናታችን ነበረች።

የእናታችንን በሞት መለየት በሰማንበት ወቅት ከርቀት በስልክ፣ የሃዘን መግለጫ ካርድ በመላክና በቅርብ ሆናችሁ የሀዘናችን ተካፋይ ለሆናችሁ ሁሉ ከፍ ያለ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

ልጆችዋ
አክሊሉ ዘገየና ግርማ ዘገየ ከአሜሪካ
ትዕግሥት ሽንኩሬ ከካናዳ



የዘጠኝ ወር ቤቴ የዘወትር ናፍቆቴ፤
ወላጅ ብቻ አይደለሽ ጓደኛዬ እናቴ።
በይ ልሰናበትሽ እንዳልል ጠከኝ፣
መቀበል አቃተኝ መሞትሽን አምኜ።
ሁለት ሰው ማጣቴን ያወቅሁት አሁን ነው፤
እናቴ እታብዬ ጓደኛዬ የምለው።

ከግርማ ዘገዬ

# በአትላንታ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ትልቅ በዓል ተደረገ

የአትላንታ ሳህሊተ ምህረት ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ምዕመናን ዓመታዊ በዓላቸውን ደማቅ በሆነ ሁኔታ ነሐ ሴ ፳፪ቀን (August 28, 1995) አከበሩ። በዚህም ታላቅ በዓል ላይ የሰሜን አሜሪካ አገረ ስብከቱ ሊቀጳጳስ ብፁዕ አቡነ ይስሃቅ፣ ብፁዕ አቡነ መልከጸዴቅ የአገረ ስብከቱ ዲን፤ ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ አቡነ መርቆርዮስ እንደራሴ፣ እንዲሁም ካህናት አባ ገብረሥላሴ ከኒው ዮርክ፤ አባ ገብረማርያም ከዲሲ፤ አባ ሲሳይ ከኦሃዮ፤ አባ መንግሥቱና አባ ወልደትንሣይ ከሎስ አንጀለስ በበዓሉ ላይ ተገኝተዋል። ከአትላንታና ከአጎራባች እስቴቶች በበዓሉ ላይ የተገኙ ወደ አምስት መቶ የሚጠጉ ምዕመናን በአገር ልብስ አሸብርቀው ለባዓሉ ትልቅ ድምቅት ስጥተውታል።

ይህ በዓል አንድም ምዕመናን በራሳቸው ጥረት የገዙትንና ታቦቷ የገባችበትን አንደኛ ዓመት ማክበር ሲሆን በሌላ መልኩም ፍልሰታ ማርያምን ለማክበር እንደሆነ ከዝግጅቱ ክፍል ለማወቅ ተችሏል። በወጣው ፕሮግራም መሠረት ሥርዓተ ቅዳሴው በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት እየተመራ እንግዶቹ ካህናትና የደብሩ አለቃ መላከ ፀሃይ ገብረማርያም አያሌው ቆሞስ ተሳትፈውበት ከተካሄደ በኋላ ታቦተ ህጉ ከመንበረ ታቦቱ ወጥቶ በምዕመናን እልልታና ሆታ ታጅቦ በአቅራቢያው ከተዘጋጀ ሜዳ ላይ ካረፈ በኋላ ተመልሷል። እሁድ ማምሻውን ጳጳሳትና ካህናት፣ አዲሱና የቀድሞው የቦርድ አባላትና እንግዶች የተሳተፉበት ስብሰባ ተካሂዶ ቤተክርስቲያኗንና ሌሎችንም ቤተክርስቲያናት በሚያጠናክሩ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይቶች ተካሂደዋል።

## ከበዓሉ ገጽታዎች በከፊል













# የላንዳፍታ አራት ዓመት ዕድገት




መስከረም 1984

ቀደም ሲል በየሶስት ወሩ በኋላም በየሁለት ወሩ እየታተመች አራት ዓመቷን አገባዳ አምስተኛውን ይዛለች። እስካሁን አስራ ሰባት እትሞች አውጥታለች።




መስከረም 1987

ያለፉትን እትሞች ለማዘዝ ለእያንዳንዱ እትም $2.50 ይላኩ።



ጥር 1986




የካቲት 1984

Name______________________________

Addresse____________________________

City____________________ St.____ Zip__________



ህዳር 1987




ሐ ምሌ 1984



ሰኔ 1985



መጋቢት 1986




ጥር 1987



መስከረም 1985



መስከረም 1986



ግንቦት 1986




ሚያዝያ 1987




ጥር 1985



ህዳር 1986



ሐ ምሌ 1986




ሐ ምሌ 1987

ልብወለድ

# የኮለምበስ ጉዞ

## ክፍል 4

## የእናት ሆድ ዥጉርጉር

ከአቢዩ

እንደሻው ሳህሌ ራሱን ስቶ ሆስፒታል ከገባ አራት ወራት ከስምንት ቀን ሆነው። ህመሙ ተሻለው ሲባል እያገረሸበት፤ አገግሟል ሲባል እንደገና እየባሰበት በአሳር ላይ ነው። ደህና ተሽሎት እያለ ሰዓት ለይቶ አንዱን ቀን ድንገት በሽታው ልውጥውጥ ብሎበት እንደአዲስ ይታመማል። ሐኪሞቹ በዕለቱ በደረሰበት አስደንጋጭ ሁኔታ የአንጎሉ ነርቦች መጎዳታቸውን ነግረውታል። የነርቭ ስሮቹ መቀጥቀጥና በራስ ቅሉ ውስጥ ጥቂት የደም መፍሰስ ሳይደርስ አይቀርም ብለው እንደሚገምቱ ነግረውታል። የበኩሉን ጥንቃቄ ካላደረገ ለሞትም ይሁን ለአካል መጉደል ሊያጋልጠው እንደሚችልም አስጠንቅቀውታል። በጥፋተኝነት ስሜት ራሱን እንዳይጎዳና ለዚህ ያበቁትን ሁኔታዎች እያሰላሰለ በሃሳብ እንዳይመሰጥ ደጋግመው ቢነግሩትም በጆ አላላቸውም። እሱም ራሱም ቢሆን ከዚህ ሁኔታ ለመራቅ፣ ለማምለጥ ያቃተው ይመስላል። እንቅልፍ አይወስደውም። በማለዳ ተነስቶ መስኮት ላይ ይቆምና በምትወጣዋ የንጋት ጀምበር ላይ ያፈጣል። ረፈድፈድ ሲል ስሜቱ ይቆስልና ራሱን ጠልቶ አልጋው ላይ ወጥቶ ፊቱን ወደ ግርግዳው አዙሮ ኩርምትምት ብሎ ይጋደማል። አንዳንዴም አይኖቹን ቡዝዝ ፍዝዝ አድርጎ ለረጅም ጊዜ ጭንቅላቱን ይዞ ሲተክዝ ይቆያል። ሌላ ጊዜ ደግሞ እጆቹን እያወራጨ ብቻውን ያወራል። ሚስቱ በዚያን ክፉ ዕለት አስከሬን ክፍሉ ውስጥ ተለክፎብኝ ነው ትላለች። እርሱ እምቢ አላት እንጂ ወደ ጠበል ልውሰድህም ብላው ነበር።

ሰሞኑን የመኝታ ክፍሉ ከፀሐይ መውጫ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ተቀይሮለታል። ጠዋት በማለዳ መስኮት ላይ ቆሞ ከምትወጣዋ ጀንበር ጋር መሟገቱን ለማስቀረት ሐኪሞቹ የፈጠሩት ዘዴ ነው። ግን ብዙም ለውጥ አላሳየም። ጭራሽኑ ሰው ማየት የጠላ ይመስል ጥቅልል ብሎ ፊቱን ወደ ግርግዳው አዙሮ በሃሳብ ሲብሰለሰል ይውላል። ፈታ ብሎ ምግብ አይወስድም። ከባለቤቱና ከታናሽ ወንድሙ በቀር ማንም ጠያቂ ወደ ክፍሉ እንዳይገባ ተደርጓል። ባለፈው ሁለት ሳምንት ከአበባ ጋር የተላከለት የይበልጣል ካፕሬቶ ደብዳቤ ዓይነት እንዳይደርሰውም ሐኪሙ ሳያውቀው ምንም ነገር አይገባለትም። እንደሻው ሳህሌ ግን ጤንነቱ ብዙ አልተሻሻለም።

ዛሬ ይልቅ ከወትሮው ትንሽ ሻል ብሎታል። ደህና እንቅልፍ ተኝቶ አድሯል። ቁርሱንም እንደነገሩ ቀማምሷል። ሰሞኑን ጭፍግግ ብሎ የሐዘንና የመሰበር ጽልመት የዋጠው ፊቱ ቀለል ያለው ይመስላል።

ከታናሽ ወንድሙ ከመልኬ አጎናፍር ጋር እየተጨዋወቱ ነበር። መልኬ ከአልጋው ፊት ለፊት ካለው ወንበር ላይ ተቀምጦ ያወራል። እንደሻው ሳህሌ ግን ብዙ አይናገርም። ወንድምዬውን እያወራውም። እርሱም የሚያወራውን የሚያዳምጥ አይመስልም። የገዛ ወንድሙን የማያውቀው ይመስል ትኩር ብሎ በተመስጦ ሲያየው ይቆይና ከእንቅልፉ የመባነን ያህል ይነቃል። ከዚያም ራሱን እየነቀነቀ በመገረም በዝምታ ይዋጣል። አንዳንዴ ሁለቱ የአንድ እናት ልጆች የሚያወሩት የጠፋባቸው፣ የጋራ የሆነ ጨዋታ የሌላቸው ይመስል በዝምታ በየፊናቸው የየራሳቸውን ነገር የሚያሰላስሉ ይመስላሉ።

"ስማ እንጂ መልኬ!" አለ እንደሻው ሳህሌ ድንገት አንድ ነገር ብልጭ ብሎ እንደታየው ያህል።

"አቤት! ክንዴ ምንድነው?" አለ መልኬ

"እንጠያየቅ እንጂ እኔና አንተ? በደንብ እንድንተዋወቅ። አይመስልህም?"

"ምንድነው የምትለኝ ክንዴ አልገባኝም?" አለ መልኬ ግራ የተጋባ በሚመስል አኳኋን።

"እኮ! እኔም አንተን ወንድሜን የእናቴን ልጅ በደንብ ሳላውቅህ ቆይቻለሁ። አሁን በደንብ ልወቀው እንጂ ማንነትክን? ንገረኝ እንጂ ሁሉን!" አለ እንደሻው ሳህሌ ፈርጠም ብሎ።

"ለምሳሌ ስለምን?" ሲል መልኬ መልሶ ጠየቀው።

"ስለ ሁሉም! በቃ ስለ ሁሉም ንገረኝ። የአንተን ማንነት ማወቅ እፈልጋለሁ።"

"ክንዴ ምንድነው የምትለው? ስለ እኔ ምን የማታውቀው አለህ? ምን ልንገርህ?"

"ለምሳሌ ስንት ልጆች አሉህ?"

"የምን ልጅ ክንዴ? የምን ልጅ አመጣህ?"

"በየስርቻው የወለድካቸው ልጆች! እሺ እስከዛሬስ ስንት ሴቶች ዘንድ ነው ተከርቸም የገባኸው?" አለ እንደሻው ሳህሌ ኮስተር ብሎ

"ማነው እሱ እንደዚህ ዓይነት ወሬ እያመጣ የሚያወራልህ?"

"የምጠይቅህን መልስልኝ። ሁሉንም ሰምቼልሃለሁ። አሁን ከራስህ አንደበት ነው መስማት የምፈልገው። ሰው ሲሞት ወደ መቃብር ሲወርድ ጉዱ እንደሚወጣ ታውቃለህ? አንተም የእናቴ ልጅ ሞተሃል ብዬ የሌላ ሰው አስከሬን እቤቴ አምጥቼ "መልኬ! መልኬ!" እየተባለ ሙሾ ተወርዶልህ መቀበርህ ይረሳሃል? በየስርቻው የፈለፈልካቸው ዲቃላዎችህ "አባቴ! አባቴ" እያሉ እናታቸውን ይዘው እዬዬ ሲሉልህ መዋላቸውን አልሰማህም? ጥሩ አጋጣሚ ነው። አንተም ሥምህም ለዚህች አፍታ ከመቃብር በላይ ናችሁና ሳትደብቅ ሁሉንም ንገረኝ።"

"በቃ እሱ እኮ አለፈ። አንተ ከጭንቀትህ የተነሳ ያደረከውና ለዚህም በሽታ የዳረገህ ስለሆነ ለምን አትረሳውም? ለምን አትተወውም ከንዴ?"

"እንዴት ልተወው መልኬ? ንገረኝ እስቲ እንዴት ልተወው? እዚህ ከተኛሁበት ድረስ የሚመጣልኝና ስለ አንተ የምሰማው አንተን ወንድሜን መሳዬን መልኬ አጎናፍርን የማውቅህ አልመስልህ ብሎኛል። የመንደሩን ልጃገረድ ሁሉ ዲቃላ አሸክመህ የልጅ እናት ማድረግህን፣ ከአባወራ ሚስት ጋር ሳይቀር እንደምትዳራ እየሰማሁ እንዴት ልተወው? ንገረኝ እስቲ መልኬ? እናትህ ከሚሆኑ ባለፀጋ ባልቴቶች ዘንድ ለከርስህ ስትል ጓዝህን ጠቅልለህ እየገባህ ከአንዲቱ ጋ ወደ ሌላይቱ እየተገለባበጥክ ለባልነት የሚከፈልህን ገንዘብ መጠን የምትደራደር ነውረኛ መሆንክን አውቄ እንዴት እተወዋለሁ?" ሲል እንደሻው ሳህሌ በመልኬ ላይ ጮኸበት።
መልኬ የሚመልሰው የጠፋበት ይመስል አንገቱን ደፍቶ ፀጥ አለ።

"እኮ ንገረኛ! ከአንተ አፍ ሁሉን ልስማው?" አለ እንደሻው።

"የሰማኸው አይበቃም ከንዴ!" አለ መልኬ በማስተዛዘን።

"ከአንተው ከባለቤቱ አፍ ልስማው እንጂ" አለ እንደሻው ፍርጥም ብሎ።

"እሺ ምን ልንገርህ?"

"ሁሉንም ንገረኝ መልኬ! ለምሣሌ የአባወራ ሚስት ደፍረሃል።"

"ታዲያ እኔ ምንላድርግ?

"እንዴት ምን ላድርግ? የሰው ሚስት የአባወራ ሚስት? ነውር አይደለም?"

"እቤቴ መጥታ እቀፈኝ ስትለኝ እኔስ ምንልሁነው ከንዴ?"

"ከመነሻውስ ምን ትሠራለች ከአንተ ቤት? "

"ወ/ሮ ጌጤነሽ ግቢ ተከራይቼ የገባሁባት አንዲት ክፍል ቤት ከጭስ ቤቱ መደዳ ነበረችና እርሷም ለባሏ ወስፋት፣ እኔም ለራሴ ከርስ ስርመጠመጥ አንድ ማድቤት ማምሸት መጣ። መጀመሪያ ሰሞን ትንሽ ተፋፈርን። በኋላ ግን ተላመድንና አንድ ሁለት ስንል ተቀራረብን። አንዳንድ ቀንም ከአባወራው ራት እየተጨለፈ እፍታው ይሰጠኝ ጀመር። ልብ በል ከንዴ! የሰው በልቶ ዝም አይባልም። እኔም በተራዬ የሰራሁትን አበላሻለሁ ወንድ የሰራውም ቢሆን ይጣፍጣል አልኳትና አንድ ቀን በጭለማ ተሸሽጋ ጭለማ ለብሳ መጣች። አልጋዬ ጫፍ ቁጢጥ ብላ ያቀረብኩላትን መኮሮኒ ዝም ብላ ይዛው ቁጭ አለች። እንደመጋበዝ አልኩና አጎረስኳት አልተዋጠላትም። በአፏ ውስጥ ስታንገዋልለው ልብ ብዬ አየኋት። አልተዋጠላትም። ለምን እንደሆነ ይገባኛል። እጄን ትከሻዋ ላይ ጣል አደረኩና "ምነው አልጣፈጠሽም?" አልኳት። አትናገርም። የጎረሰችውን መኮሮኒ ከአንደኛው ጉንጯ ወደ ሌላኛው ጉንጯ ታንገዋልላለች። ትክ ብዬ ሳያት አይኖቿ እንባ አቅረዋል። ወደ እርሷ ተጠጋሁና "ምነው ምን ሆንሽ" አልኳት። እንባዋ ድንገት ከጉንጯ ዱብ ዱብ ሲል እቅፍ አደረኳትና ላባብላት ሞከርኩ። አትናገርም። "ምን ሆንሽብኝ?" አልኳት በጉንጮቿ ላይ ኮለል እያለ የሚወርደውን እንባዋን እየጠራረኩላት። "እቀፈኝ መልኬ! እንደሱ አይደለም ጭብጥ አድርገህ እቀፈኝ። ታገልኩ ታጋልኩ አልቻልኩም በቃ ተሸነፍኩ አቃተኝ። እቀፈኝ እቀፈኝ" አለችኝ ትንፋሿ ስቅ እያለ። ይታይህ ከንዴ! የምሸሽበት አልነበረኝም። በቃ የሆነው ሆነ!! ለመደች ተመላለሰች።"

"ጥለሃት አትሄድም። ቤቱን አትለቅም? የሰው ሚስት የአባወራ ሚስት ነውር አይደለም?"

"ወዴት ልሂድ ከንዴ! የስድስት ወር ቅድሚያ ኪራይ ከፍያለሁ። ኬሻ ወንበርና ጠረጴዛ፣ አልጋና ሻንጣዬን ተሸክሜ ከየሰው ማድ ቤት መንከራተት በጣም ሰልችቶኛል። ደግሞ ባልየውስ ቢሆን ሚስቱን መጠበቅና መቆጣጠር የለበትም? ከንዴ! መቼስ ደም ተቀብቶ ዝንብ አይፈራም። ቆንጆ አግብቶም እንቅልፍ ተወዶም አይሆንም። ተዘናግቶም አያዋጣም። ከዓይን ቀድሞ መጠርጠር፣ ማን አናገረሽ? ማን አየሽ? በዬት ገባሽ? በዬት ወጣሽ? እያሉ እንደሰጋር በቅሎ ሚስቱን ማቅናትና መግራት የባለቤቱ ፈንታ ነው። እንግዲህ እኔ ምን ላድርግ? ፍየል ሆዷን ሞልታ ተኝታ ኩላሊቷ ትንቡር ትንቡር ሲል ነብር አይቶ ዝም ይላል?" አለ መልኬ እየሳቀ።

"አንተ ነብሩ ወንድሜ ከእርስዋ ስትጨርስ ወደ አከራይህ ደግሞ ጠጋ አልክ?" አለ እንደሻው በንቀትና በትዝብት እያየው።

"ያው ጉደኛ ማድ ቤት ነው ከእርሷም ያገናኘን። ጊዜ ያለ ጊዜ መጥታ "መልኬ ምነው ተኛህ? ራበህ እንዴ? ወንድ ሲርበው ይተኛል ሴት ሲርባት ትተኛለች አሉ አለችኝ። መጀመሪያ ቀን ዝም አልኳት ሲደጋገምብኝ ጊዜ አንድ ቀን ወጥን የሚጨርስ መጎራረስ ሴትን የሚያስደፍራት መመሳለስ አልኳትና ያዝ አደረኳት።"

"ከዚያስ?"

"ከዚያማ ገንፎ በጣባ ከራስጌዬ ሆነ እንደ እራስ።"

"ከርሳም! ከዚህች ከምታከል ሴት ጋር አታፍርም? እሺ እርሷስ አታፍርም?"

"ክንዴ! ሴት ልጅ በመልክ ቀና ጎረምሳ ይሉኝታ አትፈራም። ፍርሃት የላትም!! ጠሜን ተደፍቼ ስፎክት ከማድር ወንደላጤ ቦታ ሆነህ እየው። አንጀቴ ጠብ ብሎ በልቼ አላውቅም። ላያዛልቀኝ ደግሞ የአባወራ እፍታ ለመድኩ። እንግዲህ ምን ልሁነው?" አለ መልኬ በማስተዛዘን።

"ይበልጣል ካፕሬቶንስ ታውቀዋለህ?" አለ እንደሻው በትዝብትና በጥያቄ እስተያየት

"የማነው ይበልጣል?" አለ መልኬ ራሱን እየነቀነቀ

"እንካ አንብበው ይህንን" አለ እንደሻው የሆነ ኤንቬሎፕ ከኮመዲናው አውጥቶ። መልኬ ኤንቬሎፑን ተቀብሎ ከውስጥ ያለውን ወረቀት አውጥቶ ማንበብ ጀመረ። ለትንሽ ጊዜ ዝም ብሎ ሲያነብ ቆየና።

"አነበብኩት። እና ምንድነው?" አለ መልኬ ምንም ስሜት እንዳልሰጠው ያህል!

"በደንብ አንብበው እንጂ? ከምኔው አነበብከው?"

"አየሁት ክንዴ! በቃ መልዕክቱ ገብቶኛል።"

"የዚህን ሰው ሕይወት ምንኛ እንዳመሰቃቀልክ ይታይሃል? ያደረስክበትስ ጉዳት ይታወቅሃል? ከአነበብከው ምንድነው የገባህ?" አለ እንደሻው አይኖቹን በጥያቄ በመልኬ ላይ አፍጥጦ።

"በደንብ ገብቶኛል ክንዴ! ይበልጣል የሚባል ዘልዛላ ሰካራም ወንደላጤ ማን አለብሽ ትርፌን ሎሚ ስትሸጥ ቡና ቤት አግኝቷት አባብሎአት፣ አግባብቶ ወደ ቤቱ ወስዳት ስካር ያጋለውን እርሱነቱን ለሀጨን አዝረብርቦ እርመጠመጣት። በቃ ያ ጅላንፎ መላቢስ ወንደላጤ ከፎቅ እንደጣሉት የአበባ ማስቀመጫ ከእግሮቿ ስር እንክትክት ስብርብር ብሎ ወደቀ። በአየረቁ ቤቱ ባንኮኒ ላይ በሚስማር የተመታ ያህል ተቸንክሮ አልኮል መጋቱ፣ በእኩለ ሌሊት እየተለፋደደ መግባቱ ቀረና እቤቱ ተኮራምቶ ሎሚ ሻጭ ወዳጁን መጠበቅ ጀመረ። ሳያስበው ሳያውቀው ማን አለብሽን ወዶ ራሱን ከደበቀበት፣ ከተሸነጎረበት፣ እንደልቡ ከሚዋኝበት ከሚምነሽነሽበት መለኪያ ከቬርሙጥ ጠርሙስ ተመንጥቆ ወጣና የዕውር ድመት ሆኖ ተዘፈዘፈ! ቀልበ-ቢስ ወንደላጤ አባወራነት እማረው። በሃሳብ መማሰን ጀመረ። ያለፈ ታሪኳን ማወቅ አሰኘው። አሳ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል ሆነበትና መልኬ አጎናፍርን ከልቧ ጥግ ላይ አገኘው። አስደነገጠው። በረገገ። ወንዶች ስንባል ተላላዎች ሞኞች ነን። የተወደድን ሲመስለን ለሴት ልጅ ብቸኛ ንብረት ለመሆን ፋታ አጥተን ሌላውን ፋታ እንነሳለን። በቃልኪዳን ቀለበት፣ በስማኒያ ውል ሽፋን የንብረት ገቢ ደረሰኝ Receipt Voucher የሚመስል ነገር እንዲቆረጥልን እንቸኩላለን። ግን ውሸት ነው። ማንኛዋም ሴት በእጅዋ ላይ የቃልኪዳን ቀለበት አይኑራት እንጂ በልብዋ ስርቻ አንዱ ጥግ የምትወሽቀው ወንድ አታጣም። በቃ ይሂ ይበልጣል ካፕሬቶም በማን አለብሽ ትርፌ ልብ ውስጥ መልኬ አጎናፍርን ማየቱ አበሸቀው፣ አበገነው።" አለ መልኬ ይበልጣልን ፊት ለፊት ያገኘው ይመስል እያበሸቃቀጠ።

"ግን ይህ ሰው መታረሙን፣ ኑሮው መሻሻሉን፣ መጠጥ እንኳ እርግፍ አድርጎ መተዉን ደብዳቤው ይናገራል" አለ እንደሻው።

"ልዩነት የለውም ክንዴ! በፊት የሕይወቱን መሰረት በቬርሙጥ ጠርሙስ ላይ ነበር የመሰረተው፤ በኋላ ደግሞ በማንአለብሽ ትርፌ ላይ! ራሱን ችሎ በሁለት እግሮቹ መቆም ለማይችል ለእንደዚህ ዓይነቱ ሙጃ እንተን ምን ውሻል አደረገህ? ምን አስጨነቀህ?" አለ መልኬ በመርታት ዓይነት ስሜት።

"እሺ እስከዛሬ ስንት ዲቃላዎች አሉህ?" ሲል ጠየቀው እንደሻው ሳህሌ።

"ነገርኩህ እኮ ክንዴ አላውቅም።"

"እንዴት አታውቅም? ማወቅማ ይኖርብሃል። በየደረስክበት የማታሳድጋቸውን የዲቃላ መዓት ለመፈልፈል ምንድነው ምክንያትህ?"

"ሴት ስትፈጠር በዕድሜ ዘመኗ የተወሰነ ልጅ ብቻ ነው መውለድ የምትችለው። ወንድ ግን በዕድሜ ዘመኑ ቁጥሩ ብዙ የሆኑ ልጆች ማስወለድ ይችላል።" አለ መልኬ ፈርጠም ብሎ "ይህ ነው ምክንያቴ።"

"መልኬ! በፈጠረህ በእግዚአብሔር ስራ አትግባ። እግዚአብሔር እኔና አንተ ከምናውቀው በላይ ታላቅ ነው። ስራው አይመረመርም። ከአዕምሮ በላይ ነው። ምህረቱና ቸርነቱ እጅግ ብዙ፣ ቁጣውም እንደሚባላ እሳት ነው። እንዴት እንዲህ ዓይነት መልስ ትሰጠኛለህ?" አለ እንደሻው ሳህሌ እየተውተረተረ። ደም ስሮቹ ቆመዋል። በግንባሩ ላይ ላቡ ችፍፍ ብሏል።

"ምናለ ይህን አርዕስት ብንተወው ክንዴ! ምናለ ሌላ ነገር ብናወራ?" አለ መልኬ የታላቅ ወንድሙ ደምስሮች መገታተር አይቶ።

"እሺ! ሰው ምን ይለኛል አትልም? ሰው አትፈራም?"

"ሰው?! የትኛውን ሰው ክንዴ?"

"ስንት ዓይነት ሰው አለ?" ሲል እንደሻው ሳህሌ በመገረም ተመለከተው።

"ብዙ ዓይነት ሰው ነው ያለው ክንዴ! እንደሰው የተፈጠረ ነገር ግን እንደሰው እየኖረ ያለ ስንቱ ነው? በሕይወት የስልጣን ተዋረድ ላይም የሁሉ አቀማመጥ እኩል አይደለም። በመርህ፣ በፖሊሲ፣ በመግለጫ እኩል ሊባል ይችላል። ግን አይደለም። ጄኔራልና ተራ ወታደር እኩል አይደለም። አንዱ በሌላኛው ሕይወት ያዛል። አንድ ጄኔራል በሺ የሚቆጠሩ ወታደሮች በየትኛው ጉድባ በምን ዓይነት ሁኔታ መሞት እንደሚገባቸው ይወስንላቸዋል። ሺህ ወታደር ሲሞት መጠነኛ ጉዳት ደረሰ ይባላል። አንድ ጄኔራል ሲሞት አገሪቱ አንድ ሰው አጣች ተብሎ ብሔራዊ ሀዘን ይሆናል። ሚኒስትርና ተራ ሰራተኛ አንድ አይደሉም። አንድ ተራ ዜጋና የሀገር መሪ የሰማይና ምድር ያህል ይራራቃሉ።"

"እና እንዴት ይሁን?" አለ እንደሻው የበለጠ በመገረም።

"በቃ ሆኖ መገኘት ነው ዋናው? የምታዝበት Resource፣ በእጅህ ላይ ያለ የምትቆጥረው ገንዘብ ይኑርህ። በሕይወት hierarchy ከሌላው አስበልጦ ቁብ አድርጎ የሚያስቀምጥህ እርሱ ነው።" አለ መልኬ ልቡን ነፍቶ።

"እንዲህ ስትል አታፍርም መልኬ?"

"ለምን አፍራለሁ? ምን ያሳፍራል?"

"እሺ አትፈር! አብረኸው ያለኸውን በመካከሉ የምትኖረውን ህብረተሰብ አትፈራም?"

"ህብረተሰብ? ህብረተሰብ የምትለው ክንዴ እንደሰው ተፈጥሮ ግን የአውሬ ባህሪውን በልቡ ውስጥ ደብቆ የሚኖር የጠጣው፣ የጅቡ፣ የጅንጀሮው፣ የተኩላው፣ የእራዊት ስብስብ ማለትም አይደል? የተውሳክ፣ የመዥገር፣ የቁጫጩ ጥርቅም፣ የጉሽ፣ የድፍድፍ፣ የአተላው፣ ያልጠራው የጠራው፣ የጥሬው፣ የብስሉ ማከማቻ መሆኑ አይደል? የበሬ፣ የላሙ፣ የበጉ፣ የውሻው መናኸሪያ አይደለም? ያእነዚህን ሁሉ ሕግ እንደልማድ እንደባህል ተቀብሎ እቅፎ ደግፎ የሚጠብቅ ስብስብ ጥርቅም መሆኑ አይታይህም? ታዲያ ምን ሲሆንልህ ምን ሲያደርግልህ? ምንስ እንዳያደርግህ ነው የምትፈራው? ንገረኝ እስቲ ክንዴ!" አለ መልኬ በአሸናፊነትና በመርታት ስሜት።

"እግዚአብሔር ግን ሁሉን ሰው በእምሳሉ ነው የፈጠረው።" ሲል መለሰለት እንደሻው እየተውተረተረ። ደም ስሮቹ ግትርትር ብለዋል።

"ሁሉ ሰው ግን እንደሰው አልኖረም። ክንዴ! ምናለ ይህን አርዕስት ብንተወው። በቃ ሌላ ነገር እናውራ።" አለ መልኬ የወንድሙን የደም ስሮች መግተርተር አይቶ።

"እሺ ህሊናስ አይወቅስህም?"

"እባክህ ክንዴ ተወኝ! የማይመስል ነገር አታውራኝ!" አለ መልኬ በመሰላቸት።

"ህሊና የለህም ማለት ነው? እኮ ይውጣልህ ተናገር። ሕሊና አልፈጠረብኝም በለኝና ልስማህ!"

"ምንድነው ህሊና ክንዴ? እስቲ በደንብ አስረዳኝ። አንዳንዴ እኮ ከምንላቸው ቃሎች ባሻገር ማለት የምንፈልገውን በትክክል የማንገልፅበት ጊዜ አለ። በስንቱ ሰው ውስጥስ ነው ሕሊና ያለው? ሕሊና ራሱ ምንድነው?" አለ መልኬ ትከሻውን እየሰበቀ።

"ህሊና አታውቅም መልኬ? የህሊና ወቀሳ ምን እንደሆነ አይገባህም?" እንደሻው ሳህሌ በመገረምና በጥያቄ በታናሽ ወንድሙ ላይ አፈጠጠ። ከተኛበት ቀና ብሎ አጩንቁሮ ተመለከተው። "ሕሊና አንተ ብቻ የምትሰማው የውስጥህ ድምፅ ነው። ልትሸሸው የማትችለው፣ ልታታልለው ልትሸነግለው የማይሆንልህ፣ ከሌላው ሰው እይታ ተሸሽገህ የፈፀምከውን ክፉ ሁሉ ለእራስህ እያንሾካሾከ እንቅልፍ የሚነሳህ! እንደ ጥላ እየተከተለህ ድርጊትህን ወደ አእምሮህ ጓዳ ብቅ እያደረገ መልሶ መላልሶ የሚያስታውስህ! አንተ ልትረሳው ልትቀብረው የምትፈልገውን እየቆፈረ ሆድህን ሚስጢር የውስጥህን ገበና እንደ ዕንቁ ፍንትው አድርጎ የሚያሳይህ! የሌሎችን ሕይወት በደፈጠጥክበት እርምጃ፣ የሌሎችን ጀምበር ባጨለምክበት ሩጫህ በከሳሽነት የሚሞግትህ! ልክ ነኝ ብለህ አይኖችህን አጉረጥርጠህ ስትንተከተክ ለአንደበትህ ልጓም ሆኖ ለልብህ እንደአለት ከብዶ ያዝ መለስ የሚያደርግህ! ተመቻችተህ ተደላድለህ ባለህበት ለስለስ ባለ ድምፅ

ጠቅ እያረገ ልክ መሆን አለመሆንክን የሚነግርህ አንዳንዴም እየጓጎጠ ጮሆ የሚያስደነብርህ!. . . እርሱ ነው ሕሊና ማለት! በአዕምሮህ ውስጥ በልብህ ጓዳ ከራስህ ጋር የምታደርገው ግብግብና ጦርነት!"

"የምትለው ይገባኛል ክንዴ! ግን . . . "

"ግን ምን? አታምንበትም? አንተ ሕሊና የለህም? ሕሊናህ ወቅሶህ አያውቅም? ውሎ አድሮ የማይወቅስህ፣ የማይቆጠቁጥህ ንፁህ ሕሊና እንዲኖርህ ግድ አይልህም?" እንደሻው ሳህሌ ከአልጋው ጫፍ ቁጢጥ ብሎ እጆቹን እያወናጨፈ ተውተረተረ። መልኬ መልስ አልሰጠውም። ዝምታው የማፈግፈግ አልነበረም። እንደሻው የሚጮህበትን የመቀበሉ ዝምታም አይደለም።

"ተናገር እንጂ! መልስልኝ። ለምን ዝም ትላለህ?" ሲል ጮኸ እንደሻው ሳህሌ።

"ይኸውልህ ክንዴ! የምትለው ይገባኛል። ነገር ግን . . ." አንጠልጥሎ ተወው።

"ግን ምን? ለምን አትናገርም?"

"ሕሊና ብሎ ነገር ክንዴ! ጨው አይሆን በርበሬ! ምግብ አይደል ለተራበ ወስፋት አይሆን! ልብስ አይደል ራቁትነትህን አይሸፍንልህ! ደመወዝ አይሆን ከወር አያደርስህ፣ ወይ ደግሞ ኒሻን አይሆን ከደረትህ ደርድረህ ለሰው አታሳየው! ከምን ሲያደርስ ከምን ሲገባ ነው? ውሎ አድሮ የማይቆጠቁጥህ ንፁህ ሕሊና ሲያወሩት የሚያምር ግን የማትጨብጠው የማትመዝነው ነገር ነው። እሺ! አሁን አንተ ንፁህ ሕሊና አለህ እንበል። ይህ ነው ብለህ የምታቀርበው ምን ማረጋገጫ አለህ? ለሰው የምታሳየው ቀርቶ ራስህን ንፁህ ሕሊና እንዳለህ በምን ታሳምነዋለህ? የስንቱን ሕይወት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የቀጠፈን ወንጀለኛ ንፁህ ሕሊና የለህም ልትለው ምንድነው ማስረጃህ? እስቲ ልብ በል ክንዴ! ሕሊናዬ ንፁህ ነው የማይል ከስንት አንድ ነው የምታገኘው! . . . ሕይወት አንተ እንደምትለው አይደለም ዋልታና ማገሯ የተዋቀረው። የሕይወት እሽክርክሪት ድርና ማጉ እንደሱ አይደለም የተደራው። ንፁህ ሕሊና? የንፁህነት መለኪያውና ሚዛኑ ምንድነው? የሚገርምህ ክንዴ! ለሕሊናቸው ንፅህና የሚጨነቁና የሚጠበቡ ብዙ ሰዎች ዋጋውንም ለመክፈል ብቁዎች አይደሉም። ትንሽ ሲጎነተሉ ከጭብጥ ያንሳሉ። እነርሱ fair ስለሆኑ ሕይወት fairly እንድታስተናግዳቸው ይፈልጋሉ። ይህ ሰይሆን ሲቀር አንዳንዶቹ በእራሳቸው ብስጭትና እልህ ራሳቸውን እየቀጠቀጡ የአልጋ ቁራኛ ቅስመ-ሰባራ ሆነው ይቀራሉ። ክንዴ! ይሄ ሕሊና የሚባለው ነገር ሌሊቱን ሙሉ በጀርባው ተንጋሎ በምቾት ሲያንኮራፉ ማደር ለሚፈልግ ሰነፍ ሰው የሚጠቅም ይመስለኛል።"

"መልኬ! ልጄ ሆይ! የእናቴ ልጅ! ተሳስተሃል። ንፁህ ሕሊና እውነት ነው። እውነት የትም ያደርሳል። የብዙዎቻችን ችግር እውነት ራሷን እውነት ከሚመስሉ ዝባዝንኬዎች ለመለየት አለመቻላችን ነው። የሚያብረቀርቅ ሁሉ ወርቅ አይደለም። እውነት ብለህ የያዝከው ሁሉ በእርግጥም እውነት ላይሆን ይችላል። መልኬ! የአንተን ግን በእርግጠኛነት እነግርሃለሁ። በእውነት መንገድ ላይ አይደለህም። ተሳስተሃል። ልትቀበለኝ ላትቀበለኝ ምርጫው የራስህ ነው። ነገር ግን እውነት ከጊዜ ከስፍራና ከሁኔታዎች በላይ ናት። የከሳች የመነመነች የጠፋች ብትመስል እንኳ አትሞትም። በሕሊናህ ንጽህና ውለታ እንዲከፈልህ ወይ ልትኩራራበት ሳይሆን ለውስጥህ የመንፈስ እርካታና ደስታ ለራስህ የምታደርግለት ውለታ ነው።"

"ገባኝ ክንዴ! ገባኝ! በል ሌላ ነገር እናውራ። አከራካሪ ጉዳይ አንስተን ስንጨቃጨቅ ሀመምህን እንዳልቀሰቅስብህ።" አለ መልኬ የእንደሻው የደም ስሮች ተግተርትረው በማየቱ ፈርቶ።

"የለም አንተወውም። መልኬ! የአንተን እምነት ማወቅ እፈልጋለሁ። ገባህ?"

"የምትለው ይገባኛል ክንዴ! ግን ይህ አንተ የምትለው በውኑ ዓለም ምን ያህል ይሰራል? practically በስንቱስ ውስጥ ታገኘዋለህ? መመዘኛህስ፣ መለኪያህስ ምንድነው?"

"መልኬ! አንድ ነገር ልብ አድርግ። ይቀበለውም፣ አይቀበለውም፤ ልብ ይበለው አይበለውም ህሊና በሁሉም ሰው ውስጥ አለ። ይስማውም አይስማውም ሕሊና በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ ያቃጭላል። ድምፁንም ያሰማል። የእሺታ፣ የእምቢታ መልስ ግን የባለቤቱ ነው። ንፁህ ሕሊና ያለው ሰው ከራሱ ይስማማል። ከእግዚአብሔርም ይስማማል። መልኬ! አንተ ወንድሜ ገንዘብ በምንም ዓይነት ንፁህ ሕሊናን አይተካም። ሕሊና የማይወቅሰው ሰው በድን ነው። ባይሞትም የሞተ ያህል ቁጠረው።" አለ እንደሻው ሣህሌ መልኬን ፊት ለፊቱ ትኩር ብሎ እየተመለከተው። ለአፍታ ሁለቱም በዝምታ ተዋጡ።

"ምነው ዝም አልክ? እምልህ አልጣመህም? አልተረዳኸኝም?"

"የለም ክንዴ ገብቶኛል። የምትለውን ተረድቼዋለሁ። ግን እ . . . "

"ግን ለምን? ለምን አትናገረውም? እሺ በአንተ እምነት በሰዎች ሕይወት ውስጥ ዋና የምትለው ነገር ምንድነው?"

"ክንዴ! ዋናው ነገር ሆኖ መገኘት ነው ብዬሃለሁ። ከየትም አምጣው እንዴትም አግኘው የምትቆጥረው ገንዘብ፣ የምታዝበት በእጅህ ያለ resource! በቃ ዋናው ነገር እርሱ ነው። ገንዘብ ካለህ ሁሉ አለህ። ገንዘብ ከሌለህ እምትላቸው አንዱም አይኖርህም። ገንዘብ አፍ አለው። ድንጋይ ያናግራል። ገንዘብ ካለህ በሰማይ መንገድ አለህ። አለም እንደዚያ ነው የተዋቀረችው።"

"መልኬ! እንዲህ ስትል የምርህን ነው? ይህ ነው እምነትህ? በዚህ ምክንያት ነው እኩያህ ካልሆኑ ሴቶች ጉያ ስር የተሸጎጥከው? እምነቴ ይህ ነው ስትል አታፍርም?" እንደሻው ሳህሌ የገዛ ወንድሙን የማያውቀው ይመስል አይኑን በልጥጦ ተመለከተው።

"ምን ያሳፍራል ክንዴ? . . . ዝም ስል ካልተናገርክ ትላለህ። ስናገር ደግሞ አታፍርም ወይ ትለኛለህ? የእኔን እምነት ከሆነ ማወቅ የምትፈልገው ምንም አያሳፍርም። ዓለም በጥቅም መሰረት ላይ ነው የተገነባችው። በጥቅም ዛቢያ ላይ በጥቅም መዘውር የገንዘብ ኃይል ባላቸው ብርቱዎች ለእነርሱው ጥቅም የምትሽከረከር ትንሽዬ ድቡልቡል ሉል ናት። የእኔ ቢጤውም ለመኖር ሲል በሕይወቱ እስካለ ድረስ ለራሱ ጥቅም አብሮአት ይሽከረከራል። ጥቅም! ለጥቅምህ ስትል ትሮጣለህ፣ ትጥራለህ፣ ትፍጨረጨራለህ፣ ትወጣለህ፣ ትወርዳለህ። ለጥቅምህ ስትል ትጥላለህ፣ ታነሳለህ። ለጥቅምህ ስትል መወጣጫ መሰላል መቆፈሪያ ዶማ ትሻለህ። በቃ የግድ ነው። ታደርገዋለህ። አሁን እኔ እንደምናገረው ሁሉም በግልጽ አይበለው እንጂ ሰው ማለት ከማንም በላይ ራሱን የሚወድ፣ ለራሱ ጥቅም ሲያነፈንፍ፣ ሲያጎደፍር መሽቶ የሚነጋለት ፍጡር ነው። እስቲ ልብ በል ክንዴ! የሰውን ልጅ በእድር፣ በማህበር፣ በማኅበረሰብ፣ በአገር፣ ምን ያስተሳሰረው ይመስልሃል? ምንስ የሚያጋጨው፣ የሚያናቋቁረው፣ የሚያነካክሰው ይመስልሃል? ከአንዱ የዓለም ጫፍ ወደ ሌላው ከአንዱ ምድር ወደ ሌላው ምድር ምን የሚያንከራትተው ይመስልሃል? ዞሮ ዞሮ ያው ጥቅም ነው ከዚህ አይርቅም።"

እንደሻው ሳህሌ በትዝብትና በመገረም ዝም ብሎ ሲመለከተው ቆየና አንዳች ነገር ትዝ ያለው ይመስል ቀና አለ።

"እሺ እንበል አሁን አንተ ወንድምህን በፈላ ውኃ ብትቀቅለው ብዙ የወርቅ ቡችላ ይወጣዋል ቢሉህና በእርግጠኝነት ይህን ብታውቅ እኔን የገዛ ወንድምህን የእናትህን ልጅ በሰታቴ አርገህ በፈላ ውኃ ትቀቅለኛለህ?" አለው ሌባ ጣቱን ቀስሮ።

"አይደለም። ክንዴ! እንደሱ አይደለም። ያልገባህ ነገር አለ።"

"አይደለም አትበለኝ። መልኬ! እንደአባባልህ በአንተ እምነት ሁሉ ነገር በጥቅም ምሶሶ ላይ የቆመ ነው። እናም ከእኔ ወንድምነት ይልቅ በፈላ ውኃ ቀቅለህ የወርቅ ቡችላ ብሆንልህ ጥቅምህ ነው። ይህ አይደለም እምነትህ? አሳምሬ አንተከትክሃለሁ በለኝ እንጂ ለምን እንደርሱ አይደለም ትለኛለህ?" ሲል አፈጠጠበት።

"ይኸውልህ ክንዴ? ስለጥቅም ስታወራ የተፈጥሮ ሕግም አለ። አንበሣ የድኩላ ሥጋ ይጣፍጠዋል። ለመኖር ሲል አድብቶ፣ አድኖ ይይዘዋል። ጅብ የአህያ ሥጋ ይጥመዋል። ነብር የፍየል ደም፣ ጭልፊትም የጫጩት አንጓ፣ ድመትም አይጥ ያስፈልጋታል። ተገላቢጦሹ አይሰራም። ድኩላ የአንበሳ ሥጋ፣ አህያ የጅብን ሥጋ፣ ፍየል የነብርን ደም፣ ጫጩትም ጭልፊት አያስፈልጋቸውም። እንዲሁ አንበሳ የገዛ ደበሎቹን ወይም አሮጌውን አንበሣ ለመብላት አያደባም። ነብር ነብርን አያድንም። ድመትም ድመትን አትይዝም።"

"እና!"

"እናማ! አንተም የገዛ ወንድሜ በፈላ ውኃ ብትቀቀል የወርቅ ቡችላ የሚወጣህ እንኳ ቢሆን አልቀቅልህም ለማለት ነው።"

"መልኬ! ልጄ ሆይ! የእናቴ ልጅ! ሕይወትህን በአደገኛ መንገድ ላይ እየመራሃት ነው። እስከዛሬ አያትህ ከሚሆኑ ዲታ ሴቶች ጉያ ተወሽቀህ ማንነትህን ከደህ የነጠፈ፣ የቀዘቀዘ ስሜታቸውን ስታሞቅ ኖረሃል። አሁን ግን ይብቃህ። እባክህ ሰው ሁን። ፍፃሜህ እጅግ ያስፈራኛል። የአንተ ዳፋ ይሄው ለእኔም ተርፎኝ ለአልጋ ቁራኛነት ዳርጎኛል። እባክህ መልኬ ልብ በል። ልብ ግዛ።" አለ እንደሻው ሳህሌ በማባበልና በማስተዛዘን ሁኔታ! መልኬ የማይረታለት መሆኑ ገብቶታል።

"ክንዴ! ስለ እኔ ብዙ አትጨነቅ። ይልቅስ ፍፃሜህ የምትለኝ ነገር እንደኮሎምቦስ ጉዞ እየሆነ ይመስለኛል።"

"ምን አመጣው ኮሎምቦስን እዚህ? ምን ያገናኘዋል?" አለ እንደሻው በጥያቄ ወደ መልኬ እየተመለከተ።

"ኮሎምቦስ ጉዞ ሲጀምር ሕንድን ፍለጋ ነበር የተነሳው። ከመርከበኞቹ ጋር በውቅያኖስ ላይ ለወራት ሲጓዝ ከርሞ ከዕለታት አንድ ቀን ምድር አየ። ህንድን ያገኘ መስሎታል። ግን ሕንድን ሳይሆን ሰፊዋን፣ ትልቋን፣ ሐብታሚቱን አገር አሜሪካንን ነበር ያገኘው። ጭራሽ ገዥዋ ሆነ። ንብረቱ አደረጋት።"

"እና ከአንተ ጋር ምን አገናኘው? በምኑ ይመሳሰላል?"

"የእኔም ጉዞ እንደኮሎምቦስ ጉዞ እየሆነ ይመስለኛል ክንዴ?"

"እኮ ምን አገናኘው?" አለ መልሶ በጥያቄ አጨንቁሮ እየተመለከተው።

"ይኸውልህ ክንዴ! ከዚህ በፊት አጫውቼሃለሁ። የመጀመሪያ ቀን የዚያን ዕለት ምሽት "ውቢት ፏፏቴ" ቡና ቤት የወሰደኝ ለምለም ኩርኩርን ፍለጋ መውጣቴ ነበር። በአጋጣሚ ግን የሽንብራ አፍንጫ የምታክለዋ ደሃይቱ ለምለም ኩርኩር ቀረችና ከቡና ቤቱ ባለንብረት ከሀብታሚቱ ከውቢት መንገሻ ዘንድ ተገኘሁ። የደጉ ቡጢና እርግጫ ከሚመቸው መኝታዋ ላይ አደረሰኝ። ይሄ አጋጣሚ ሲገርመኝ አንተ ደግሞ ወንድሜን ገድለውት ጥለውታል ብለህ ከሆስፒታል ሆስፒታል ስትንከራተት ውለህ የሌላ ሰው አስከሬን አስጭነህ ከቤትህ አጋድመህ ገዳዮቹ ያልካቸውን ውቢት መንገሻን፣ ደጉንና ደብሪቱን በነፍስ ግዳይ ወንጅለህ በፖሊስ አሳሰርካቸው" አለ መልኬ በእርጋታና በጥንቃቄ!

"እስከዛሬም ሀሊናዬን ዕረፍት የነሳኝና በሽታዬንም ያባባሰብኝ ከራሴ ጭንቀትና ግምት ተነስቼ በነዚህ ንፁሃን ሰዎች ላይ የፈፀምኩት በደል ነው። አንተ ለምለም ኩርኩር ዘንድ እንደእናቲት ፍየል በጫት ገራባ ላይ ተኝተህ ሳይህ የሆነው ሁሉ እንደጨረባ ተንጫጫብኝ። ከጆሮ ግንዴ ስር በምላጭ አንዳች ነገር ቅንጥስ ተደርጎ እንደተቀረጠ ያህል ማጅራቴንና ጀርባዬን ቀዘቀዘኝ። እጥወለወለኝና ራሴን ስቼ ወደቅሁ። ከዚያ በኋላ የሆነውን አላስታውስም። በስንተኛው ቀን ስነቃ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ውስጥ መሆኔን አወቅኩት። መቼስ ድኜ ከዚህ ልውጣ እንጂ መጀመሪያ ወደ ቤቴ ሳይሆን በቀጥታ ወደ ካዛንቺስ ሄጄ ውቢት መንገሻን፣ ደብሪቱንና ደጉን እግራቸው ላይ ወድቄ ይቅርታ እንዲያደርጉልኝ እለምናቸዋለሁ።" አለ እንደሻው ሳህሌ በፀፀትና በጥፋተኝነት ስሜት አንገቱን ደፍቶ።

"ባታገኛቸውስ ክንዴ?"

"በዋስ ተፈተዋል አላልከኝም? የት ይሄዳሉ? ከአገር ለቀዋል?" አለ እንደሻው ሳህሌ በጭንቀት።

"እንዲያው ድንገት አንደኛቸውን ልታገኝ ባትችልስ?"

"እንዴት ነው ልታገኛቸው ባትችል ማለት? ለምን አላገኛቸውም? ምን ሆነዋል? መልኬ ምንድነው ልትነግረኝ የፈለከው?" አለ እንደሻው ሳህሌ ከቅድሙ ይልቅ በጭንቀት ስሜት ተውጦ ከአልጋው ጫፍ ላይ ቁጢጥ ብሎ።

"አይዞህ ክንዴ! ምንም የሆኑት ነገር የለም። አትፍራ።"

"የለም መልኬ! ልትነግረኝ ያለ ነገር መኖሩ ይሰማኛል።"

"የምነግርህ አዲስ ነገር የለኝም። ነገር ግን እነሱን ይቅርታ ስትጠይቃቸው ለእኔ ደግሞ ሟች እኔ አለመሆኔን በፍ/ቤት ቀርበህ እንድታስረዳልኝ እፈልጋለሁ። አሁን አይደለም። ሲሻልህ ማለቴ ነው። ድነህ ስትወጣ።"

"ለምን አስፈለገህ?" አለ እንደሻው በጥርጣሬ።

"አየህ ክንዴ! ነገሩን ከምታውቁት ከአንተና ከጥቂት ሰዎች በቀር መልኬ አጎናፍር የሚባለው ወንድምህ ሰው ገድሎት መሞቱ ነው የሚታወቀው። ለዚህ ደግሞ ከምኒሊክ ሆስፒታል የሚገኘው Death Certificate ከራስ ደስታ ሆስፒታል አምጥተህ ከቤትህ አድሮ በበነጋታው በእድርህ አማካይነት በጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን የተቀበረው አስከሬን ሕጋዊ ማስረጃዎች ናቸው። አገር ያውቀዋል። ስለዚህ ሟቹ እኔ ሳልሆን አንተ ወንድሜ ተገድሏል ከሚል ጭንቀት የተነሳ በስህተት የሌላ ሰው አስከሬን ወደ ቤትህ መውሰድህን፣ በዚያው ምሽት እኔን ስታየኝ ራስህን ስተህ ሆስፒታል መግባትህን፣ በማግስቱ ስለነገሩ ምንም የማያውቁት ዕድርተኞችህ ከራስ ደስታ ሆስፒታል ያመጣኸውን የሌላ ሰው አስከሬን ጊዮርጊስ መቅበራቸውን ቀርበህ ለፍ/ቤት ካላስረዳህልኝ እንደ ሕጉ መልኬ አጎናፍር የሚባል ሰው በሕይወት መኖሩን ለመቀበል አይቻልም።" አለ መልኬ በቀስታና በጥንቃቄ ቃላት እየመረጠ ሁኔታውን ለማቅለል እየሞከረ።

"ለምን አስፈለገህ? ንገረኝ! መኖርህን ለማረጋገጥ ፍርድ ቤት ድረስ የሚያደርስ ነገር ምን አገኘህ?" ሲል እንደሻው በጥያቄ አፈጠጠበት። የፍርሃት የጥርጣሬና የጭንቀት ስሜት ፊቱ ላይ ጎልቶ ይታያል።

"የለም ክንዴ! ብዙ አትጨነቅ። ይህ ህግ የሚጠይቀው ፎርማሊቲ ነው" አለ መልኬ ነገሩን ለማቅለል የፈለገ በሚመስል አኳኋን።

"እውነት? ሕግ የሚጠይቀው ፎርማሊቲ?" አለ እንደሻው በትዝብትና በጥርጣሬ!

"የወርቅ ቡችላ እንዲወጣኝ በፈላ ውኃ ውስጥ እየጣድከኝ አለመሆንክን በምን አውቃለሁ? ቅድም ስትለኝ የነበረውን መቆፈሪያ ዶማ መወጣጫ መሰላል እያደረግከኝ ቢሆንስ እንዴት ላምንህ እችላለሁ?" አለ እንደሻው ሳህሌ አልጋው ላይ ቁጢጥ እንዳለ በጥርጣሬና በጭንቀት እጆቹን እያወናጨፈ።

"እመነኝ ከንዴ! ግድየለህም።"

"አላምንህም። ፈጽሞ አላምንህም መልኬ! ምንህ ይታመናል? ፍርድ ቤት ድረስ የሚያስኬድና ምስክር አስቆጥረህ በሕይወት መኖርክን ማረጋገጥ ለምን እንዳስፈለገ አይገባኝም። ግን ከምንም ተነስተህ እንዳች የጥቅም ነገር ሳይኖርበት ይህን አታደርግም። ለዚህ እርግጠኛ ነኝ።"

"ግድ የለህም ከንዴ እመነኝ!" እንዲህም ብዙ አትጠርጥረኝ። ወንድምህ ነኝ መሳይህ! ከአንድ ማኅፀን የወጣን የእናትህ ልጅ።"

"እርሱን አላጣሁትም መልኬ። ግን የእናት ሆድ ዥጉርጉር ነው። እኔና አንተ ከአንድ ማህፀን የወጣን የአንድ እናት ልጆች ብንሆንም እንኳ አይነታችን ለየቅል ነው። ባህርያችንና ነገራችን አይጣጣምም። ለምን አልፈራህ? ለምን አልጠረጥር? እምነትህን የሕይወት መመሪያህን እየነገርከኝ! ሀሊና የማይወቅስህ፣ እግዚአብሔርን የማትፈራ መሆንክን ሳውቀው! ለዚህስ ያደረሰኝ የአንተ ጣጣ አይደለም? ትክዳለህ? ዳግመኛ አለመሳሳቴን እንዴት እርግጠኛ መሆን እችላለሁ? ሞኝ ሰው እባብ ሁለቴ ይነድፈዋል ይባላል። አንዴ ሳያይ ሁለተኛ ሲያሳይ! የመጀመሪያውን ሳልድን ፍ/ቤት ቆሜ ስንዘራዘር ሁለተኛ መነደፌስ ቢሆን እንዴት አውቀዋለሁ?"

"አንተ እኮ በሆነው ነገር ሁሉ ሀሊናህ ንፁህ ነው። ያደረከው ነገር ከራስህ ጥንቀትና ግምት ተነስተህ እንጂ ማንንም ለመጉዳት ብለህ አይደለም። አሁንም ፍርድ ቤቱ የሚጠይቅህን ብቻ ማስረዳት ነው። ሌላ ነገር እንድታደርግ አትጠየቅም። ይህን ያህል ምን አስፈራህ?"
"አትሸንግለኝ መልኬ! ንፁህ ሕሊና ሞኝነት አይደለም። አይምሰልህ! እንደ ፋሲካ ሰንጋ ለእርድ መጎተትም አይደለም፤ ወይም ደግሞ ሌላውን መያዣ መንጠቆ ሆኖ በየዋህነት ለመሰሪዎች መጠቀሚያ መሆንም አይደለም። ለህሊናው ንጽህና የሚገደው ሰው እንደእባብ ብልህ እንደእርግብም የዋህ ይሆናል። በማስተዋልም በጥንቃቄም ይራመዳል። እኔስ ይህን ነው እያደረኩ ያለሁት? ለዚህ ነው ምክንያቱን ካልነገርከኝ ተገድጄ እንኳ ፍርድ ቤት ብቀርብ አልናገርም እምልህ። እስቲ ንገረኝ ለምን አስፈለገ? መልኬ! ምክንያቱን ካላወቅኩት በማንጅራቴ ብታርደኝ ፍ/ቤት ቀርቤ አልናገርም።"

"ከንዴ! ምን ጠርጥረህ ነው ይህን ሁሉ የምትለኝ?"
"የንብረት ነገር፣ የውርስ፣ የፍትሐብሔር ነገር እጠራጠራለሁ። መኖርህን ለማረጋገጥ የሕግ ፎርማሊቲውን ብቻ የማሟላት ጉዳይ መስሎ አይሰማኝም። የደበቅሽኝ ነገር እንዳለ እጠረጥራለሁ። "አለው እንደሻው መልሶ ትክ ብሎ እያየው።

"አይደለም። ከንዴ ልደብቅህ አይደለም። ስሜትህን እንዳልጎዳህ ፈርቼ ነው።" አለ መልኬ ትንሽ እንደማቅማማትና እንደመሽማቀቅ እያለ።

"እውነቱን \አውቄው በማደርገው ነገር ስሜቴ አይጎዳም። ግድየለህም ንገረኝ።"
"ይኸውልህ ከንዴ! ውቢት መንገሻ በፖሊሶች የተወሰደች ዕለት ማታውኑ ክፉኛ ታመመች።"

"እና ሞተች ነው የምትለኝ መልኬ!" አለ እንደሻው ሣህሌ በድንጋጤ መላ ሰውነቱ እየተርበተበተ። ጥርሶቹ ተንገጫገጩ። ፊቱ በአንዴ ሳንባ መሰለ። ዓይኖቹ ፈጠው ቀሩ።

"አልሞተችም። ቆይ ከንዴ ረጋ በል ላስረዳህ። የተያዘች ዕለት ማታውኑ ታመመች። ሕመሟ አዕምሮዋን የመሳት ስለነበር ስትለፈልፍ ነበር አሉ። በሶስተኛው ቀን በጣም ብሶባት ልብሷን እየቀዳደደች እርቃኗን መሆኗን ስትጀምር ፖሊሶች አማኑኤል እብዶች ሆስፒታል አስገቧት። እዚያ የሚከታተላትም ሰው ስላልነበራት በጣም ባሰባት። በቃ ለየላት። አበደች። ከሆስፒታሉ እንዴት እንደወጣች ሳይታወቅ ወጥታ ጠፋች። በአዲስ አበባ ውስጥ ያልተፈለገችበት የለም። እስካሁንም እያስፈለኳት ነው። ከሆስፒታል ወጥታ ስለመጥፋቷና ስለነበረባት የአዕምሮ ህመም የሆስፒታሉ ሐኪም ቀርበው ለፍ/ቤት አስረድተዋል።" አለ መልኬ አይኑን በታላቅ ወንድሙ ላይ ተክሎ። እንደሻው ሳህሌ ከቅርብ ርቀት ተተኩሶ እንደተመታ ያህል መላ ሰውነቱ ኩምትርትር አለ።

"ወይኔ እንደሻው! ወይኔ እንደሻው ሳህሌ . . . ወይኔ! ወይኔ! የንፁህ ሰው ሕይወት በእጄ ጠፋ!! ወይኔ እንደሻው! በማታውቀው ነገር የዚህችን ሰው ሕይወት አጨለምኩ። ወይኔ! ወይኔ!" እያለ ስቅስቅ ብሎ ማልቀስ ጀመረ። በሁለት እጆቹ እናቱን ይዞ አንገቱን አቀርቅሮ ተንሰቀሰቀ።

"ይኸውልህ ከንዴ! አሁን የአንተ እንባ ምንም አይጠቅማትም። ይልቅስ በየአቅጣጫው ሰው አሰማርቶ ለማስፈለግና ብትገኝ እንኳ ለማስታመም ያላት ገንዘብ፣ ሀብትና ንብረት መከበር አለበት። ታውቃለህ ከንዴ! ይህቺ ሴት ልጅ አልወለደችም። የቅርብ ዘመድ የላትም። ዕድሜዋን ሙሉ የደከመችበት ሀብቷን መንግስት ሳይወርሰውና የትም ተበትኖ ማንም ተቀራምቶ ከመጥፋቱ በፊት አንድ ነገር ማድረግ አለብን። ከንዴ! ሁኔታው እንዲገባህ ያስፈልጋል። ጊዜ ሳናባክን በአፋጣኝ አንድ ነገር ማድረግ ይኖርብናል። በባንክ ደብተሯ ከ750,000 ብር በላይ አለ። በመኖሪያ ቤቷ ከ50,000 ብር የማያንስ ጥሬ ገንዘብ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የቤት ቁሳቁስ፣ ጌጣጌጦቿ እንዲሁም ቡናቤቱና በውስጡ ያለው ንብረት፤ በጠቅላላው ብዙ ሚሊዮን ብር ግምት ያለው ንብረት በስሟ አለ። ይህን ዝም ብለን

መበተን አንችልም። ለዚህ ነው አንድ አፋጣኝ ነገር ማድረግ ያስፈልጋል የምልህ! ለጊዜው ያለሁት የቅርቧ ሰው እኔ ብቻ ነኝ። ፊርማም ባይኖረን አብረን መኖራችን በሕጉ የባልና የሚስትነት ያህል ዕውቂያ ስለሚኖረው ለፍ/ቤት ቀርቤ አመልክቻለሁ። እስመስክሬያለሁም። በሕይወት እስክትገኝ በስሟ ያለው ንብረት እንደጋራ ንብረታችን ተቆጥሮ በሞግዚትነት ለማስተዳደር፤ በሕይወት ባትገኝ ደግሞ ፍ/ቤቱ የመጥፋት ውሳኔ ቢሰጥ የወራሽነት መብቴ እንዲጠበቅልኝ ውሳኔ እየተጠባበቅሁ ነኝ። ሁሉ ነገር አልቆ ለውሳኔ የቀረው የኔን በሕይወት መኖር ለማረጋገጥ ያንተ ምስክርነት ብቻ ነው። ይታይህ ከንዴ! ያንተ ፍ/ቤት ሄዶ መመስከር ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ! ትሰማኛለህ ከንዴ! ያንተ ፀፀት እንባ ወይም የሐሊና ወቀሳ ለውቢት መንገሻ ምንም የሚፈይድላት ነገር የለም። ባለፈው በሆነው መፀፀቱ ሳይሆን ልታደርገው በሚገባህ ነገር ልትረዳት ይገባል። ይህ አጋጣሚ ካለፈ ነገ ሌላ ፀፀት ሌላ ቁጭት ነው የሚያመጣብህ።" አለ መልኬ ከተቀመጠበት ወንበር ተነስቶ አንገቱን ደፍቶ እየተንሰቀሰቀ የሚያለቅሰውን ወንድሙን ትከሻ ይዞ። "ትሰማኛለህ ከንዴ! ማንም ይብላው ይህን ገንዘብ? የትም ተበትኖ ይቅር ነው የምትለው? ይህቺ ሴት ትሙትም ትኑርም የደከመችበትን ሀብቷን ላስከብርላት አይገባም?" አለ መልኬ ሁለት እጆቹን እያወናጨፈ። የሚናገራቸው ቃላት ወንድሙ እንዲሰማቸው ብቻ ሳይሆን ወደ ሰውነቱ ዘልቀው እንዲገቡ የፈለገ በሚመስል አኳኋን።

እንዳሻው ሳህሌ አንገቱን ደፍቶ ፊቱን ትራስ ውስጥ ቀብሮ ስቅስቅ ብሎ ያለቅሳል። እየደጋገመ "ወይኔ እንዳሻው ወይኔ እንዳሻው ...ውቢት መንገሻ አበደች!...ራቁቷን ሄደች!...ጠፋች!...ወይኔ! ወይኔ! ወይኔ እንዳሻው!" እያለ መላ ሰውነቱ እየተርገፈገፈ ይንሰቀሰቃል። መልኬ የሚነግረውን የሚሰማ አይመስልም። መልኬም ማለት የፈለገው ያለቀበት ወይም የጠፋበት ይመስል እጁን አጣጥፎ ፈዞ ቆመ። እንዳሻው ለትንሽ አፍታ ትንፋሹን ዋጥ አድርጎ ዝም ብሎ ቆየና "ወይኔ እንዳሻው" ብሎ ጮሆ ተስፈንጥሮ እወለሉ ላይ ተከሰከሰ። መልኬ በድንጋጤ ከቆመበት መንቀሳቀስ አቃተው። ዞር ብሎ ቀና ሲያደርገው ደም በአፍንጫው ተለለለል ብሎ ይፈሳል። የለበሰው ቢጃማ በደም ነጠብጣብ ቀልሟል። ወዲያው ሐኪሞችና ነርሶች ተሯሩጠው መጥተው ክፍሏን ሞሏት። ከእንደሻው አፍንጫ የሚፈሰው ደም አስደንግጧቸዋል። ዳግመኛ ራሱን ስቷል። አልጋው ላይ አጋደሙትና መልኬን ከክፍሉ አስወጥተው ዘግተው አልጋውን ከበው ቆሙ። መልኬ አጎናፍርም በድንጋጤ፣ በተመሰቃቀለና ግራ በመጋባት ስሜት በተዘጋው በር ላይ ዓይኖቹን ተክሎ ፈዞ ከውጭ ቆመ የኮሎምቦስን ጉዞ እያስሳሰለ!!

* * *


# ሀናና ብንያም
# የልብስ ስፌትና ዲዛይን
# H & B TAILORING

የሠርግ የሚዜ ልብሶች በትዕዛዝ እንሠራለን።

ጤፍ ዱቄት
በሶ
እልበት
ቡና
በርበሬ
ሚጥሚጣ
ሽሮ
ቅመም በያይነቱ
በተጨማሪ
የቪዲዮ ካሴቶች
የቴፕ ካሴቶች
የተለያዩ መጽሄቶች

**ወለላ ወርቁ**
**WOLELA WORKU**

LEMO SERVICE
ለሠርግና ለልዩ ዝግጅት
የሌመዚን አገልግሎትም
እንሰጣለን።
1-800-679-1816
Pager- 738-7783

**የተለያዩ የአገር ባህል ልብሶች እንሸጣለን።**

**ቆንጆ ጤፍ እንጀራም እንሸጣለን ጎብኙን!**

**431 North Indian Creek Rd Suite E**
Clarkston, GA 30021
Phone: (404)296-2766
Pager - 632-6283

## የሲያትሉ ዳሽን ሻምፒዎና ሆነ

12ኛው የሰሜን አሜሪካ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ያዘጋጀው ዓመታዊ የእስፖርት በዓል በሳንዲያጎ ከተማ ከJuly 2, 1995 - July 9, 1995 በደማቅ ሁኔታ ተከናውኗል። የዓመቱም የእግር ኳስ ሻምፒዮና የሲያትሉ ቡድን ሆኗል። ይህም የሆነው የሲያትሉ ዳሽን ቡድን July 8, 1995 ከሎስ አንጀለሱ ዳሎል ቡድን ጋር ባደረገው የመጨረሻ ማጣሪያ ውድድር ዳሎልን አሸንፎ የቶሮንቶን ቡድን 4ለ1 ያሸነፈውን የአትላንታ ቡድን 3ለ2 በማሸነፍ ነው። በመጨረሻው ቀን በሜሳ ኮሌጅ በተደረገው የዋንጫ የመጨረሻ ጨዋታ በብዙ ሺህ የሚቆጠር ተመልካች ተገኝቶ ነበር። በብዙ ተመልካች ዘንድ የነበረው ግምት የመጨረሻው ጨዋታ በአትላንታና በኤል ኤው ዳሎል መካከል ይሆናል የሚል ነበር። የዓመቱንም ዋንጫ አትላንታ እንደሚወስድ ቀደም ብሎ ባሳያቸው ጨዋታዎች ተገምቶ ነበር። ፍፁም ያልተጠበቀው የሲያትል ቡድን ባደረገው ሽግዩ ጨዋታ በመጀመሪያ ዳሎልን አሸንፎ ለመጨረሻው ግጥሚያ ማለፉ፣ ቀጥሎም ለዋንጫ መብቃቱ ብዙውን ያስገረመ ነገር ነበር። የሲያትሉን ዳሽን ቡድንን እንኳን ደስ አላችሁ እንላለን።



የዘንድሮው ሻምፒዎና የሲያትሉ ዳሽን ቡድን

ቀደም ባሉት ቀናት ለዚሁ የዋንጫ ጨዋታ ከተለያዩ እስቴቶች ከካናዳ፣ ከእንግሊዝና ከስዊድን በመጡ በጠቅላላው 26 ቡድኖች መካከል የተደረጉት የማጣሪያ ጨዋታዎች ተመልካቾችን ያስደሰቱ፣ በቡድኖች መካከል ወንድማዊ ፉክክር የታየባቸው ነበሩ። ይሁን እንጂ በብዙ ቡድኖች መካከል ይታይ የነበረው አለመመጣጠን አልፎ አልፎ ተመልካቾችን ያሰለቸ መሆኑ ታይቷል። ይህ አለመመጣጠን በሚገኙ ግቦች ለምሳሌ (10 ለ 0)፣ (9ለ0) መሸናነፍ ገና በመጠናከር ላይ ያሉ ዝቅተኛ ቡድኖችን ተስፋ የሚያስቆርጥ እንዳይሆን ያሰጋል። ምናልባትም በሁለት የተለያዩ ዲቪዥኖች ቡድኖችን የመከፋፈል ሁኔታ ቢኖር ችግሩን ለማቃለል ይረዳል የሚል ግምት አለን። የዘንድሮው ውድድር ብዙ ቡድኖች የተሳተፉበት ቢሆንም በተመልካች በኩል ከዚህ በፊት በዲሲና በሌሎች ቦታዎች ከታየው በጣም ያንሳል። ምናልባትም ከቦታው ማዕከላዊ አለመሆን ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለ።

### ጠቅላላ ዝግጅቱን በተመለከተ

የሚከተሉትን የተገነዘብን ሲሆን ለወደፊቱ የማሻሻያ ሃሳቦች ሆነው ሊታዩ ይችላሉ።

1. ሳንዲያጎ ከተማ ደስ የምትል ከመሆኗም በላይ ብዙ የቱሪስቶች መስህቦች አሉዋት። ሳምንቱን በሙሉ ጨዋታዎች ስለነበሩ ብዙ ኢትዮጵያውያን አንድም ከፕሮግራሙ ጥበት ሁለተኛ የአካባቢውን ሁኔታ በደምብ ካለማወቅ እነኚህን የቱሪዝም ቦታዎች ለመጎብኘት ዕድል አላገኙም። ስለዚህም በምሽት ዝግጅቶችና መዝናኛ ቦታዎች ላይ ብቻ በመገኘት በአልኮል መደሰት፣ በየፓርቲዎች ላይ ብቻ ተገኝቶ መጨፈር ይታያል። በፕሮግራሙ ዝግጅት በኩልም ይሁን በአካባቢው መጎብኘት የሚገባቸውን የቱሪስት መስህቦች የዝግጅት ክፍሉ ተመልካቾች እንዲያውቁት ቢያደረግ መልካም ይመስለናል።

2. የተለያዩ የባህልና ኢትዮጵያ ነክ ዕቃዎችና ምግቦች መሸጫ ቦታ በጣም አነስተኛ በመሆኑ በተለይ

(ወደ ገጽ 12 ይዞራል)

# ኑሮ በአሜሪካ

በአሜሪካ ኑሮአችሁ ምን ገጠማችሁ? ኑሮን ለማመቻቸት በሚደረጉ ጥረቶች ላይ ባሉ የማህበራዊ ኑሮ ችግሮች ላይ ለመወያየት ይህ አምድ አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚል እምነት አለን። በውይይት የጋራ መፍትሄ ለማግኘት ይቻላል የሚል እምነት አለን። በተጨማሪም በዚህ አገር ኑሮአችን ተሰባስበን በጋራ የምናከናውናቸውን ተግባራት ለማስተዋወቅም ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል እንላለን። አንዱ ከሌላው ልምድ ሊማር ይችላልና። በአምዱ ላይ በተለይ ካልተጠቀሰ በስተቀር የሚቀርቡ አስተያየቶችም ሆነ የገጠመኝ ታሪኮች አንባብያን የሚልኩት መሆኑ ይታወቅልን።

## "እልፍ ሲሉ እልፍ ሊገኝ"

ከአትናትዮስ

### ክፍል ሶስት

ከፀሐይ ጋር ከተለያየሁ በኋላ ትንሽ ግራ የሚያጋባ ጊዜ ነበር የሆነብኝ። እርፎ መቀመጥ መፈለግም አለ፤ ይቅርብኝ እግዚአብሔር እኔን ለጋብቻ አልፈጠረኝም ብዬ እንደማስብም አድርጎኝ ነበር። እንግዲህ ጋብቻን ፈልጌ ካላገኘሁት እሱ ይፈልገኝ ብዬ ተስፋ ቆርጬ ቁጭ አልኩ። አንድ ሁለት ወር ያህል እንደቆየሁ ሌላ ሁኔታ አጋጠመኝ። ይህን ታሪክ ሰፋ አድርጌ ልንገራችሁ። ዓርብና ቅዳሜ ሲመጣ ማመሻሸት አይቀርምና አበሾች ለመዝናናት አይሄዱም ብዬ ካሰብኩበት የብሉስ ክለብ ሄድኩ። ሃሣቤ እንኳ እንደው አለ አይደል ምንም ይሁን ምንም የሌሊት ብቸኝነቴን ለማስታመም ብረሳ በማለት ነበር። ክለቡ ሞቅ ብሏል።

ሙዚቃው ለስለስ ያለ ብሉስ ቢሆንም ሰው ደስታውን በጩኸት በጭብጨባና በፉጨት ስለሚገልፅ ደመቅ ያለ ነው ለማለት ያስኛል። አንድ ጥግ ፈልጌ ቁጭ አልኩ። ለምን እንደሆነ እንጃ የትም መዝናኛ ክለብ ይሁን ምግብ ቤት ስሄድ ጥግ መቀመጥ ነው የምፈልገው። እኔ ብቻ ሳልሆን ብዙ አበሾች የምንፈልገው እንዲሁ እንደሆነ ይሰማኛል። ቀዝቃዛ ቢራዬን እየተጎነጨሁ ሙዚቃ እየሰማሁ በዓይኔ መቃኘት ጀመርኩ። ሁሉም ይዝናናል። ጥንድ ጥንድ ሆነው የመጡት አፍ ለአፍ ገጥመው ያወራሉ። የእኔ ብጤው ብቸኛ ደግሞ ዓይኑ ይቃዣል። ብቸኛ የሆኑ ሴቶችም አድናቂና ተመልካች እንዳላቸው ለማወቅ ገልመጥ ገልመጥ እያሉ ያያሉ።

ትንሽ ከእኔ ራቅ ካለ ቦታ ላይ አንዲት ልጅ ላይ ደነገጥኩ። የማውቃት የማውቃት መሰለኝ። ብቻዋን ነው ቁጭ ያለችው። መልኳ የአበሻ መልክ መሆኑን አልተጠራጠርኩም። ቆንጆ ናት። የወይን ጠጅ መሰለኝ የያዘችው። እንደሌሎቹ ዓይኖቿ ብዙ አይቃዡም። ከመቀመጫዬ ተነሳሁና እሷ ወዳለችበት አካባቢ ሄድኩ። አካባቢዋ እንደደረስኩ ተያየን። የማይተዋወቅ አበሻ ከአበሻ ድንገት ሲተያይ እንደሚያደርገው ከአንገቴ ሰላም ለማለት ያህል ጎንበስ አልኩ።

ከእግር እስከ ራስ ፀጉሬ በዓይኗ ገረመመችኝና እሷም ሰላም እንደማለት አለች። የአበሻ መልክ ስላላት ብቻ የማውቃት መሰለኝ እንጂ ከዚህ በፊት አይቻት አላውቅም። ፈገግታ ያላጀበውን ሰላምታዋን ከሰጠችኝ በኋላ ፊቷን ዘወር አደረገች። ነገር ነገሩ መዝጋቷ ነው። ሁኔታዋ ቢያበሽቀኝም እልህ ያዘኝና ላናግራት ወሰንኩ። ምን ይቀራል?

"ሰላም" አልኳት ወደ እሷ ጠጋ ብዬ

"What?" አለችኝ።

"Sorry, I thought you were an Ethiopian" አልኩ። ሌላ፥ ብትሆንሳ?

"ምኔ ነው ኢትዮጵያዊ የሚመስለው?" አለችኝ በአማርኛ

"ሁለመናሽ! አትናትዮስ እባላለሁ" አልኳት

"ስምህን አልነበረም የጠየቅሁህ?" አለችኝ። በግልምጫ ቆረጠችኝ።

"ብቻሽን ነው እንዴ ያለሽው? join ባደርግሽ?" አልኳት።

"ምን ዓይነት ድርቅና ነው። ብሆን ባልሆን ምን አገባህ?" አለችና እንደመዝጋት ዓይነት ፊቷን ዞር አደረገች።

ዝም ብዬ ከፊት ለፊቷ ካለው ባዶ ወንበር ላይ ቁጭ አልኩ።

"ቁጭ አልክ እንዴ? ምን ዓይነት ጣጣ ነው። ቢሸሹአችሁ አይገባችሁም።" ብላ ምንቅር ብላ መጠጧን ይዛ ተነሳችና ወደ ባንኮኒው አካባቢ ሄደች። ብቻዬን ወንበሩ ላይ ቀረሁ። ብሽቅ አልኩ።

ሰው እየኝ አላየኝ ለማረጋገጥ ዞር ዞር ብዬ አየሁና ቀስ ብዬ ተነስቼ ወደ መቀመጫዬ ተመለስኩ። ጤነኛ አይደለችም ብዬ ገመትኩ።

"ቢሸሹአችሁ አይገባችሁም" ያለችው ሊገባኝ አልቻለም። ማንን ነው? እኔን ነው? የት የማውቃትን? እያልኩ ማሰላሰል ገባሁ። በአንድ በኩል እንዴት "እኔን እንዲህ ታመናጭቀኛለች?" እላለሁ። በሌላው በኩል ደግሞ "የማናት ቀውስ? ትቅራ!! ይኼኔ በአደገኛ ዕፅ የተበከለች ቀውስ ትሆናለች" እያልኩ ሳሰላስል ትንሽ ቆየሁ። የቢራ ጠርሙሴን እያየሁ በሁለት እጆቼ እያሻሸሁ ሳለ፤

"ይቅርታ አመናጭቄ ጥዬህ በመሄዴ" አለችኝ ያችው ልጅ ከተቀመጥኩበት ቦታ በመምጣት ቁልቁል እያየችኝ።
ቀና ብዬ ዝም ብዬ አየሁዋት። ብሽቀት ስለነበረብኝ ቃል አልተነፈስኩም። አውሬ መስላ ታየችኝ። ውበቷም ደግሞ አለ።

"ብሽቀት አለብኝ፤ አበሻ የሚባል ላለማየት ብዬ ነበር እዚህ የመጣሁት፣ እና ገና ከመምጣቴ በመጀመሪያ ያናገረኝ ሰው አበሻ በመሆኑ ተናድጄ ነው። ለማንኛውም ይቅርታህን እንደማትነፍገኝ እተማመናለሁ። ካላደረግህም የራስህ ጉዳይ" ብላ ልትሄድ ስትል፤

"ለምን ቁጭ አትይም?" አልኳት።

እንዴ አየት አድርጋኝ ቁጭ አለች። በእጆቿ አገጯን ደግፋ ታየኝ ጀመር።

"አበሻ ሆነሽ ምንድነው እንዲህ በአበሻ ላይ የምታማርሪው? ደግሞ አበሻን ሁሉ በጅምላ የሚያስጠላሽና የሚያሸሽሽ ጉዳይ ምን ይሆን?" አልኳት።

"ምቀኞች፣ ተንኮለኞች፣ ዋሾዎች፣ ጉረኞች፣ ስንቱን ልቁጠርለህ፤ ስለሆናችሁ ነው" አለች። ዓይኗን እያጉረጠረጠች ስትናገር ብሽቀት እንዳለባት ያስታውቃል። ዓይኗ ግን ደስ ይላል።

"አንቺ ምን ሆነሽ? አሜሪካ መኖር አበሻነትን ያዘነጋል እንዴ? አልኳት። ውስጤ ግን እንደበሸቀ ቢሆንም ደም ግባቷ አንድ መልዕክት እንዳለው ደግሞ ቀደም ብዬ ነግሬአችሁዋለሁ።

"ወድጄ አይምሰልህ እንዲህ ለማለትና ለመወሰን የበቃሁት። ብዙ ነገር ደርሶብኛል። የራሴን ወገን ለመጥላት ፈልጌ ወይ ደግሞ እንደፈረንጆቹ ልሁን ብዬ አይምሰልህ። ከደረሰብኝ ታሪክ ተነስቼ ነው። እንዲህም ልበል እንጂ "የገዛ ጣት ገማ ተብሎ እንደማይቆረጥ" ሁሉ ሆዴ አልችል ይለኛል። ስለዚህም ነው አሁን ተመልሼ የመጣሁትና ይቅርታ ልልህ የፈለግሁት" አለችኝ ቅሬታ በፊቷ ላይ ይታይ ጀመር።

ምን አድርገዋት ይሆን? ታሪኩን ለማወቅ የሚያጓጓ ሆነብኝ ደግሜ ስሜን ነገርኳት።

"አሰገደች ነው ስሜ" አለች።

"ልትነግሪኝ ፈቃደኛ ነሽ ወይ?" አልኳት

"ምኑን?" አለችኝ

"ደረሰብኝ ያልሽውን ነገር?"

"ምን ያደርግልሃል?"

"እንዳው ለማወቅ፣ ለአንቺም ቢሆን እኮ አዕምሮሽን የሚያብሰለስል ነገር ካለ ስትናገሪውና ለሰው ስታካፍዪው ይቀልሻል፤ አይመስልሽም?" አልኳት።

"ለማን ነው የማወራው? ያውም ለአበሻ? አብደሃል መሰለኝ። ምስጢር ብለህ የምታካፍለውን ችግር መተረቻ፣ ስም ማጥፊያ ነው የሚያደርጉት፤ ጥሩ ጓደኛ አገኘሁ ብዬ ያወጣሁት ሰው ሄዶ ለጎደኞቹ እንዲህ አደረግኩዋት፣ እንዲህ አለችኝ እያለ አልጋ ላይ የተሰራውን ሳይቀር ያወራል። ጉራ ይሁን ምን አይገባኝም።

"በእኔ በኩል አትስጊ።"

"አንተን ከሌሎች ልይህ አልችልም። ሁሉም መጀመሪያ ሲተዋወቅህ እንዲሁ ነው የሚለው። ትንሽ ሲቆይ ነው ጭቃ ጅራፉ የሚመጣው፣"
አሰገደች የደረሰባትን ችግር ሁሉ የዚያን ዕለት እንድትነግረኝ ፈልጌ እንኳ አልነበረም ትንሽ የጨቀጨቅኋት። በአንድ በኩል ለመተዋወቅ መፈለግም አለ። በሌላ በኩል ደግሞ እንዲህ ያሰኛትን ነገር ምክንያቱን ለማወቅ መጓጓትም አለ። ምናልባት ይህ እሷ አበሻን እንድትጠላ ያደረጋት የአበሻ ባህርይ በእኔ ላይ ኖሮ ይሆን እኔ የምትስማማኝና የምትወደኝ ሚስት ለማግኘት ያልቻልኩት? ይህንንም ማሰብ አለ። በዚያን ምሽት ሁሉን ለማወቅ ሳይሆን ልተዋወቃት ጓጓሁ።

"ፈቃድሽ ከሆነ ስልክሽን ብትሰጪኝ" አልኳት።

ለጥቂት ደቂቃዎች ዝም ብላ አየችኝና "ትንሽ ሥነሥርዓት ያለህ ትምሰላልህ? ለምንድነው ስልኬን የምሰጥህ? አበሻ እንደሆን አልወድም ብዬሃለሁ።"

"ምናልባት እኔ ደግሞ አበሻ የሚጠላ ሰው መተዋወቅ ፈልጌ እንደሆነስ?" አልኳት እንደመሳቅም እንደመቀለድም ብዬ። ብዙ ጊዜ እንኳ ደፈር የምል አልነበርኩም።

ስልክ ተቀያየርንና ትንሽ ተጨዋውተን ተለያየን። እሷ አበሻ ያስመረራት፤ እኔ ደግሞ የአበሻ ሚስት ያለህ የምል፤ እግዚአብሔር ተገናኙ ብሎን ይሆን ብዬ አሰብኩ።

ብዙ ሳልሰነብት ደወልኩላት። ቡና እየጠጣን ለማውራት ቀጠሮ ተሰጣጣን። በቀጠሮው ዕለት ቀደም ብዬ ከቀጠረችኝ ቦታ ተገኘሁ። መጣች። ከዚያም ቡናችንን ይዘን ወሬያችንን ቀጠልን።

"የዚያን ዕለት ሳትታዘበኝ አልቀረህም። መቸስ ስከራ ነው ብለህ አስበህም ይሆናል?" አለች በፈገግታ።

"እንደዚያ እንኳ አላሰብኩም።" አልኳት።

"የደረሰብኝን ታሪክ ሁሉ ባጫውትህ አትፈርድብኝም። ከእኔ የበለጠ አበሻን የሚወድ አልነበረም። ስለዚህም ለአበሻ ጥሩና ግልፅ ለመሆን በጣርኩ ቁጥር እንደሞኝና ቂል እያዩ ሁሉም ተጫወቱብኝ፤ ከዚያ በኋላ ነው እርግፍ አድርጌ ለመተው የወሰንኩት" አለች።

"ቦይ ፍሬንድ ወይስ ጓደኛ?" አልኩና ችግር የገጠማት ከየትኛው እንደሆነ ለማወቅ ጠየቅሁ። ይገርማችኋል ይህን ለማወቅ የፈለግሁበትን ምክንያት ይህ ነው ብዬ ልገልፅላችሁ ይቸግረኛል። የአሰገደችን ሁኔታ ለማወቅ ግን በጣም ጓጓሁ።

"ቦይ ፍሬንድ ብትል፣ ጓደኛ ብትል፣ ዘመድም ቢሆን ሁሉም ያው ናቸው። መመቀኛነት፣ እንዱ በአንዱ ወሬ መንዛት፣ ተንኮል መፈፀም፣ በማያውቁት ነገር ሁሉ አዋቂ መስሎ ለመታየት መሞከር፣ ብቻ ምናለፋህ በቅርቤ የኖሩትም ሆኑ ከጊዜ በኋላ ያወቅኋቸው ሁሉም ያው ናቸው፣" አለችና ታሪኳን አጫወተችኝ።

ከአገር ቤት ከወጣች ወደ አስር ዓመት እንደሆናት፣ የመጣችው ለትምህርት እንደነበረና እዚህ ስትመጣ ሁሉ ነገር እንደጠበቀችው ሳይሆን ቀርቶ ያን የምትወደውን ትምህርቷን መቀጠል እንዳልቻለች፣ መጀመሪያ ያረፈችበት የአጎቷ ልጅ ጋር ሳትስማማ ቀርታ እንደወጣች፣ ስራ ለማግኘት ብዙ ችግር እንደገጠማት፣ ከዚያም እስቴት ቀይራ ወደዚህ እንደመጣች ሰፋ አድርጋ ታሪኳን ነገረችኝ። እዚህም እስቴት የመጣችው አንድ ድሮ አገር ቤት ታውቀው የነበረው ቦይ ፍሬንዷ ጋ እንደነበረና እሱም ጋ ቁምስቅሏን አይታ እንደወጣች አጫወተችኝ።

"ይህን ሁሉ ታሪኬን ለምን ዝክዝክ አድርጌ እንደምነግርህ ታውቃለህ?" አለችኝ ድንገት አቋርጣ።

"እኔ ስለጠየቅሁሽ?" አልኩኝ አፌ እንዳመጣልኝ።

"አይምሰልህ! ስለጠየቅኸኝ አይደለም። አየህ እህ ብሎ የሚሰማህ ስታገኝ የደረሰብህን ሁሉ ስትናገር ጭንቀትህ ይቀልልሃል። በሌላ በኩል ደግሞ አንተን ሳይህ አስተዋይና ወሬኛ የሆንክ አልመሰልከኝም። ለዚህ ነው። አንዳንዱ አበሻ ታሪክህን ስትነግረው ዞር ብሎ ያማሃል። አንተ ግን ጭምት መሰልከኝ። አይደለህም እንዴ?" አለችኝ።

"ስለ ራሴ እንዲህ ነኝ ብዬ ማውራት ይቸግረኛል። በእርግጥ ወሬ አልወድም።" አልኳት።

"እሱን ብዬ እስቴት ለቅቄ የመጣሁለት ቦይ ፍሬንዴ ጋ ሁለት ዓመት ኖርኩ። መጀመሪያ እንደመጣሁ ወረት ሆኖበትም ይሁን ሌላ በደምብ ነበር የሚያስብልኝ። አንድ ስድስት ወር አብረን እንደኖርን የመሰላቸት ባህርይ እያሳየኝ መጣ። ድሮ የማውቀው የምወደው ሰው በመሆኑ ቻልኩት። የመጣሁ ሰሞን በጊዜ እቤት ይገባል። ኋላ ማመሻሸት ጀመረ። ሲል ሲል እየሰከረ እየመጣ ይረብሸኝ ጀመር። ይተዋል እያልኩ ታገስኩት፣ የማሳየውን ፍቅርና ጥሩ ጠባይ መቀበል አልቻለም። ሲወጣ ሲገባ ይነጫነጫል፣ ይቆጣል። ቁምነገር ወዳለው ግኑኝነት ተሻግረን እንድንጋባ ስለምፈልግ አስብለትና እሳሳለት ስለነበር ለምን እየተለወጠ እንደመጣ ለማወቅ አልቻልኩም።

ጓደኞች ያበዛል። ሲጠጣ የሚያመሸውም ከእነሱ ጋር እንደሆነ ስለማውቅ አንድ ቀን ረጋ ብዬ ነገርኩት። ዱላ ቀረሽ ስድብ አወረደብኝ። ጓደኞቼን ለቀቅ አድርጊ አለኝ። እኔ ከጓደኞቹ ጠብ የለኝም። አልፎ አልፎ እቤት ሲመጡ ጥቂት ከማናገር በቀር ብዙ አላውቃቸውም። የሚያወሩት ነገር ስለማይጥመኝ አልቀርባቸውም። ቁምነገር ባለው መንገድ ለእሱ የሚበጀውን በመንገር የመከርኩትም የትዳር ጎደኛዬ ይሆናል ብዬ የምወደውና የማስብለት በመሆኔ ነበር እንጂ እኔ እሱን ከጎደኞቹ

ለማለያየት አልነበረም። እኔን ተቆጥቶ ብቻ ቢቀር ጥሩ ነበር። እሱ ግን ሄዶ አትወዳችሁም ይበላቸው ምን አልገባኝም ጥምድ አድርገው ያዙኝ። ጭራሽ አንደኛው "አንቺ ለመሆኑ ምን ሆንሽና ነው ይህን ያህል የሚያንጠባርርሽ? ከነበርሽበት እስቴት ለምን ወደዚህ እንደመጣሽ ደግሞ የማናውቅ መሰለሽ? ስላንቺ ብዙ ሰምተናል። ጓደኞችን ድሮ ስለሚያውቅሽ ነው እንጂ ይህን ያህል እሱን control ልታደርጊ የሚገባሽ አይደለሽም . . ." ምን ልንገርህ ወረደብኝ። አለቀስኩ። ምንም መልስ ልሰጠው አልቻልኩም። ከዚያ በኋላ ከቦይፍሬንዴ ጋር አብረን ብንኖርም እየተራራቀን መጣን። ሲፈልግ እያደረ፣ ሲያሰኘው እየከረመ መምጣት ጀመረ። ቃል ሳንለዋወጥ ሁለትና ሶስት ቀን መቆየት መጣ። ቤቱን ለቅቄለት እንዳልወጣ የኑሮውን ችግር ታውቀዋለህ። ብቻዬን ቤት ተከራይቼ መኖር አቅሙም አልነበረኝም። ይህ በዚህ እንዳለ አንድ ቀን አንደኛው ጓደኛው ያለሁበትን ጊዜ ጠብቆ ይመጣል። ለምን እንደመጣ ብነግርህ አታምንም። የቅርብ ጓደኛው እኮ ነው። 'እሱ አይወድሽም፣ ሊነግርሽ ፈርቶ ነው እንጂ ቤቱንም ለቀሽ እንድትወጪለት ይፈልጋል። በጣም ነው ያሳዘንሽኝ። አለና መጀመሪያ ካየሁሽ ጀምሮ በጣም ደስ ትይኛለሽ' አይለኝም መሰለህ። ደነገጥኩ። የነበርኩበት ሁኔታ ይታይህ። ቦይ ፍሬንዴ ከሌላ ሴት ጋር እንደሚወጣ ነገረኝ። የልጅቷንም ስም ጨምሮ። ምንም አላልኩ። ዝም አልኩ፤ በመጨረሻም እንዲሄድልኝ ለመንኩት ሌላ ጊዜ መልሱን እንግርሃለሁ፣ ላስብበት አልኩትና ሄደ።"

አስገደች ይህን ታሪክ በምትነግረኝ ጊዜ በጣም ታሳዝን ነበር። በአነጋገሯና እንዲሁም በደረሰባት ነገር ሁሉ ምን ያህል ምሬት እንዳለባት ለመረዳት አላዳገተኝም። ለጥቂት ደቂቃ ፀጥ ብላ ከተከዘች በኋላ ታሪኳን ቀጠለች።

"በጣም የቅርብ ጓደኛው እንዲህ ካለኝ ብሎም ላውጣሽ ብሎ ከጠየቀኝ እንግዲህ ምን ቀረኝ? ጓደኛሞች ሊፈራረቁብኝ እንደተዶለተብኝ ዓይነት አድርጌ አየሁት። አንዱ ብሎት ብሎት ሲበቃው ለሌላው Recommend ያደረገኝ ዓይነት።

እዚህ ሁኔታ ላይ ብደርስ ውጤት ለሌለው ነገር ከቦይ ፍሬንዴ ጋር መጨቃጨቁ አልታየኝም። ዝም አልኩና ከዚያ ቤት መውጫ መንገዴን መፈለግ ጀመርኩ። ጓደኛውም ደጋግሞ ደወለ። ተንኮል ሊሰራብኝ ካሰበ እኔስ ለምን አልጠቀምበትም ብዬ አስቤ ነበር። እግዜር የማይወደውን ነገር መስራት መጥፎነቱ ግልፅ ሆኖ ታየኝ። በተጨማሪም ራሴን ዕቃ ማድረግ እንጂ ጥቅሙ አልታይ አለኝ። እንግዲህ ይታይህ የአበሻን ጠባይ" አለችና ተከዘች። "ብዙ ለፈለፍኩብህ አይደል?" አለችኝ።

"በጣም አሳዘንሽኝ። የደረሰብሽ ታሪክ በጣም ያሳዝናል። ከዚያ በኋላ በቃ ወጣሽ አይደል?" አልኳት የታሪኳን መጨረሻ ለመስማት ጎጉቼ።

"ይህ ድርጊት በሆነ በወሩ ቤቱን ለቅቄ ወጣሁ። የገባሁበት ቤት ድረስ ቦይ ፍሬንዴ እኔን ፍለጋ መጣ። ነገሩ ይቅርታ ሊለኝ ነበር። የመጨረሻውን ቁርጡን ነገርኩት። ቆየት ብሎ ደግሞ ጓደኛው መጣ። ሙልጭ አድርጌ ሰድቤ አበረርኩት። ከዚያ በኋላ አበሻ አስጠላኝ።" አለችኝ።

በእርግጥ በጣም የሚያስመርር ሁኔታ ገጥሟታል። አበሻ ሁሉ እንደዚህ ዓይነት ባህርይ እንደሌለው እንድታውቅ ማድረግ አለብኝ ብዬ ወሰንኩ። ደግሞም ግልፅነቷ ሳበኝ። እንዳው ልቤም ፈቀዳት። ለደረሰባት የመንፈስ ሕመም ሐኪሟ እንድሆን ዕድሉን እንድትሰጥ ልጠይቃት ፈለግሁ። እየፈራሁ እየተባሁ ጠየቅሁዋት። እሺታም ይሁን እምቢታ ብቻ ትክ ብላ አየችኝ።

(ይቀጥላል)


## ውድ የላንዳፍታ አንባብያን

መጽሄታችንን የበለጠ ለማሳደግ፡ ጥራቱን ለመጠበቅ አንባብያን ደምበኛ እንዲሆንዋት እንጋብዞታለን። ይህኛውን መጽሄት ተውሰው ከሆነ ያነበቡት የሚቀጥለውን እትም ይገዛሉ ወይም ደምበኛ ይሆኑናል ብለን እናምናለን።

መጽሄቷ ደግሞ የበለጠ ልታድግ የምትችለው ለዝግጅቷ የሚወጣውን ወጪ መሸፈን ስትችል ነው። በአገርዎ ቋንቋ በሰው አገር የምትታተመው መጽሄት ማደጓን እርሶም ይፈልጋሉ በሚል እምነት ነው።

የደምበኝነት ቅጽ ገጽ 48 ላይ ይገኛል።

# የቦክስ መድረክ
# የቦክሰኞች ሪንግ - የትግል መድረክ

(ከሰይፉ መኩሪያ - ከአትላንታ)

ሁለት ወንዶችን የእጅ ጓንት በመስጠት የድብድብ ትርዒት እንዲያሳዩና አሸናፊው እንዲታወቅ የሚደረግበት የቦክስ ስፖርት ነው። ይህ ለህብታሙ ክፍል የመዝናኛና በተለይም ደግሞ የገንዘብ ውርርድ ማካሄጃ በመሆን የተጀመረ ስፖርት ነበር። ለተሷቋሾች በሚወስነው የገንዘብ ሽልማት ሳቢያ የቦክስ ሪንግ ድህነትን ማምለጫ መድረክም ነበር። ይህ የቦክስ ታሪክ በአሁኑ ዘመንም ያልተለወጠ መሰረታዊ ሀቅ ሆኖ ይገኛል። ሆኖም የቦክስ ሪንግ ቀስ በቀስ የትግል መድረክ (ማለትም የፖለቲካ ትግል መድረክ) መሆን የጀመረው ጥቁር ቦክሰኞች መድረኩን መርገጥ ከጀመሩ በኋላ ነበር።

## ከጃክ ጃንሰን - እስከ መሐመድ አሊ የቦክሰኞች ትግል

የመጀመሪያዎቹ ጥቁር ቦክሰኞች ባርያዎች ወይም ከባርነት በቅርብ ነፃ የወጡ ሰዎች ነበሩ። ፈረስ ለግልቢያ እንደሚያሰለጥኑ ሁሉ እነዚህን በቅርብ ከባርነት ነፃ የወጡት ሰዎች በቀድሞ ጌቶቻቸው ስር የቦክስ ስልጠና እየተሰጣቸው ከባርነት የኢኮኖሚ ሥርዓት ወጥተው ገንዘብና ትርፍን ብቻ ሊያጧጥፉ ወደሚያመቻቸው ወደ ካፒታሊስት የኢኮኖሚ ስርዓት አንድ አካል መሆን ጀመሩ። ልክ እንደዛሬው ያኔም ቦክስ የገንዘብ ማግኛ መንገድ ብቻ ሳይሆን ግላዊ ነፃነት/መብትን ማስከበሪያ መድረክም ነበር። ይህን በመሰለው ታሪካዊ ሂደት የቦክስ ስፖርት በጥቁሮች መሃል ልዩ የሆነ ቦታ እስካሁን ድረስ ይዞ ይገኛል። የመጀመሪያው ጥቁር (Heavy weight) ሻምፒዮን ጃክ ጆንሰን ይባላል። ከእርሱ በፊት ከጥቁር ጋር አልገጥምም ይል የነበረው ፈረንጅ ቦክሰኛ ጂም ጀፍረስ ሻምፒዮን ነበር። በ1908 ዓ/ም ሲድኒ አውስትራሊያ ውስጥ በተካሄደው ግጥሚያ (ግጥሚያውን ለማካሄድ ፈቃደኛ የሆነ የአሜሪካ ከተማ ስላልተገኘ) ጥቁሩ ጆንሰን በማያወላውል መንገድ ነጩን ሻምፒዮና ሲያሸንፍ በጥቁሮች አካባቢ ታላቅ ደስታና ፌንጠዝያ ሆነ። በማከታተልም የነጭ ጋንግስተሮች በዚህ የስፖርት ውጤት በመብሸቃቸው የተነሳ በየከተማው እየተዘዋወሩ በጥቁሮች ላይ የዘረኝነት ዱላና ጭፍጨፋ አካሄዱ። ሪንግ ውስጥ ሆኖ ነጭ ቦክሰኞችን ሲደበድብ ፊቱ ላይ የፈገግታ ምልክት እያሳየ ከመሆኑም በላይ ፈረንጅ ሴቶችን በየሄደበት የሚያሽኮረምም ቦክሰኛ በመሆኑ ጃክ ጆንሰን በነጮች አካባቢ የተጠላ ሻምፒዮን ነበር። ኒውዮርክ ያትምስ "ዘሩን አሰዳቢ" ቦክሰኛ ነው ማለት በጋዜጣ አውጥቶ ነበር። ወዲያው የአሜሪካው መንግስት (The Federal Govt.) በማከታተል ጃክ ጆንሰንን በ"ግብረገብ ጉድለት"(Moral Conviction) ለመክሰስ ሲዘጋጅ ጃክ ጆንሰን አገሩን ጥሎ ይሰደዳል። ከሶስት ዓመት በኋላ በ1915 ዓ/ም ሞራሉ የወደቀውና ከአገሩ በስደት የተፈናቀለው ጃክ ጆንሰን ሀቫና-ኩባ ውስጥ ጄሲ ዊላርድ ለሚባል 'የነጭ ተስፋ' (White Hope) ቦክሰኞች ሻምፒዮናነቱን በሃያ ስባተኛው! ራውንድ አስረከበ። ጃክ ጆንሰን ሻምፒዮናነቱን ካስረከበ በኋላ የከባድ ሚዛን የሻምፒዮና ግጥሚያ ለሃያ አምስት ዓመታት ለጥቁሮች የተከለከለ መድረክ ሆኖ ቆየ። ከዛ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ብቅ ያለው ጥቁር ቦክሰኛ ጆ ሊዊስ ነበር። የጆ ሊውስ አሰልጣኞች (የዲትሮት ጥቁሮች ነበሩ) የጃክ ጆንሰን ሁኔታ በቦክሰኛው ላይ እንዳይደገም በመፍራት ብዙ ጥንቃቄዎች በማድረግ ነበር ጆ ሊውስን የሚያሰለጥኑት። የጠረጴዛ ወግና (Table Manner)፣ የአነጋገር ስልትን፣ ከማስተማራቸውም በላይ ጆ ሊውስ አሸናፊ ለመሆን ማለትም የዘረኞች ዳኞችን አድልዎ ያለ ጥርጥር ማሸነፍ ከፈለገ ያለው አማራጭ ተጋጣሚውን ዘርሮ መጣል ብቻ መሆኑንም በመወትወት ያስተምሩት ነበር። በተጨማሪም ፈረንጁን ተጋጣሚ በሚደበድብበት ሰዓት ፈገግታ እንዳያሳይና በተቻለ መጠን ከነጭ ሴት ጋር እንዳይታይ ይመክሩትም ነበር። ጆ ሊውስ ለጥቁር አሜሪካኖች አርአያ (Role Model) እንዲሆን የታጨና የሰለጠነ ቦክሰኛ ሆኖ ቀረበ። ጆ ሊውስ የከባድ ሚዛን ሻምፒዮና ግጥሚያውን ያካሄደው በ1935 ዓ/ም ነበር። በዛን ወቅት የነበረው ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ ቤኒቶ ሙሶሎኒ ኢትዮጵያን ለመውረር የሚያደርገው የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ የነጮችና የጥቁሮችን ዓለሞች በማካረር ላይ ነበር። ጥቁሩ ጆ ሊውስ የሚጋጠመው ፕሪሞ ካርኔራ የሚባል የጣልያን ዝርያ ከነበረው ቦክሰኛ ጋር በመሆኑ የሁለቱ ግጥሚያ በጥቁር ኢትዮጵያ ላይ ፋሽስት ጣሊያን ከምትዘጋጅበት የወረራ ጦርነት ጋር ተዛምዶ መታየት ጀመረ። በዚህ ሳቢያ የቦክሱ ግጥሚያ በተመልካቹ መሃል ድብድብና ግድያ ሊያስከትል ይችላል ተብሎ በመገመቱ ግጥሚያው ከመጀመሩ በፊት ብዙ ማሳሰቢያና ማስጠንቀቂያዎች እንዲነገሩ ተደርጎ ነበር። በዚህ በኒውዮርክ ከተማ ውስጥ በተካሄደው ግጥሚያ፣ በአሜሪካኑ ማፍያ ይደገፍ የነበረው ፕሪሞ ካርኔራ በስድስተኛው ዙር ላይ በጆ ሊውስ ምት ተዘርሮ በመውደቁ፣ ጆ ሊውስ የሻምፒዮናው ባለቤት እንዲሆን አበቃው። ከአንድ ዓመት በኋላ ማለትም 1936 ዓ/ም የጀርመን ናዚዎች 'የነጭ ዘር የበላይነት' ምልክት በማለት የለፈፉበት አንድ ግጥሚያ ላይ ማክስ ሽሜሊንግ (Max Schmeling) . . .

(ወደ ገጽ 35 ይዞራል)

# አዳም ና ሔዋን

አዳምና ሄዋን የተሰኘው አምዳችን የሚያተኩረው በተቃራኒ ጾታዎች መሃል በሚኖረው ግንኙነት ላይ ነው። የገጠመኝ ታሪኮችና አስተያየቶች የመሳሰሉት ይቀርባሉ– በእውነተኛ ገጠመኝ ላይ የተመሠረቱ የፍቅር ታሪኮችንም እናቀርባለን። አምዱን የመወያያና የመማሪያ አምድ ለማድረግ እንዲቻል አንባብያን አስተዋጽዖአችሁን እንጠይቃለን። በአምዱ ላይ በተለይ ካልተጠቀሰ በስተቀር የሚቀርቡ አስተያየቶችም ሆነ የገጠመኝ ታሪኮች አንባብያን የሚልኩል መሆኑ ይታወቅልን።

## ዕጣዬ

### ከአብርኽት

"ዕጣዬ" በተሰኘ ርዕስ አብርኽት (የብዕር ስሟ ነው) በስደት ኑሮዋ የገጠማትን በተከታታይ እያቀረበችልን ነው። ይህን አሳዛኝ የፍቅርና የስደት ታሪክ ለአንባብያን ስናቀርብ አቀራረቡን እንዲጥም ከማድረግ በቀር በታሪኳ ላይ የጨመርነው ሆነ የቀነስነው ነገር የለም። እሷ በአሁኑ ወቅት በአሜሪካ አገር በስደት ላይ ናት።

### ክፍል 10

የተዋወቅናቸው ፋሲካና አጥናፉ ያለንበትን ሁኔታ ከተረዱልን በኋላ በመጀመሪያ እንዴት ከዚህ ሰውዬ ቤት እንደምንወጣ በኋላም እንዴት ካርቱም መሄድ እንደምንችል ዘዴ ዘዴውን መከሩን። በሃሳቡ ከተስማማን እነሱ ሊረዱን እንደሚችሉ ቃል ገቡልን።

አላመነታንም፣ አልተጠራጠርንም። በነገሩን መሰረት እነሱ ረዱንና ከቀጣሪያችን ነጋዴ ቤት ጠፍተን እዚያው ገዳሪፍ ለአንድ ሁለት ሳምንት ተደብቀን ቆየን። ፋሲካ የመቆያ ቦታችንን አሞቻችቶልን ስለነበር አልቸገረንም። ከአንድ ሁለት ሳምንት በኋላ ካርቱም ካሉት ጓደኞቹ ጋ ልናርፍ እንደምንችል እነሱም እንደሚቀበሉን ነገረን። ጊዜ አልፈጀንም። በጉቦ መታወቂያ ወረቀት ወጥቶልን ወደ ካርቱም ሄድን። ያለመታወቂያ ወረቀት መንቀሳቀስ አይቻልም። ካርቱምም እንደገባን ጅሬፍ ሻጣ ከሚባል አካባቢ ካሉ ከነፋሲካ ጓደኞች ቤት ሰፈርን። በጥሩ ሁኔታ ተቀበሉን። አንድ ሁለት ቀን እንደቆየን የቤት ሰራተኛነት ስራ ተገኝቶልን ተቀጠርን። የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ጽ/ቤትም ሄደን አመለከትን፤ ተመዘገብን። በተሰጠን ምርጫ ሁለታችንም አሜሪካ መሄድ እንፈልጋለን ብለን ገለፅን። የራሱን Sponsor (ኃላፊ) ማግኘት ለሚችል ሰው ጉዳዩ ይቀላል የሚል ወሬ ስለሰማንና እኔም እህቴ አሜሪካ ስለምትኖር ይቀለናል ብዬ እስፖንሰር ራሳችን እንደምናገኝ ገለፅን።

አሜሪካን አገር ላለችው ታናሽ እህቴ ወዲያውኑ ፃፍኩኝ። ለእኔም ለሰይፍዬም እስፖንሰር እንድትፈልግ ነበር ዋናው ጥያቄዬ። ከዚያም በአቅራቢያዬ የሚገኝ የስልክ ቁጥር ላኩላት። በ2ኛው ወር ገደማ ደብዳቤዋ ደረሰኝ። ለሁለት ሰው በአንድ ጊዜ እስፖንሰር ማግኘት እንደሚያስቸግርና ለእኔ ግን ተስፋ እንዳገኘች የሚገልጽ ደብዳቤ ነበር።

ለፍቅሩ ፍቅሬን ጥዬ የመሄድ አንጀት ስላልነበረኝ ይህንኑ ለሰይፉ ገለጽኩና የሁለታችን ካልሆነ ለብቻዬ አልመጣም ብዬ ለመፃፍ ስዘጋጅ ሰይፉ አይሆንም ብሎ ከለከለኝ። "አንቺ ቀድመሽ ሂጂና እኔ ደግሞ እከተላለሁ" አለኝ። ከብዙ ምክክር በኋላ በዚሁ ተስማማን። እኔ ቀድሜ ልሄድ፣ እሱ ደግሞ እኔ ሄጄ ሁኔታውን አመቻችቼ ሊመጣ።

ከዚያ በኋላ እስፖንሰር የመገኘቱ ጉዳይ ተሳካና ይኸንኑ የሚገልፅልን መረጃ በእህቴ ተልኮ ካርቱም በገባሁ በ8ኛው ወር ገደማ እኔ ወደ አሜሪካ የመምጣቴ ሁኔታ ተሳካ። ከእህቴም ጋር በስልክ ተደዋወልን። ተነጋገርን። እኔም በጣም የምወደውን ሰይፍዬን ተለይቼ አሜሪካ ለመብረር ተዘጋጀሁ። የእኔ ፕሮሰስ 8 ወር የፈጀ እኔ ከሄድኩ በኋላ ሁኔታውን የበለጠ አጣድፌ ሰይፍዬን ስድስት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ እንደማላውጣው ሙሉ በሙሉ ተስፋ አድርጌ ነበር።

የሱዳን ኑሮአችን አከተመ እንዳልል ሰይፉ ከእኔ ተለይቶ ሊቀር ነው። ለረዥም ጊዜ ያልተለየኝ የምወደው ሰይፍዬ፣ ለደቂቃ ልለየው የማልፈልገውን ሰይፍዬን ወደ ኋላ ትቼ እኔ ቀድሜ ወደ አሜሪካ ስሄድ የሚሰማኝን ትረዳላችሁ። ስለዚህም ግማሽ ኑሮዬ ግማሽ እኔ እዚሁ ካርቱም ሲቀር ግማሹ እኔ ነበር በአይሮፕላን ሊሳፈር የተዘጋጀው።

ወደ አሜሪካን አገር ቀደም ብላ ከአዲስ አበባ የሄደችው ታናሽ እህቴ ጋ መሄድ የምችለው እኔ ብቻ ስለሆንኩ ነው እንጂ ሰይፉን ጥዬ መሄድ ፈልጌ አልነበረም። እህቴ ደግሞ እስፖንሰር (ኃላፊ) ማግኘት የቻለችው ለእኔ ብቻ ነበር። ከሰይፉ ጋር የተስማማንበት እኔ እንደሄድኩ ሁሉን ነገር ለእሱ ጨርሼ እሱ ደግሞ የሚመጣበትን መንገድ ለማመቻቸት ነበር። እኔ እኳ ጠብቀን አንድ ላይ የምንሄድበትን መንገድ እናመቻች የሚል ነበር ሃሳቤ። ሰይፉ ግን ይህን ዕድል እንድናበላሽ አልፈለገም።

ወደ አሜሪካን ለመምጣት ሁለት ቀን ሲቀረኝ ጀምሮ ሆዴን ባር ባር አለው። ከሰይፉ መለየቴና

ከለመድኩበት ቦታ ወደ አዲስ ቦታ መሄዴ፣ ሆዴን ቡጭ ቡጭ ያደርገው ነበር። ይህን ያህል በሱዳን የስደት ኑሮ ያልተለየኝ ሰይፉ ዛሬ እኔ ጥዬው ስሄድ ምን ይሰማው ይሆን እያልኩ አስብ ጀመር። አስብ አስብና ደግሞ ወደፊት እሱም መጥቶ ተገናኝተን፣ ተጋብተን፣ ኑሮአችንን በአሜሪካ አገር ስንገፋው ይታየኝና እጽናናለሁ። ብዙ የሚወራላት፣ ብዙ የተነገረላት፣ ብዙ የተባለላት አሜሪካ ለመምጣት ምን ያህል እንደሚያጓጓ ታውቁታላችሁ። ስለ እሱ ብዙ አላወራም። በሰለጠነች፣ በቴክኖሎጂ የተስፋፋች ለሁሉም የሆነች ብርቋ አሜሪካ ለመምጣት ማን የማይፈልግ አለ? ቀደም ብለው ዕድላቸው ተሳክቶ ወደ አሜሪካ የመጡት ኑሮአቸው ሌላ መሆኑ ሲሰማ ማን ወደዚያ ለመሄድ የማይጓጓ አለ? እነበላይ፣ እነረጋሣ፣ እነተንሳይ፣ እነ ተክሌ፣ እነ ትብለፅ ዛሬ በአሜሪካ ጎዳናዎች ላይ የሚያሽከረክሯቸው መኪናዎች፣ የሚኖሩበት ቤት፣ የሚያደርጉት ነገር ሁሉ ሌላ ነው ይባላል። አገሬም እያለሁ እዚህም ሱዳን እያለሁ ለጓደኞቻቸውና ለዘመዶቻቸው የሚላኩትን ደስ ደስ የሚሉ ከለር ፎቶዎች አይቶ ማነው እንደዚያ መሆን የማይፈልግ? እና እንግዲህ ስደተኛው ሁሉ ልቡ የቆመው አሜሪካ ነውና እኔም ኋላ ደግሞ ሰይፉ ተጨምሮ አሜሪካ ገብተን እንደዚህ ያለ ሕይወት ለመኖር ስሜታችን ከፍ ያለ ነበር።

ደግዋ አሜሪካ ሆዬ፣ ስደተኞችን ኃላፊ የሚሆናችው ሰው እስካገኙ ድረስ ወደ አገሯ ገብተው ያለ ምንም ችግር የኑሮና የስራ ፈቃድ ሰጥታ እንደምታስተናግድ አረጋገጠችልኝ። ታዲያ አሜሪካ የምትሰጠውን ዕድል በእኩልነት፣ አድሎ ባልተሞላበት መንገድ ስደተኞች እንድንጠቀምበት ችግር እየፈጠሩ ስደተኛውን የሚያጉላሉ አልጠፉም። ችግር ሲፈጠር ዘዴ መፈለግ ያለ ነውና በዘዴ በዘዴ መሰናከሎችን ሁሉ አስወግደን የእኔ ወደ አሜሪካ ቀድሞ የመምጣት ሁኔታ ተሳካ።

እንግዲህ ከሰይፉ መለየቴ ቅር ያሰኘኝ እንጂ እንዳልኳችሁ አሜሪካ በገባሁ ዓመት ባልሞላ ጉዜ ከእህቴም ተማክሬ ሰይፍዬን ለማስመጣት ነበር ትልቁ እቅዴ። እናም ከሰይፉ እምባ በእምባ ሆነን ተሰነባበትን። እኔም ታላቂቷ አሜሪካ መጣሁ። እህቴ አለችበት እስቴት።

ታናሽ እህቴ የምትኖረው ብዙ አንኳን ባይባል ጥቂት አበሾች ከሚኖሩባት ከተማ ነበር። እሷ ከመጣች ወደ ስድስት ዓመት ገደማ ስለሆናት አገሩን ደህና ተላምዳለች። አይሮፕላን ማረፊያ ልትቀበለኝ መጥታ መጀመሪያ ሳያት ገረመኝ። በጣም አምሮባት፣ ዘንጣ አገኘሁዋት። ናፍቆትም ነበርና በደስታ ተቀበለችኝ። ጉስቅል ማለቴን አይታ "ወየው የእናቴ ልጅ!" አለችኝ። ከዚያም በዘነጠ መኪና ይዛኝ እቤቷ ስታመጣኝ ደግሞ ሌላ ደስታ ተሰማኝ። ቤቷ ሌላ ነው፣ ሶፋው፣ ቲቪው፣ ቪዲዮው፣ የመኝታ ቤቷ፣ ለእኔ እንኳ የተዘጋጀው መኝታ ቤቱም ቢሆን ሌላ ነበር። እውነትም አሜሪካ መንግስተ ሰማያት ነው አልኩኝ። እህቴም ጓደኞቿ ሁሉ ሆነው በደምብ ደግሰው ነበር የተቀበሉኝ። ሳምንቱን ፈቃድ ወስዳ እህቴ በመጀመሪያ የወረቀቶቼን ጉዳይ ማስተካከል፣ በሌላው ጊዜ ደግሞ እያዞረች ድንቅ ድንቅ የሆኑ ቦታዎችን አስጎበኘችኝ። ምንም ታናሼ ብትሆን እሷ ቀደም ብላ የመጣችና ስለአገሩም ብዙ የምታውቅ በመሆኗ የምትለኝን፣ የምትሰጠኝን ምክር ሁሉ በጽሟና አዳምጥ ነበር።

ማታ ማታ እቤታችን ቁጭ ብለን ስላለፈው፣ ስለነበርኩበት ሁኔታ፣ ስለሰይፉ፣ ስለሱዳን ስደተኞች በሙሉ አጫወትኳት። በጨዋታዬ መሐል ስለሰይፉ ደጋግሜ በማንሳቴ በእኔና በእሱ መሐል ያለው ግኑኝነት ኮስተር ያለና እኔም በጣም የምወደውና የማስብለት መሆኑን የተረዳች ይመስለኛል። የእሱን ማስመጣት ጉዳይ ደግሞ የእኔ ችግር በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ የማነሳው ነገር ስላልመሰለኝ አላነሳሁባትም። መጀመሪያ የእኔ ጉዳይ መስመር መያዝ አለበት ተጨማሪ ሌላ ችግር አንስቼ የእናቴን ልጅ የሃሳብ ጭንቀት ውስጥ ልከታት አልፈለግሁምና አቆየሁት።

እና እንግዲህ የአሜሪካ ኑሮዬን ጀመርኩ። መቼም አገር እስኪለመድ ያለ ነገር ነውና ትንሽ ድንግርግር ይላል። ምንም ያለሁት እህቴ ቤት ቢሆንም የማደርገውን፣ የምለውን ነገር ሁሉ ለአገሩ እንግዳ ይሆን? በማለት እየፈራሁ ነበር የምፈፅመው። እህቴም በመጀመሪያ አካባቢ ናፍቆቱም ምኑም ስላለ የማደርጋቸውን አንዳንድ ለአገሩ እንግዳ የሆኑ ድርጊቶችን እንዳላየ ታልፈው ነበር። እሷም ከመጀመሪያው ሳምንት በኋላ ወደ ስራዋ የተመለሰች በመሆኗ እኔ ብቻዬን እቤት እውል ነበር። ከስራ ስትመጣ ምግብ ሰርቼ እጠብቃታለሁ። ራታችንን በልተን ትንሽ ዘወርወር እንልና ቤታችን እንገባለን። ሶስተኛውና አራተኛው ሳምንት እንዳለፈ ግራ እየገባኝ መጣ። እቤት ብቻ መዋሉ እየሰለቸኝ ሲመጣ ተሰማኝ። ደግሞ ብቸኛ ሲኮን መንፈስ በሃሳብ መረበሹ አይቀርምና የሰይፉ ሁኔታ ትዝ እያለኝ እረበሽ ጀመር። ለአምስት ዓመት ያልተለየሁት ሰይፉ የበለጠ ትዝ እያለኝ ተቸገርኩ። ቀደም ሲል እኔ ሱዳን እያለሁ እህቴ አንድ ሁለቴ ስልክ የደወለችልኝ ቦታ ሰይፉ በየቀኑ እየሄደ ደወለች ወይ እያለ እንደሚጠይቅ አውቅ ነበር። ምክንያቱም ተነጋግረናልና። እንደመጣሁ ደብዳቤ ፅፌለታለሁ። ይድረሰው አይድረሰው ማወቅ የምችለው እሱ ደርሶት መልስ ሲጽፍልኝ ብቻ ነው። ስልክ እንዳልደውል ደግሞ እህቴ ገና እንደመጣሁ የስልኩን ውድነት አስጠንቅቃኝ ነበርና ላነሳባት አልቻልኩም።

(በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል)

## የቦክስ መድረክ · (ከገጽ ፴፪ የዞረ)

የሚባለው ጀርመናዊ ቦክሰኛ ጆ ሊዊስን አሸንፎ ነበር። ከሁለት ዓመት በኋላ በያንኪ ስቴድዮም ውስጥ በሁለቱ መሀከል በተደረገው ድጋሚ ግጥሚያ (rematch) በስፖርት ታሪክ ውስጥ ትልቅ ምዕራፍ የያዘ ውድድር ሆነ። ጆ ሊውስ በሄደበት ሁሉ፣ በጋዜጣና በሬዲዮ የአሜሪካው ፕሬዚዳንት፣ የአሜሪካው ኮምኒስት ፓርቲ . . . ማለትም ፀረ ፋሽስት የሆኑ ኃይሎች ሁሉ ማክስ ሽሜሊንግን በኖክ አውት ማሸነፍ የዜግነት ግዴታው፣ የፀረ ፋሺስት ትግልና የጥቁር ህዝብ ኩራት እንደሚሆን ያለማቋረጥ ያሳስቡት ነበር። ከዚህም በላይ ጆ ሊውስ ልምምድ (Training Camp) በሚያካሂድበት ቦታ ድረስ በመምጣት የአሜሪካ ናዚዎች የተቃውሞ ሰልፍም አካሂደውበት ነበር። በእነዚህ ሁሉ ግፊቶች ተወጣጥሮ የነበረው ጥቁር አሜሪካዊው ቦክሰኛ ጆ ሊውስ የናዚ ተስፋ የነበረውን ማክስ ሽሜሊንግን በሁለት ደቂቃ ውስጥ ማለትም ገና በመጀመሪያ ዙር ላይ ዘርሮ በመጣል ድሉን ተቀዳጀ። ይህን ድል ይህንን የጥቁር ድል ጥቁሮች ያለአንዳች ፍራቻ በደስታና በትልቅ ዝግጅት በሙሉ ልብ ለማክበር ቻሉ። ይህ ድል የቦክስ ድል ብቻ ሳይሆን የናዚዎች "የነጭ የበላይነት" እምነት ፍርክስክሱ የወጣበት ድል መሆኑም ግልፅ ነበር።

ጆ ሊውስ አሜሪካ በተለይም ነጭ አሜሪካ የጠበቀችበትን ሁሉ ለማሟላት ጥረት ያደረገ ቦክሰኛ ነበር። ለሶስት ዓመት በወታደርነት ተመዝግቦ አሜሪካንን አገልግሏል። በግጥሚያ ሳቢያ የሚገኝ ገንዘቡን ለጦር ኃይሉ በስጦታ መልክ አስረክቧል፣ በውትድርና ደሞዝ ብቻ እየኖረ ዘጠና ስድስት ግጥሚያዎች (Exhibition bouts) እየተዘዋወረ "በጥቁር" እና "ነጭ" ካምፕ ተከፍሎ ለነበረው የአሜሪካ ጦር ኃይሎች አሳይቷል። ሆኖም ይህ ሁሉ በቂ አልነበረም። የአሜሪካው መንግስት ያልተከፈለ ቀረጥ አለብህ በማለት ሲያበሳጨት ከርመዋል። በመጨረሻም ገንዘብ የለሽ ድሃ ሆኖ ላስ ቬጋስ ውስጥ በሚገኝ የቁማር ቤት በአስተናጋጅነት ተቀጥሮ ነበር።

የመጀመሪያው ቦክሰኛ ጃክ ጆንሰን እና ሁለተኛው ጆ ሉዊስ እንዱ በነጭ የተጠላ ሁለተኛው ለነጭ ያገለገለ "መጥፎ ባሪያ" (Bad Nigger) እና "አቃጣሪ" (Uncle Tom) በመባል ይታወቁ እንደነበረ የቦክስ ታሪክ ያሳያል።

የእነዚህ ሁለት ግንባር ቀደም የቦክስ ሻምፕዮናነት ታሪክ ከበስተኋላቸው በመጡት ሌሎች ቦክሰኞች ላይ ልዩ ተፅእኖ ነበረው። ከጆ ሊውስ በኋላ የከባድ ሚዛን ምድብ በጥቁሮች እየተሞላ ሲሄድ ይህ 'Bad Nigger' (መጥፎ ባሪያ)እና 'Uncle Tom' (አቃጣሪ) የሚሉ መጠሪያዎች ኋላ ለመጡትም ቦክሰኞች እንደ መጠሪያ ወይም አንዱን ቦክሰኛ ከሌላው መለያ ቅጽሎች ለመሆን በቁ። የቦክሱ ዓለም የፈለቀበት ህብረተሰብ ውስጥ የሚታዩት ጭቆናዎችን ማንፀባረቅ ጀመረ።

በተከታታይ የመጡት አዲስ የከባድ ሚዛን ምድብ ቦክሰኞች ፍሎይድ ፓተርሰንና ሶኒ ሊስተን ነበሩ። ፍሎይድ ፓተርሰንን ከብሩክሊን ጌቶ አውጥቶ ወደ ቦክሰኝነት ዓለም የወሰደው ኩሥ ዲአማቶ (Cus D'Amato) የሚባል ፈረንጅ አሰልጣኝ ነበር። (በነገራችን ላይ የዘንድሮውን ዝነኛ ቦክሰኛ ማይክ ታይሰንንም ከነበረበት የጌቶ ኑሮ አውጥቶ ወደ ቦክስ ዓለም የከተተው ይኸው ፈረንጅ ነበር።) ፍሎይድ ፓተርሰን ረጋ ያለ፣ ገንዘቡን የማያባክንና ቤተክርስቲያን አዘውታሪ በመሆኑ ሰፊ ተወዳጅነት ነበረው። በተለይ በነጩ ህዝብ ወገን ተወዳጅነቱ ግልጥ ነበር። በወጣት ዕድሜው የተቀዳጀው የከባድ ሚዛን ሻምፕዮናነት በዋይት ሀውስ ቤተ መንግስት ውስጥ በክብር እንግዳነት ያስጠራው ከመሆኑም በላይ፣ ፈረንጅ ሴት አግብቶ በፈረንጆች ሰፈር ቤት ገዝቶ የሚኖር ሻምፕዮን ነበር። በሌላ ወገን የሶኒ ሊስተን ሁኔታ ከዚህ የተለየ ነበር። ሶኒ ሊስተን ቦክሰኝነትን የጀመረው እስር ቤት ውስጥ በነበረበት ጊዜ ሲሆን ወደ ፕሮፌሽናል ደረጃ የተዛወረው ከሚዘረ እስር ቤት ውስጥ እስራቱን ጨርሶ ነፃ የተለቀቀ ጊዜ ነበር። በ1956 ዓ/ም ከፖሊስ ጋር ባደረገው ግጭት ጭማሪ እስር ተፈርዶበት ለ9 ወር ካገለገለ በኋላ ይኖር የነበረው ትርኪ ምርኪ ስራዎችን–ዘበኝነት (Body Guards) የመሳሰሉትን በመስራት ነበር።። በ1962 ዓ/ም አካባቢ የሶኒ ሊስተን ሪከርድ ሲታይ አስራ ዘጠኝ ጊዜ በፖሊስ የተያዘ ወንጀለኛ መሆኑ ግልጥ ነበር። ፓተርሰንን ለመግጠም በሚዘጋጅበት ወቅት ጋዜጠኞች ለሚያናፍሱት ወሬ ይህ የፖሊስ ሬኮርድ ሶሊ ሊስተን ወንጀለኛ ወይም መጥፎ አርአያ (Bad Role made) አስመስለው ከማቅረባቸውም በላይ የሶኒ ሊስተን የውልድ ሰርተፍኬት (Birth Certificate) ለማግኘት ባለመቻላቸው የሶኒ ሊስተን ወንጀለኛነት ይበልጥ የተረጋገጠ መስሏቸውም ነበር። ሆስፒታል ውስጥ ባለመወለዱ – በድሆች መንደር ውስጥ አንድ ገጠር ቦታ ነበር የተወለደው – የውልድ ሰርተፍኬት የሌለው ቦክሰኛ፣ ብዙ ጋዜ የእስራት ሪኮርድ ያለው ሰው ለነጩ ዓለም አስፈሪና ተቀባይነት የተነፈገው የቦክስ ተወዳዳሪ ነበር። ብዙ አሜሪካኖች ፓተርሰንን በመደገፍ ሶኒ ሊስተን ይሸነፋል በማለት ገንዘባቸውን አስያዙ። ሆኖም ገና በመጀመሪያው ዙር ላይ ሶ ሊስተን በሰነዘረው ቦክስ ፓተርሰንን ዘረረው። አሸናፊነቱንም ተቀዳጀ። ቀጣይ ቦክሰኛ ካስየስ ክሌይ (መሀመድ አሊ) ነበር። ፓተርሰን ተሸንፎ ሶኒ ሊስተን ሻምፕዮን በመሆኑ – ይህ ሻምፕዮን የነጮች ቅዠት (White's Nightmare) ተብሏል። ሶሊ ሊስተን በሻምዮናነቱ ብዙ ሳይቆይ ተሸንፎ እንዲቀርላቸው የሚመኙ ብዙዎች ነበሩ። በዚህ መሰረት ካስየስ ክሌይ ለግጥሚያው በሚዘጋጅበት ወቅት የነጮች ተስፋ (White's hope) ተብሎ ተስፋ የተጣለበት ቦክሰኛ ነበር። እንዳውም ፓተርሰንና ሶኒ ሊስተን በተጋጠሙበት ሰዓት ቦክስ . . . (ወደ ገጽ 44 ይዞራል)

# ፖለቲካና ባላገር

ከሂርጳሳ አንዱዓለም (ከአለፈው የቀጠለ)

ልጅአምበራ የጎጃም እምብርት ነው። ጤፍ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ ግብጦ ያበቅላል። ይልቁንም ግብጦ ደህና ይመረትበታል። ግብጦ እንዲህ የዋዛ አዝመራ አይደለም። አረቄ፤ ጠላ ይሆናል። የግብጦ አረቄ ስም አለው። ለደም ብዛት ፍቱን መድሃኒት ነውም ይባላል። የግብጦ ንፍሮ ለልጅ ቤት፣ ለችግር ቀን መግፊያ፣ ማለፊያ ቀለብ ነው። ተቆልቶ በውሃ ይነከርና ከዚያም እየተጎለፈተ ተጠርጥሮ ይበላል።

ልጅአምበራ ከሰከላ ማዶ ከአዴት ወዲህ መሃሉ ላይ ተጣብቆ ያለ አገር ነው። ድሮ ድሮ በሰከላ ወረዳ ክልል ውስጥ ነበር። በኋላም ወደ አዴት ወረዳ ተከልሎ ትንሽ ቀን ታይቷል። አንዳንዴ ከሁለቱም ወረዳ ሳይሆን እንደ ጠፍ መሬት ገዥ ሳይረግጠው፣ የመንግሥት ሹም ሳያውቀው፣ የጎበዝ አለቃና የሽፍታ መፈንጫ ሆኖ ይከርማል። ልጅ አምብራ ወጣ ገባ፣ ገደላማና ሰባራ መሬት የሚበዛው ሲሆን ደልዳላ መሬት የለበትም። ጎርፍ ያጠቃዋል። ናዳም አለው። አንዳንዱ አካባቢ በዶማ ጋራ ጋራው ከሚቆፈር በቀር በአብዛኛው በበሬና በፈረስ ነው የሚታረስ።

ልጅአምበራ አስራ ሁለት ደብር ነው። አራት ቀበሌ ገበሬ ማህበር አለው። አንዱ ቀበሌ ገበሬ ማህበር አራት ደብር ይገዛል።

አበጃሜ ሚካኤል – አንድ
ልጅአምበራ መድኃኒያለም – ሁለት
ዱሌ ኪዳነምህረት – ሶስት
አብሰከን ማርያም – አራት ሆነ ማለት ነው።

ልጅ አምበራ መድኃኒያለም ደጋ ሲሆን አበጃሜ ሚካኤል ደግሞ ጮቄ ደጋ ነው። በጣም ደጋ!

የልጅአምበራ ሰው ቋንቋው በሆዱ ነው። ብዙ አይናገርም። ከተናገረም ግንባሩን እያጥፍም። ጠሊያ ልጅአምበራ ሞፈር መቁረጥ ያውቃል። ካልተለበለበ መቼ ይታረቃል። የተባለለት ልጅአምበራ ተከፋው ተቆረጠ ወንድነቱን ገልቦ ካላሳየ አይሆንለትም። ዋና ገበያቸው አርብ ገበያ ነው። አዴትም ሰከላም ይገበያያሉ። ከሰከላ ይልቅ አዴት ይቀርባቸዋል። ሰከላ ትንሽ ራቅ ይላል። ጓዝ ሳልያዘ ደህና ጠብጣቢ የአራት ሰዓት መንገድ ነው። የልጅአምበራ ሰው ሰላም አግኝቶ አርፎ አያውቅም። የጥጃ ሌባ፣ በረት ገልባጭ፣ አጥር ሰርሳሪ ሾለክላካ ሌባ አይጠፋበትም። ነፍሰ ገዳይ ቀማኛም እንዱ ሰባራ መሬት ውስጥ ተወሽቆ ብዙ ያስቸግራል። ብቻውን ሂያጅ ጦልቧላ መንገደኛ ሲያገኙ ሕይወቱን አጥፍተው ገንዘቡን ሞጭቀውበት ይሄዳሉ።

ልጅአምበራ የመኪና መንገድ ቀርቶ እንደልብ የሚያራምድ ጥርጊያ ጎዳና የለውም። ፖሊስ አይቶት፣ የመንግስት ሹም ረግጦት አያውቅም። መንግስት የማያውቀው፣ ገዥ የማይደርስበት ልጅአምበራ እርስ በእርሱ ተደጋግፎ፣ በሀዘን በደስታው አብሮ ተጋግዞ የመኖሩን ያህል በደም የመፈላለግ የነፍስ ግድያውም በዚያው ልክ ነው። ወንድም የተገደለበት የገዳይን ወንድም በመግደል ደም ይመልሳል። ይሄ የጎጃም ደንብ ነው። ልጅአምበራ ደግሞ ይተዳደርበታል። የወንድሙን ወይም የሚች ወገኑን ደም ማውጣት ያልቻለ ወንድ እንደሰው አይቆጠርም። ይዘፈንበታል። በለቅሶ ሙሾ ይወረድበታል። እንደወንዶቹ በሰው መሃል አፉን ሞልቶ ለመናገር አደባባይ ሕዝብ መሃል ለመቆም አይቻለውም። "ደም አውጪ የሌለው እንደእከሊ ደም" እየተባለ ይተረትበታል። በሰርግ ይዘፈንበታል። በየአጋጣሚው ሁሉ "የወንድምህን ደም ያላወጣህ" ተብሎ ይሰደብበታል። ወንድሙ የተገደለበት ቆሞ የሚያስቀብር ከስንት አንድ ነው። ወዲያው ዕለቱኑ ገስግሶ ሂዶ የገዳይን የቅርብ ወገን አንድ ሁለቱን ነድሎ አንጥፎት ይሄዳል። ቆሞ ቢያስቀብር እንኳ ውሎ አያድርም። ደም በደም መከፈል አለበት። የጎጃም ህግ የልጅአምበራ መተዳደሪያው ነው። ገዳይ ከአገር ቢጠፋ ደምመላሽ ወንድም የገዳዩን ዱካ እያፈላለገ ቆይቶ አድምጦ አድምጦ እተሸሸገበት ደርሶ በእሳት ጮራ በጠራራ ፀሐይ አንጋሎት ይሄዳል። የሚገደል የቅርብ ዘመድ ቢጠፋ ተረግዞ እስኪወለድ ወይም በማህፀን ያለ ጽንስ ተወልዶ እስከሚያድግ ጠብቆ ይበቀላል። ከጠፋ ከጠፋ እስከልጅ ልጅ ይጠበቃል። ገዳይ ሚስት ኑራው ሚሽቲቱ ልጁን ይዛ ብትሰወር እንኳ ለደም መመለሻ የሚሆን የገዳይ የቅርብ ዘመድ ከጠፋ የሚች ወገን ሚሽቲቱ እገባችበት አብሮ ገብቶ ልጁን ገድሎ ደሙን ይመልሳል። ሕግ ነው። የልጅአምበራ ሕግ! ደም በደም ብቻ ስለሚወጣ የሽማግሌ ዕርቅ አያቆመውም። በእንዲህ ዓይነቱም ጉዳይ ሽማግሌ አይገባም።

ጊዜው 1982 ዓ.ም አጋማሽ ላይ ነው። የልጅአምበራ ሰው ከአባይ ማዶ ከደብረታቦርና ከጋይንት የሚደርሰው የወያኔ ወሬ ልቡን አቁሞታል። ከወዲህ ግድም ከወደማርቆስ ከወደፍኖተሰላም ከብር ሽለቆ የሚሰማው የሰራዊት ምልመላ የዘመቻና የጦርነት ዝግጅት ደግሞ ሰላም ነስቶታል። የራሱ ብዙ ብሶት አለው። አቤት የሚልበት ጠፍቶታል። የሚካኤል ዕለት ቅዳሴ አስተጓጉሎ በአውራጃው ሹም ዘንድ ቀርቦ አቤት ለማለት ብዙ ሰው ወደ አውራጃው ከተማ ይጎርፋል።

የሚካኤል ዕለት አንዱን ቀን የአውራጃው ሹም በማሰልጠኛው ጣቢያ ገብቶ ሲሰለጥን የከረመውን ሚሊሽያ ዒላማ ለማስተኮስ ከወዲያ ወዲህ ይራወጣሉ። አስተኳሽ ወታደሮች ጠመንጃ ጥይትና ዒላማ ማስተኮሻውን አሰናድተው ሚሊሽያውን ከካምፕ ለማስወጣት የሹሙን ትዕዛዝ ይጠባበቃሉ።

አውራጃ ሹሙ ወደ ማሰልጠኛ ጣቢያው ፈጥነው ለመሄድ ከቢሮአቸው ሲወጡ በራቸውን ይዞ ብዙ ባላገር ተሰብስቧል። የእያንዳንዱን ጉዳይ እንዳይመለከቱ ተቻኩለዋል። ረግጠውትም አልፈው እንዳይሄዱ የባላገር ባለጉዳያተኛ ነጠላ አደግድጎ እያሳልፍም። ለአፍታ በረንዳው ላይ ቆም አሉና የሚጠብቃቸውን ባላገር ተመለከቱ።

"ምንድነው ጉዳይዎ አባቴ?" አሉ ነጠላቸውን አደግድገው ወደቆሙት አዛውንት እየጠቆሙ።

"እግዜር ያሳይዎ ጌታው አገር የቆረጠልኝን ደመወዜን ተከለከልኩ" አሉ ሽማግሌው ወደፊት ቀረብ እያሉ።

"የምን ደመወዝ?"

"ጥለተ በረድ እዞራለሁ። አገሩን ከተምች ከበረዶ እጠብቃለሁ። ልብስና ጉርሴን አገሬው ቆርጦልኝ ነበር። የሸንጎ እንደራሴው ነው ያስከለከለኝ"

"ማነው ስምዎ?"

"መሪጌታ ምን ይችል ሆዴ እባላለሁ።"

"የት ገበሬ ማህበር ነዎት?"

"ልጅአምበራ መድኃኒያለም ነኝ። ከዚህ ቀደምም ቅኔ መወድስ ለዚህ ለእንደራሴው አቅርቤለት ጥምጥም እንኳ ሳይገዛልኝ አሁን ይብስኑ አገር የቆረጠልኝን ደመወዜን አስከለከለኝ።"

"ምን ነበር የተቀኙለት?" ሲል ጠየቁ ሹሙ።

"ኧረ! እንዲህም አልነበር ጌታው! ቢያውቀው ለእርሱ የሚገባም አልነበር!"

"እስቲ ይንገሩኝ። ልስማው። ምን ነበር ቅኔ መወደሱ?" አሉ ሹሙ በለበጣ ዓይነት።

ሽማግሌው ቅኔ መወደሱን ለማስታወስ አንገታቸውን ትንሽ ዘንበል፣ አይናቸውን ከደን አድርገው ቆዩና አፋቸውን አሞጠሞጡና ከትከሻቸው ቀና ሰገግ ብለው።

"አብዮት ጎዳና በጣም ተራቀቀ፣
የልጅ አምበራው ካህን ከሸንጎ ዘለቀ።
ጓድ መንግስቱ ኃ/ማርያም
በጣም ልጅ አውጥቷል፣
የልጅአምበራው ካህን አማካሪ ሆኖ
ማርቆስ ላይ ተሹሟል፣
ሕጎችን እንደምንጭ በቃሉ ያፈሳል።
ደግሞ ሕገ-ምንጩን ፀበል ቢያደርጋቸው፣
ህመምተኛው ጭቁን ተፈወሰባቸው።

"በቃዎት በቃዎት። ሰማነው አባቴ! ይሂዱና ከእርሱው ጋር ይጠያየቁ። ይሄ እኛን አይመለከትም።" አሉ ሹሙ።

"እንዴት ነው የማይመለከት ጌታው? እርሱንማ ጠይቄው እንጃባክ ብሎኝ ነው ወደዚህ መምጣቴ።"

"አሁንም ይሂዱና እርሱኑ ይጠይቁት"

"እንዴት? እኔ የመንግስት ድሃ አይደለሁም? አገር የቆረጠልኝን ደመወዜን ስከለከል እንዴት ነው እርስዎ የማይዳኙኝ?" አሉ ሽማግሌው በእልህ እየተንቀጠቀጡ።

"ነገርኩዎት እንግዲህ ከሰሙ ይስሙ። ይሄ እኛን አይመለከትም።"

"ወደዩትም አልሄድ እኔስ። እዚሁ እመንግስት ደጅ እሞታለሁ።"

"ምን ይላል ይሄ ተብታቢ ደብተራ። ሲነግሩት አይሰማም? ሂድ ወዲያ!" አሉ ሹሙ በቁጣ ወደ አንዲት አሮጊት ባለጉዳይ እየሄዱ።

"እርስዎስ ለምን መጡ እናቴ?" አሉ ወደ አሮጊቷ ዞር ብለው።

"ልጅ እያለ ምን መኝታ አለ ጌታው? ዘንድሮ ፀሎቴ አልተሰማም። ቅዱስ ሚካኤል ተቀይሞኛል። ከአንድ ቤት እንዴት ሶስት ጎበዝ ይዘምታል? እኔን ማን ያጥባኝ? ማን ይቅበረኝ? ወልጄ ወልጄ በስተእርጅና ሜዳ ወድቄ ጅብ ይብላኝ? ታላቅየው የዛሬ ስንት ዓመት ሕዝባዊ ሰራዊት ሁኖ ዘመተ። ታናሽዩውም እቻምና ታጣቂ ሁኖ ዘምቶ ይሂው ይኑር ይሙት አይታወቅም። የመጨረሻው አንድ እርሱ

ቢቀረኝ መሣሪያ ተነእንግቱ ይሰጣችኋል ተብሏልና ስልጥኜ ጠመንጃ ታጥቄ መጣለሁ ብሎ እዚህ እናንተ ዘንዳ ሰልፍ እየረገጠ ነው። እኔ እንግዲህ ምን ልሁን ጌታው?" አሉ አሮጊቷ በመቀነታቸው እንባቸውን እየጠራረጉ።

"መሣሪያ ተሰጥቶአቸውማ ወደቀበሌያቸው ይመለሳሉ።" አለ ሹሙ።

"አይ አለማወቅሽ አገርሽ መራቁን አሉ። ምኑን ወደቀበሌው ተመለሰ ጌታው? ቅጥንብሩ ጠፍቶ በየቤቱ ልብ መድቃት ሁኖ እያዩቱ? እኔስ የመንግስት ድሃ አይደለሁ? ማን አለኝ? ልጄን ብቻ አውጥተው ይስጡኝ። መሣሪያው ተነእንግቱ ይቅርበት። እኔ ጥገቴን ሽጬ እገዛለታለሁ።"

"ይህን ችግርዎን ጠቅሰው ማመልከቻ አስገብተዋል?"

"የለም! ሁሉን አልይገኘው ሁኜ? እዛባ መዛቅና ከማድቤት ማደፍደፍ እንጂ ማመልከቻ መፃፉንስ አደባባይ መዋሉንስ የት አባቴ አውቄበት ብለው?"

"ያውልዎት እዚያ ጋ ማመልከቻ የሚጽፍ ሰው አለ። ያጽፉና መዝገብ ቤት ገቢ ያድርጉ?" አሉ ሹሙ። አሮጊቷ ግንባራቸውን መሬት መንካት እስኪቀረው ለጥ ብለው እጅ ነስተው እየመረቁት ወደ ራፖል ፀሐፊው አመሩ።

"ጌታዬ የማመለከተው ጉዳይ ነበረኝ!" ሲል አንድ ከሲታ ባላገር እየጮኸ መጥቶ ከሹሙ ፊት ቆመ።

"ምንድነው የአንተ ደግሞ?"

"አምራች እንዲፈርስ፣ ድሃ ወደባድማው እንዲመለስ፣ የተነጠቀው ማሳ እንዲመለስለት አዲስ አዋጅ ስለወጣ ለእኔም እንዲፈረድልኝ ነው ጌታው?" አለ ባላገሩ።

"የምን አዋጅ? መቼ የወጣ ነው ይሄ የምትለው አዲስ አዋጅ?" ሲሉ ባላገሩን መልሰው ጠየቁ ሹሙ።

"መች አጡት ጌታው? እንኳን እርስዎ ድፍን የጎጃም ገበሬ ጋዜጣውን በአንዳንድ ባውንድ እየገዛ እንደዳዊት በብብቱ ይዞት የለ?"

"እኔ አላውቅም እንዲህ የሚል አዲስ አዋጅ" አሉ ሹሙ በጥያቄ ዓይነት።

"የቅይጡን ጋዜጣ ነው የሚለው።" አለ አንዱ ባላገር ከጎኑ።

"የቅይጥ ኢኮኖሚ ፖሊሲ የወጣበትን ጋዜጣ ከሆነ የምትለው እርሱ ሌላ ነው።"

"ምነ እንዲያው መጥታችሁ አንድ ቀን ለአንዲት ደቂቃ እንኳ ብታዩልን? ጎመን የምንበትንበት አጥተን ዛሬ ውሎአችን እንደሴቲቱ ከደጅ ሆኗል። እናንተ አይታችሁልን እረፉ ብትሉንና ፈርዳችሁብን እርሻው በቀረብን።"

"የመሬት ጉዳይ አውራጃ ገበሬ ማህበርን ስለሆነ የሚመለከተው ሂዱና እዚያ አመልክቱ። እነሱ ናቸው ይህን የሚፈቱላችሁ።" አሉና ሹሙ ወደ ሌላ ባላገር ባለጉዳይ ዞሩ። ተቻኩለዋል። ልባቸው ዒላማ ማስተኮሱ ላይ ነው።

"ምንድነው የአንተ ጉዳይ?" አሉ ሹሙ። ከራስጌ እስከግርጌ ገጹን ሙሉ ግጥም ተደርጎ የተቸከቸከ ማመልከቻውን በሁለት እጁ አንከርፎ ወደቆመ ባላገር ዞር ብለው።

"ይህቺን ይዩልኝ ጌታው።"

"በቃልህ ንገረኝ። ይህን ሁሉ ሐተታ ማን ሲያነብ ይውላል?" አሉ

ሹሙ ከላይ እስከግርጌው ድረስ በተወላገደ ጽሁፍ የተቸከቸከውን ማመልከቻ ባላገሩ እጅ ላይ ቁልቁል እየተመለከቱ።

"የለም ጌታው። የኔውስ የሌላ ነው። ይህቺን ብቻ አንዴ ይዩልኝ" አለ ባላገሩ በማስተዛዛን።

"ምንድነው? የመሬት ጉዳይ ነው?"

"የለም።"

"ስርቆሽ ነው?"

"የለም። የኔውስ የሌላ ነው። ምነ ማመልከቻዬን አንዴ ቢያዩልኝ?" አለ ባላገሩ በጭንቀት ስሜት።

"የነፍስ ግዳይ ነው?"

"የለም ጌታው? የኔውስ የብቻው ነው። ራፖል ፀሐፊው ደህና አሳምሮ ጽፎልኛል። አንዴ ብቻ ቢያዩልኝ!"

"እንግዲያ ምንድነው? በቃልህ እማታስረዳኝ? ይህን ሁሉ ሀተታ የማነብበት ጊዜ የለኝም።" አሉ ሹሙ። ባላገሩ ለራፖል ፀሐፊው ተናዞ ተናዞ ደህና በወረቀት የተከተበለትን አቤቱታውን በቃልህ አስረዳ ሲባል ከዩት እንደሚጀምረው ግራ ገብቶት ዝም ብሎ ቆየና:-

"የሰው ሁሉ ችግሩ ለየቅል ነው። ጌታው!" አለ ድንገት ከአፉ የወጣ ያህል።

"ሰውዬ የራስህን ችግር ተናገር። ስለሌላው ሰው ችግር አያገባህም። ምንድነው ጉዳይህ?" አሉ ሹሙ ባላገሩን በማመናጨቅ።

"የትጥቅ ነው ጌታው! አንዲት ብረት ነበረችኝ። የገበሬ ማህበር ሊቀመንበሩ ለመንግስት ገቢ አደርጋለሁ ብሎ ነጥቆኝ አንድ አውደልዳይ አማች አለው ለእርሱ ሰጠብኝ። አገር ያወቀው አውደልዳይ ነው። ስለተሸከመው ተኳሽ የሆነ መስሎት እደረሰበት ሁላ እያነገታት ይዞራል። ባየሁት ቁጥር ደሜ እየፈላ ቆሽቴ አረረ! አሁንም ትጥቄ እንዲመለስልኝ ነው አቤቱታዬ። ጠመንጃዬ ተተመለሰችልኝ እርሷን ይዤ ለእናት አገሬ ዘምቼ ብሞትም ፍቃዴ ነው። ይህ አዲሱ የቅይጥ አዋጅም ይደግፈኛል ጌታው!"

"ይህን አዲሱን አዋጅ እኛ ሳንሰማው የጎጃም ባላገር አውቆታላ ባካችሁ? ለመሆኑ ጠመንጃህ ምንድናት?" አሉ ሹሙ በመገረም።

"አጭር ምንሽር ናት ጌታው!"

"ታዲያ እንዲሁ ትመለስልኝ ብለህ አመልክትይ ለዘመቻ ምን ትሰራለች አጭር ምንሽር?"

"ትሰራለች ጌታው ባለቤቷ ታልፈራ ብዙ ትሰራለች።"

"መች ነው የገዛሃት አንተ?"

"ኸረ! ከእኔው ጋር የኖረች ነበረች። ኩታራ የነበርኩ ጊዜ ነው የገዛኋት"

"በል ማመልከቻህን ይዘህ ለፖሊስ አዛዡ አመልክት። የትጥቅ ነገር እነርሱ ናቸው የሚያዩልህ።" አሉና ሹሙ ባላገሩን አሰናበቱት።

ወዲያ ፈንጠር ብለው ዳዋት ያነገቱ አንድ ሽማግሌ፣ ሁለት ቄሶችና አንድ ልጅ እግር ባላገር ቆመው ሹሙ እስከሚያናግራቸው ተራቸውን ይጠባበቃሉ። ከቤተክህነት የተፃፈ ደብዳቤ ይዘዋል። ለጥ ብለው እጅ ነስተው ቆሙና አደግድገው ቆሙ።

"የእናንተስ ምንድነው?" አሉ ሹሙ ወደ እነርሱ ዞር ብለው።

"ይኸውልዎ ጌታዬ! ይህን አሽከር ምርጥ ዘር የትዋለ የተባለች ሴት በባሕላችን መሰረት ልጇን ከዳረችለት በላይ እርሱ ትምህርቴ አንሶኛል ልጨርስ ብሎ አሰዋ መዲያኔዓለም ድረስ ሂዶ ተምሮ ሲመለስ ሚሽቱን አልሰጥህም ብላ ይሄ አሽከር ስልጣነ ኪነት እንዳይበቃ ስለአረገችብን ከእርስዎ ዘንድ ታጣቂ እንዲሰጠን ነበር " አሉ አንደኛው ቄስ።

"የምን ታጣቂ?" አሉ አውራጃ ሹሙ በቁጣ።

"ሴቲቱ ይህን አሽከር ሊቀ ክህነቱን ልታስፈርሰው ስለሆነ አስገድዶ እርስዎ ዘንድ የሚያቀርብልን ታጣቂ ነው ጌታው"

"ምንድነው የምትቀልዱት እናንተ? ከስንት በኩል እንደንፈፊት ተወጥረን አንዲት ሴት አስገድደን ለማምጣት ታጣቂ ወታደር እንድንልክ ትጠይቁናላችሁ? በሉ ዞር በሉ ወደዚያ . . . ምን ዓይነት . . . አንተኛውስ?" አሉ ሹሙ በብስጭት በማጉተምተም ከቄሶቹ ጋር ወዳሉት ሽማግሌ ዞር ብለው።

"ከእነርሱው ጋር ነኝ ጌታው።" አሉ ሽማግሌው ቆፍጠን ጎርነን ባለ ድምፅ።

"በሉ ዞር በሉ ከእናንተ ጋር ጨርሻለሁ። እናንተ የደላችሁ ናችሁ ቀልደኞች!"

"የለም ጌታው! እንግዲህ መቼስ ምንም ቢሆን በአገር ተወክለን ነው የመጣነ። ሴቲቱ ነገርተኛ ናት። ቄስ መለኩሴ ቢላክባት ነገ ተነገወዲያ እያለች ስታጉላላ ቆይታ ኋላ አንድያዋን አሻፈረኝ ብላው አረፈች። ይህም ጉብል "ስንት ዓመት ሙሉ ተንከርትቼ ተንከርትቼ ለስልጣነ ኪነት ሳልበቃ ብሎ ሀዘን ቢጎዳው፤ ተምሬ ተምሬ እንዴት ትምህርቴን ውኃ ይበላብኛል ብሎ ቢበሳጭ ጊዜና አውራጃው ዘንድ ይዛችሁት ሂዳችሁ ፈጥሙለት ብሎ አገር ቢወክለን ነው መምጣታችን። አሽከሪቱን አግብቷት ስጋ ወደሙ አብረው ወስደው ካልቆረቡ ለስልጣነ ኪነት ሊበቃ አይቻለውም። ሌላም ሳግባ ቢል አፍራሻ መሆኑ ነው - ደብተራ!! አፍራሻ አፍራሻው፣ እዳሪ እዳሪውን እንጂ ቤተመቅደስ ገብቶ ሊቀድስ አይችልም። በዚህ ላይ አብረውት የተማሩት ጓደኞቹ ስምንት ዘጠኝ የሚሆኑቱ አንደኛውን መሣቂያ ያረጉታል? ኸረ! ከብስጭቱና ከንዴቱም አይተርፍ! ገና ለገና አሁን እንኳ "ምን ብዬ ነው ወደዚያ የምመለስ በዚሁ ወደ አንዱ አገር እጠፋለሁ። ምነው ቁራሽ ለምኜ ፎክቼ ተምማር ቀንጃ ገብቼ እንደሆንኩት ሆኜ በሆነ" እያለ ሆድ ይብሰው ጀምሯል።

"እና ምን አድርጉ ነው የምትሉን?" አሉ ሹሙ በንዴት።

"ወታደር መላክ ቢቀር ትንሽ ምልክት ይስጡን ጌታው"

"የምን ምልክት?"

"ሴቲቱ ተገድዳ እንድትቀርብልን ትንሽ ወረቀት ጌታው። ይህ አሽከር ነገ አንድ ነገር ቢሆን ጠጠቱን አንችለውም።"

"የታለ እርሱ ልጁ?" አሉ ሹሙ። አንድ ቀጠን ዘለግ ያለ ልጅ ወደፊት ቀርቦ ቆመ።

"ተሜ! አንተ ነህ? ማነው ስምህ?"

"ዲያቆን አለሄኝ ገላጋይ" አለ አንገቱን በሀዘን ዘንበል አድርጎ በቅጭምታ

"እናቲቱ ከከፋች አንተ ሌላ እማታገባ? ስንት ቆንጆ ሞልቶልህ የለ!" አለ ሹሙ። እንደቀልድ እንደማፌዝ ብሎ!

"እንደርሱማ ፎክቼ ደክሜ ተምሬ ሊቀክህነቴ ይፈርስብኛል ጌታው። አፍራሻ ደብተራ መሆኔ ነው። አፍራሻ አፍራሻውን ቄሶቹ እንደከፉ ውሻ ነው የሚያዩት። ለሙትና ለተዝካር ጊዜ ዳዊቱን እየደገመ መሀራ ይበላልዩ ቤተመቅደስ ገብቶ አይቀድስም። ለዚያውም አፈር ብላ እየተባለ። ሥጋ ወደሙ አብሬያት ወስጄ ካልቀረብኩ ቅስናው አይሰጠኝም።" አለ ዲያቆኑ ሳግ እየተናነቀው።

"ስንት አሉ የአንተ ጓደኞች የቆረቡ?"

"አብረውኝ ተምረው፣ አግብተው፣ ቆርበው የሚቀድሱ እንኳ አንድ ስምንት ይሆናሉ። እነ አዲሱ፣ እነ ወርቅነህ፣ እነ አትንኩት፣ እነ ይታይህ፣ እነ እሱባለው . . ."

"በሉ የዛሬ ሳምንት ልጅቱን ይዛ እንድትመጣ ለሴትዮይቱ ንገሩዋት። ያን ዕለት ልጅቱን ይዛ ባትመጣ እንደሚቀና ወይፈን በአንገትሽ ቀንበር አስገብቼ ነው የማስመጣሽ ብሎሻል ብላችሁ ንገሩዋት። ለእርሷ ቀላጤ ስፅፍም አልገኝ በሉ ሂዱ።" አሉ ሹሙ በባለስልጣንነት አነጋገር። ሰዎቹም ደስ ብሏቸው እጅ ነስተው ተያይዘው ሄዱ።

"እርስዎስ አባቴ ምንድነው ጉዳይዎ?" አሉ ሹሙ ቀርበው እጅ ነስተው የቆሙትን ባላገር። አሮጌ ካፖርት የለበሱ አጠር ያሉ አዛውንት ናቸው።

"ስልስትና ለመጣሁበት ለዚያው ጉዳዬ ነው ጌታው" አሉ ሰውየው ችፍርግ ጢማቸውን እያሻሹ። አቤቱታውና መመላለሱ የታከታቸው ይመስላሉ።

"በአገር ሽማግሌ እንዲታይልዎት ለሸንጎ እንደራሴው ልኬዎት አልነበረም ወይ? ምን አለዎት?"

"እሱስ ያነዘረብኝ ጉዳይስ ሌላ ነው"

"እርስዎ ለምን ይሳደባሉ? ጉዳይዎ የተመራበት ሰው ሁሉ ሰደቡኝ ያላለ የለም። በዚህ ዕድሜዎ የስድብ ንግግር ነውር አይደለም እንዴ? ሁለተኛ አንድ ሰው ሰደቡኝ ብሎ ቢነግረኝ ይኸን ሽበትዎን በደረቁ ላጭቼዎት ነው አስገብቼ ከጥጃ ሌባ ጋር አቆራኝቼ የምጠፍርዎት?"

"የለም። ከእኔውስ አንደበት ስድብ አልወጣም ጌታው! የሚሄድበት ሹሞች ሁሎችም ለሚመለከተው ባለሥልጣን አቅርበን እናስፈጽምልሃለን፤ እኛ ማቅረብ እንጂ መፈጠም ስልጣን የለንም እያሉ ተሰአት ተመለስ፣ ነገ ተመለስ እያሉ እያመላለሱ ልቤን ቢያወልቁት ጉዳዬን መፈጠም የማትችሉ ከሆነ የማቅረብ የማቅረቡንማ እኔው ደጅ ጠንቼ አቀርባለሁ ብላቸው ነው ሰደበኝ የሚሉኝ። ጉዳዬን መፈጠም የማይችለውን የእኔ ቢጤውን ሰው ለምን ደጅ እጠናለሁ አልኩይ እኔ ስድብም አልወጣኝ። የተራብኩ፣ የተጠማሁ ደካማ ሽማግሌ ነኝ። በየትኛው ጉልበቴ ነው እምሳደበው ጌታው?" አሉ ሽማግሌው በሀዘኔታ ሳይሆን በተስፋ መቁረጥና በእልህ ዓይነት አነጋገር።

"የሸንጎ እንደራሴውን አልሰደቡትም? እዚህ እኔ ፊት ደካማ ነኝ ሽማግሌ ነኝ ከሚሉ አንደበትዎን ሰብስበው አቤት አይሉም? ምን ያሰድብዎታል? በሄዱበት ቢሮ ሁሉ 'እኒያ ተሳዳቢ ሽማግሌ' እየተባሉ መሆኑን ቢረዱት ጥሩ ነው። እንዴት አንድን በሕዝብ የተመረጠን የሸንጎ እንደራሴ ጓድ ይሰድባሉ?" አሉ ሹሙ በጥያቄ ሽማግሌውን እየተመለከቷቸው።

"እርሱው አይደል ገሚሱን የእንጀራ ልጅ ሌላውን አበልጅ እያረገ የአፍንጫ ላይ ቂጥኝ ሆኖ በሽታ የሆነብን! ሌላማ መች ከውጭ መጣብን።"

"ቢያውቁት አንድን የሕዝብ እንደራሴ ጓድ እንዲህ ማለቱ ራሱ ትልቅ ወንጀል ነው።"

"ዛሬ ነው ጓድ የተሆነው ጌታው! መሪጌታ ነበር። ቁራሽ ሲለምንበት የነበረው አኩፋዳ ኮሮጆው አበጃሜ ሚካኤል ደብር እዋርካው ላይ ተሰቅሎሎታል። እንኳንስ የልጅአምበራ ሰው ቀርቶ ቁራሽ ሲለምን ያስቸግሩት የነበሩት ውሾች እንኳ አልረሱትም። ገበያ ቢያመቻት እናቷን ሸጠቻት አሉ። ጊዜ ሲሰጣት

ጀግኒት መሪጌትነቷ ቀረና ጓድ ሁና የሸንጎ እንደራሴ ተብላ ከወንበሩ ላይ ፊጢ ተባለልኝይ! ጅራታም የአህያ ልጅ የማንተዋወቅ ሁነን ነው? ተውጭ አልመጣብን፣ ባዕድ አይደል፣ የዘለቀ ትምህርት የለው እኛው ጣታችንን ቀስረን የመረጥነውም አይዶል? ዛሬ እቤተመንግስት ገብቶ ባለስልጣን ጉያ ተወሽቆ የእርሱ አራት አራሽ አድርጎ የቀለደብን። ድፍን ባላገር እንደከበሮ ተለጉሞ ከሞቱት በላይ ከቆሙት በታች ሁነን ስንሄድ እርሱ እንደእርጉዝ ድርስ ሁኖ ተንጠርብቦ መጀነኑ በእኛው ትከሻ አይደል? ኋላ ይህን በወንጭፍ የሚዘራውን ገንዘብ፣ በየደረሰበት ለስንቷ ጋለሞታ የሚመዠርጠውን ባውንድ ከዬት አመጣው? አያቱ አላቆዩት? አባቱ አላወረሱት። አባቱ መምሬ ደግሰው ሞት ባይኖር ነፍሳቸውን ይማረውና አንድ ቀን እንደሰው ሳያምርባቸው ደህና እጅ ጠባብ እንኳ ሳይኖራቸው ነው አፈር የገቡት። ኮሮጃቸውን ይዘው በየሰው ቤት ለብድር ሲዞሩ ነው ሞት ደጉ የገላገላቸው። ምነው ጥንቅቅ አድርገን ስንተዋወቅ ጌታው" አሉ ሽማግሌው ያበጠው ይፈንዳ በሚል የቁጭት ስሜት እየተውረገረጉ።

"አይሳደቡ አንቱ ሽማግሌ ኋላ ነግሬዎታለሁ። እማይወጡበት ዳፋ ነው የሚገቡት።" አሉ ሹሙ በቁጣ።

"አልተሳደብኩም ጌታው። እውነቱን ነው የተናገርኩ።"

"አይሳደቡ ብያለሁ። አሻፈረኝ ካሉ ወስጂ ነው ከበሬ ሊባና ከነፍስ ገዳይ ጋር አቆራኝቼ እምጠፍርዎት።"

"ኧረ ባሰሩኝና እንደጨው እሟሟ እንደሆነ ልኬን ባየሁት! ከልጅአምበራ እየተመላለስኩ መንገድ ከሚጎዳኝ እንዲያዩን እዚሁ ማረፊያ ባገኘሁስ አልጠላም።

"አንድ ሳምንት ቁንጫና ትኋን ሲልስዎት እንዲህ አይሉም። ልክ ይገባሉ።"

"ኧረግ! ሕግ ፈርቼ እንጂ ስንት በረሃ የዋልኩ፣ ስንት ያየሁ ጅግና ነኝ። ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል! ይሄ ጅራታም የአህያይቱ ልጅ ዛሬ መቀለጃ አያደርገኝም ነበር። ምን ይደረግ! ውሻ የጌታዋን ጌታ አታውቅም አሉ።"

"አይሳደቡ እርስዎ ሰውዬ! የሸንጎ እንደራሴ አይሰደብም። ውርድ ከራስዎ ዛሬ።"

"እንዲህም አርጎ የሸንጎ እንደራሴ! እውነትም እንደራሴ! . . . በር መዝጊያ ተዳርሶ ያለ መስሎኝ!"

"ምን ለማለት ፈልገው ነው?" ሲሉ በጥያቄ አፈጠጡባቸው ሹሙ።

"እንጃ እኔስ? እየመሸ መስሎኝ! እየስፍራው ልብ መድቃት ሁኖ እያዩት! ብዙ አብረን መሰንበታችንን እንጃ ጌታው!"

"የመሸቦትስ እርስዎ ነዎት። አግበኛ ደብተራ። ይሂዱ ከዚህ። ሁለተኛ እዚህ እንዳይደርሱ" አሉ ሹሙ በቁጣ አይኖቻቸውን እያጉረጠረጡ።

"ኧረ እኔም አልመጣ። ከእንግዲህ ምን ቀረኝና! አንዱን ቀን የእንግላል ሲጥሉዋችሁ ሸሽገኝ ልትል ትመጣለህ። . . . ጅራታም የአህያይቱ ልጅ ሁላ" አሉ በማጉተምተም። እየተቆናጠሩ መንገዳቸውን ቀጠሉ።

የአውራጃው ሹሙ ልባቸው ወደ ዲላማ ማስተከሻ ስፍራው ቀድሞአቸው ሄዷል። ባለጉዳይ ደግሞ ሊለቃቸው አልቻለም። የእያንዳንዱ ባለጉዳይ አኳኋን አላማራቸውም። በብስጭት መንፈስ ወደ መኪናቸው እየሄዱ እያሉ አንድ ራስ በራ አዛውንት ቀርበው እጅ ነሱ። ከወገባቸው ጎንበስ ከአንገታቸው ዝቅ ብለው እጅ ሲነሱ በብታቸው ስር ያነገቱት ዳዊት ተንጠልጥሎ ይታያል።

"ምንድነው?" አሉ አውራጃ ሹሙ። በተሰላቸና በተቻኮለ አኳኋን

"አንድ ችግር ፈጠብኝ ነው ጌታው።" አሉ ሰውየውም እንዴ ወደ ሹሙ እንዴ ወደተከተላቸው ባላገር ዞር እያሉ።

"ከየት ገበሬ ማህበር ነው የመጣችሁት?"

"ልጅአምበራ መዲያኔዓለም"

"የልጅአምበራ ገበሬ ዘንድሮ አንድያውን ግብርናውን ትቶ ውሎው አደባባይ መሆኑም አይደል እንግዲህ!" አሉ የአውራጃው ሹሙ በመሰልቸትና በምሬት አነጋገር "ለምን ታስቸግሩናላችሁ? በየቀበሌያችሁ አስታራቂ ሽማግሌ ገላጋይ ፈልጋችሁ ጉዳያችሁን እዚያው እማትጨርሱ?"

"ያለ ዕውቀት ይሆናል ጌታው! ነገሩ ነገር እየወለደ የምናደርገው ቋንቋው ጠፍቶንም አይደል

በዚህ አዝመራ ወቅት ይህን ሁሉ መንገድ ተጉዘን መጥተን መንጓለላችን። ይኸው እምና የመጋቢት አቦ ጀምሮ አፋችን ከጨኸት፣ እግራችን ከቁመት ተለይቶም አያውቅ። እንደእኔስ ድካም የሚፈጠምልኝም አልሆነ። 'አንድ በሬ ስቦ አንድ ሰው አስቦ' አይሆንም ብል ጊዜ ነው ሞላው የደብሩ ሰው ተሰብስቦ የአገር ሽማግሌዎችና የጎበዝ አለቆች መርጦ ከኔ ጋር ወዲህ መሰደዱ። ከእንግዲህ እኔ ነጣ ነኝ።"

"እንግዲያ ድፍን አገር አስከትተው መምጣትዎ፣ አድማ አስመትተው ሊያስወርሩን ወይስ አገሬውን ሊያሸፍቱት ፈልገው ነው?" አሉ ሹሙ በባለስልጣንነት አነጋገር ሽማግሌውንና ክብብ አድርጎቸው የቆመውን ባላገር እየተመለከቱ።

"የለም ጌታው እኔስ አልሆነልኝም። የአገር ጉዳይ እፈጥም ብሎ ከልጅአምበራ መዲያኔዓለም መንገድ ሲያዳፋኝ ውዬ ያለ አንድ መላ ባዶ እጄን መመለሱ ቢሸለቸኝ ለጉዳያችን ምን ቋጠሮ አበጀህለት ብሎ አገሬው አምርሮ ቢጠይቀኝ እኔ ደከምኩ ማንም ሰው አላለኝም ጉዳያችሁን ራሳችሁ ሂዱና አስፈጥሙ ብላቸው ነው ይህ የሚያዩት ሰው ተከትሎኝ መምጣቱ። እንዲያው ለነገሩ ቢሆንስ ጌታው! መቼስ ኑረውበታል። የልጅ አምበራን ሰው የጎጃምን ባህርይ ሲያውቁት እሹም ደጅ ቆሞ ነው አድማ የሚመታስ? ዘንግ ይዞ ነውስ የሚሸፍት?" አሉ ሽማግሌው በትዝብት አይን ሹሙን አተኩረው እየተመለከቱ። ዙሪያቸውን ከቦ የቆመው ባላገር ንግግራቸው ያጠገበው ይመስል በመርታት ስሜት እርስ በእርሱ አጉተመተመ።

"የስንት ደብር ሰው ነው እዚህ ያለው?" አሉ ሹሙ በእርጋታና በትእግስት። ሁኔታቸው አላማረውም። ወዲህ ወዲህ ደግሞ ማስልጠኛ ጣቢያ ያለውን ምልምል ሰራዊት ዒላማ ለማስተኮስ ልባቸው ተንጠልጥሏል። ቀልባቸው ቆሟል።

"የአራት ደብር ሕዝብ ተሰብስቦ የመረጣቸው ሽማግሌዎችና የጎበዝ አለቆች ናቸው።"

"ከዬት ከዬት?" አሉ ሹሙ አጀንዳቸው ላይ ማስታወሻ እየፃፉ።

"ልጃአምበራ መድያኔዓለም፣ አበጃሜ ሚካኤል፣ ዱሌ ኪዳነምህረት፣ አብለከን ማርያም። ይኸው ነው" አሉ ሽማግሌው ፍርጥም ብለው

"የአውራጃውን ፓርቲ 1ኛ ፀሐፊ እንዲያነጋግሩ ልኬዎት አልነበር የሚካኤል ለት መጥተው። ምን አለዎት?"

"የለም። አላግኝቶም። ስብስቦሽ ናቸው ተብዬ ጠብቄ ቢታክተኝ ወደ እርስዎ ዘንድ ተመልሼ መጥቼ ነገርኩዎት።"

"ታዲያ የሸንጎ እንደራሴውን እንዲያነጋግሩ መልሼ ልኬዎትም አልነበር?" አሉ ሹሙ። መኪናቸው ውስጥ ገብተው ወደ ዒላማ ማስተኮሻው ስፍራ ለመፈትለክ አቆብቁበዋል። ሽማግሌው መናገር ያልፈለጉትን ነገር እንዲናገሩ የተገደዱ ይመስል ፊታቸውን ቅጭም ግንባራቸውን ቁጥር አድርገው እንገታቸውን ወደ መሬት ደፍተው ዝም አሉ።

"ምን አለዎት?" አሉ ሹሙ ከዝምታቸው አንዳች ነገር ጠርጥረዋል። ከቧቸው የቆመው ባላገርም ስሜት እየደፈረሰ መሆኑ ታያቸው።

"የለም። በጅ አላለኝም። ያነዘረብኝስ ጉዳይ ሌላ ነው።" አሉ ሽማግሌው የእልህ ሲቃ በዋጠው አንደበትና በእርግጠኝነት። በዙሪያቸው ተቸምችሞ የቆመው ባላገር የጥቃቱ ምንጭ ወለል ብሎ የታየው ይመስል በቁጣ ስሜት አውካካ።

"ድሮስ መች አጣነው መጠቂያችንን! መንግሥት ደማችንን ያወጣልናል ብለንይ" አለ አንድ ጎርነን ያለ ድምፅ ከባለገሮቹ መካከል። አንገቱን አቀርቅሮ በአውራ ጣቱ መሬቱን እየቆረቆረ የሽማግሌውንና የሹሙን ምልልስ ሲያዳምጥ የቆየው ባላገር ሁላ ደሙ ፈላ። እስከዛሬ የሆዱን በሆዱ ይዞ ዋጥ አድርጎ ቀብሮት የኖረው ብሶት የገነፈለበት ያህል፣ የቆመበት አፈር የፈጀው ይመስል በቁጣና በቁጭት ተንጫጫ። ለእፍታ ውካታና ጫጫታ ፀጥታውን አደፈረሰው። እልህና ሲቃ በቦታው ተተካ።

"እያተዳመጣችሁ ጎበዝ" አሉ ሽማግሌው ወደ ባላገሩ ዞር በለው።

"ምን አለዎት ሸንጎ እንደራሴው?" አሉ ሹሙ ደገሙና።

"የልጅአምበራን አምራቾች ለማፍረስ አገሬውን እያሰደምክ መሆኑን ደርሰንበታል ነው ያለኝ።" አሉ ሽማግሌው ጥርሳቸውን ነክሰው።

"ደርሶ መሬታችንን ነጥቆ ለአምራቾች የሰጠብን ማን ሆነና ነው? እንዲህ ማለቱ።" አለ አንድ ደሙ የፈላ ባላገር

"ምነው እያ የማትዳኙን ከሆነ ቁርጡን ብትነግሩን" አለ ሌላው።

"ከእንግዲህ እኔ ነጣ ነኝ አገሬ!" አሉ ሽማግሌው ወደ ባላገሩ ዞር ብለው "ቢሻው አገሬው ከዚህ ካልሆነለት ማርቆስ ድረስ ሂዶም፣ አዲስ አበባም ቢሆን ሰው ልኮ ጉዳዩን ማስፈጠም ይችላል። እኔ ግን ከእንግዲህ ነጣ ነኝ።"

"እዚህ ያሉት ችግራችንን ያልሰሙን በእውነት ማን ይሙት ማርቆስና አዲስ አበባ ያሉት ይሰሙናል ብላችሁ ነው? ለእግዚአብሔር አሳቅለን ይቅር እንተወው።" አሉ ሌላኛው ባላገር እንደተቆነጠጠ ልጅ ሳግ እያነቃቸው።

"አሳምረው ይሰሙዪ! ለምን አይሰሙም? ራስ ኃይሉ ቤተ መንግስት ገብተው መቀመጣቸው፣ እንደ ውኃ ቀጂ ጥዋት ማታ አዲስ አበባ መመላለሳቸው የእኛን ችግር ሊያሰሙ አይደል? እንግዲያማ እኛስ ምን ልንሆናቸው? እነሱስ ምን ሊሆኑን ነው?" አለ አንድ ጎልማሳ ባላገር።

"ምኝ ይፀድቃል ወይ ቢሉት ገለባ ይበቅላል ወይ አለ አሉ ሰውዬው። መቼስ አገሬ! እኛው የመረጥነው እንደራሴያችን ያልሰማንን የልጅአምበራን ሸግር ማርቆስ ራስ ኃይሉ ቤተመንግስት ያሉቱ ይሰሙናል ለማለት ቁልብጥ የላት ድርጎ አማራት እንዳይሆንብን!" አሉ ሌላኛው አዛውንት

"ምነ እንግዲያ ስለእነርሱ አንዲት ቃል በስህተት ክፉ ስንተነፍስ እሚሰሙት! ስለራሳቸው ሲሆን መርፌ ጠብ ስትል ይሰሟታል። የአገሬው ሸግር ሲሆን ግን ምን ሲደረግ ቤተመንግስት ይደርሳል ይባላል። ለመሆኑ በማን ላይ ነው እንዲህ ሰማይ ጥግ መደረሱ? ባላገር ከተናቀ?" ሲል ደነፋ መጀመሪያ የተናገረው ጎልማሳ ባላገር።

የአውራጃ ሹሙ የባላገሩ ሁኔታ አላማራቸውም። ለመቆጣት ለማስፈራራትም አሰቡና መልሰው ተዉት። ሆድ ለባሰው ማጭድ አታውሰው እንዳይሆንባቸው ፈሩ። የከፋውን ባላገር ማባባልና ባይሆን ተስፋ እየሰጡ መሸንገሉ ነው እንጂ የባሰ ካስከፋት በዚህ ባለየለት ጊዜ ነገር ማበላሸት ሆኖ ተሰማቸው።

"ለመሆኑ ማመልከቻችሁ አሁን ማን ዘንድ ነው ያለው?" ሲሉ ጠየቁ ሹሙ ዝም ብለው ሲያዳምጡ ቆይተው

"የፊተኛውን ፓርቲ ጽ/ቤት፣ የሚካኤል ዕለት ያስጣፍኩትን ሸንጎ እንደራሴው ዘንድ በኋላ የተጣፈውን አውራጃ ገበሬ ማኅበሩ ጽ/ቤት ነው ያስገባሁ። መቼስ እንደማመልከቻው ብዛት ቢሆን ገና ድሮ ጉዳያችን በተፈጠመ።" አሉ የመጀመሪያው ሽማግሌ።

"የሸንጎ እንደራሴውን ማመልከቻ ለማን ሰጣችሁት?"

"ለራሱ ሰጠነው! ኋላ ለማን እንሰጠዋለን

"አነበበው?"

"አነበበው?!! አቀማጥሎይ ሲያነበውስ!" አሉ ሽማግሌው።

"ግልጥልጥ አድርጎ አገር የነገረውን ውስጥ ውስጡን እያዳፈነ ያለ ማን ሆነና ነው ሌላ! መቼስ ያውቀዋል ኑሮአችንን ጠይቆ የሚረዳው ነገር አይደለም።" አለ ጎልማሳው ደመ–ፍሉ ባላገር።" ሙተናል! ሙተናል! ሙተናልዪ! ይሄ ልጋጋም ውሻ የውሻ ልጅ እንዲህም አይቀልድብንም ነበር።"

"ተው ታገስ አያ ገላው።" አሉ የመጀመሪያው ሽማግሌ።

"ታግሼማ ነው እንዲህ መጠቃቴ። ጎጆዬን አንድጄአት ብሄድ ፊቱኑ ይሄ የእንጭቅ ልጅ ነጭ አሩን ሲያራብኝ አልገኝም።"

"ተው ታገስ አያ ገላው! ታገስ ብዬሃለሁ። ምን ይላል ይሄ ገጭጋጫ ዥል! ዛሬ ነው መቀለጃ መሆንክን የምታውቀው? መሀይም ባላገር ድሮም መቀለጃ ነው። ደንቆሮ የሰማ ዕለት ያብዳል አሉ። ታገስ ብዬሃለሁ።" ሲሉ ሽማግሌው የቁጣ ዶፍ አወረዱበት። አያ ገላው ስድብና ቁጣውን ውጦ አንገቱን ደፍቶ ፀጥ አለ። ለመናገር ያቀበቀበው እንደመፈንገል ያለው ባላገር ሁላ ሲገረፍ ቆይቶ አፍህን ያዝ እንደተባለ ህፃን እልህና ሳግ እየተናነቀው ዝም አለ። ለዚያች አፍታ ፀጥታ ሰፈነ።

"አሁንም እግዜር ያሳይዎ ጌታው! የሚጠይቀን ጠፍቶይ አቤት የምንልበት ርቆንይ፣ ጠምቶናል፣ ርቦናል። በየቤታችን ልጆቻችን ጠማቸውን ነው የሚያድሩ። ይህ ሁሉ ስለምነው ቢሉ ማሳችንን ተነጥቀን ለአምራቾች ስለተሰጠብን ነው። በድምጥም በጽሁፍም ሹም ለሆናችሁቱ ለሁሎችም አቅርበናል። አገሬው ዳኝነት አጥቶ ቢዳማ እኔ ነጣ መሆኔን ይወቁልኝ" አሉ የመጀመሪያው ሽማግሌ ሸክም የወረደላቸው ያህል በረጅሙ እየተነፈሱ።

የአውራጃ ሹሙ ከበዋቸው የቆሙትን ባላገሮች ለአፍታ ዝም ብሎ በትካዜ ተመለከቷቸው። ለራሳቸውም ለእርሱም ያዘኑ መሰሉ። እንዲህ በዋዛ እንደማይላቀቁ አውቀዋል። ወደቀበሌያቸው ተመልሰው አንድ ነገር ቢያደርጉም ዳፋው ከእርሳቸው ራስ ላይ እንደማይወርድ ተረድተዋል። አባብሎና አረጋግቶ ማሰናበት እንዳለበቸው ገብቶአቸዋል። በዚህ ላይ ወደ ማስልጠኛው ጣቢያው ሂዶ ሚሊሽያውን ዲላማ ለማስተኮስ ልባቸው ቆሟል። ግራ በተጋባ መንፈስ ዝም ብለው ሲያስቡ ቆዩና:–

"የሚካኤል ዕለት ከሸንጎ እንደራሴውና ከአውራጃ የገበሬ ማኅበር ሊቀመንበሩ ጋር እዚያው ቀበሌያችሁ ድረስ መጥተን መፍትሄ እንሰጣችኋለን። ያን ዕለት ሕዝቡን ሰብስባችሁ ቆዩን። በሉ አሁን ሂዱ።" አሉ ሹሙ የእውሸት ፈገግታ እያሳዩዋቸው። እንደጅብራ ተገትሮ ቆሞ የነበረው ባላገር ሁሉ የተፈረደለት ያህል ደስ ብሎት እጅ ነስቶ ሹሙን እየመረቀ እያውካካ የየአመሉን ለማድረስ ወደ የመሸታ ቤት ተበታተነ። አውራጃ ሹሙም መኪናቸውን አስነስተው ለዲላማ ማስተኮሻ ወደተዘጋጀው ስፍራ በረሩ።

(ይቀጥላል)

*          *          *

**የቦክስ መድረክ . . . (ከገጽ 35 የዞረ)**

ከመጀመሩ በፊት ካስየስ ክሌይ ሪንጉ አጠገብ ሆኖ የፓተርሰንን እጅ ጨብጦ ሶኒ ሊስተንንም ከመጨበጥ ይልቅ ኮሚክ በሆነ አገላለፅ እጆቹን በፍራቻ መልክ ወደ ላይ ከፍ አድርጎ እንደሚሸሽ ሰው ራቅ እያለ በመሃድ አስቂኝ ትርዒት ለማሳየት በመሞከሩ ካስየስ ክሌይ በዛን ወቅት ስለ ሶኒ ሊስተን የነበረው አስተያየት ፈረንጆቹ ከነበራቸው ግምት ጋርመመሳሰሉን አሳይቷል። ሶኒ ሊስተንን እንዲያሸንፍ ተስፋ የጣሉበት ይህ አዲስ ቦክሰኛ - ካስየስ ክሌይ የሶኒ ሊስተንን አስተዳደግና ቁመና ይሳደብ ነበር። በንግግሩም ላይ "Big ugly bear ... he can't talk ... I am gonna give him to the local zoo after I whup him ... he is too ugly to be the World champ ..." በማለት የባርያ ገዥዎችን (የነጮችን) ቋንቋ በመጠቀም ሶኒ ሊስተንን ተሳድቧል። በማያሚ ከተማ የተካሄደው ግጥሚያ ሶኒ ሊስተንን ሰባተኛውን ዙር መጨረስ አቅቶት ሻምፕዮናነቱን ለክሌይ አስረከበ። ክሌይ ሻምፒያናነቱን እንዳረጋገጠ ከግጥሚያው በኋላ ከማልከም ኤክስ እና ከጂም ብራውን ጋር ውይይት አካሂዶ ነበር። በነጋታው ማልኮም ኤክስን ከጎኑ አድርጎ ለጋዜጠኞችና ለተቀረው ዝህብ "በአላህና በሰላም አምናለሁ። የነጮች ሰፈር ለመኖር ፍላጎት የለኝም፤ ነጭ ሴት ለማግባትም ፍላጎት የለኝም። በአስራ ሁለት ዓመቴ ነበር የተጠመቅኩት ሆኖም ምን ማለት እንደሆነ አላውቅም ነበር ከአሁን ጀምሮ ክርስቲያን አይደለሁም። ወዴት እንደምሄድና እውነት ምን ማለት መሆኑን አውቃለሁ ስለዚህም እንድሆንላችሁ የምትፈልጉትን ዓይነት ሰው አልሆንም። የፈለግሁትን ዓይነት ሰው ለመሆን መምረጥ የምችል ነፃ ሰው ነኝ" በማለት ማንም የቦክስ ሻምፕዮና ወይም ማንም ጥቁር ስፖርተኛ በአደባባይ ወጥቶ ያላሳየውን ግላዊ ነፃነትና ፖለቲካል ንግግር ለመጀመሪያ ጊዜ በመንገር የስፖርቱን ዓለም ብቻ ሳይሆን የአጠቃላይ የህብረተሰቡን በተለይም የነጭ አገዛዝንና የክርስቲያንና የእምነት ጥያቄ ላይ አስቀመጠው። የቀድሞው ካስየስ ክሌይ የአሁኑ መሀመድ አሊ በዚህ ብቻ አላበቃም ነበር። በቀጣዩ ቀን በሰጠው መግለጫ ላይ መሀመድ አሊ ከቀድሞዎቹ ሻምፕዮኖች የተለየ መሆኑንና የእርሱ አርአያነት የቦክሱ ዓለምም ሆነ የነጩ ዓለም የሚወስነው አለመሆኑን ተናገረ።

"ጥሩ ልጅ ነኝ። መጥፎ ነገር ሰርቼ አላውቅም። እስር ቤት ገብቼ አላውቅም፤ ፍርድ ቤትም ቀርቤ አላውቅም፤ (ከነጮች ጋር ለመዋሃድ) የintegration ሰልፍ አልተሳተፍኩም፤ በየሄድኩበት በአይኖቻቸው የሚጠቅሱኝን ነጭ ሴቶች ከቁም ነገር አልቆጥራቸውም። አውራ ዶሮ የሚጮኸው ብርሃኑን ተመልክቶ ነው እንጂ በጨለማ ውስጥ አይጮህም። እኔም ብርሀን ስለተገለጠልኝ ነው (አሁን) የምጮኸው"በማለት እስር ቤት ውስጥ ታስሮ ከነበረው ከሶኒ ሊስተን ጋር እንዳያመሳስሉት፣ ከነጭ ሴት ጋር ተጋብቶ ከነበረው ከጃክ ጆንሰን ጋር ልዩ እንደሆነ፣ ነጮች ሰፈር ውስጥ ቤት ገዝቶ ይኖር ከነበረው እንደ ፍሎይድ ፓተርሰንን መሐመድ አሊ የመቀላቀል ሀሳብ እንደሌለው በግልጥ መናገሩ ነበር። ታዋቂው ቦክሰኛ ጆርጅ ፎርማን እንዳስቀመጠው "የመሐመድ አሊ እስላም መሆን የሃይማኖት ለውጥ ነው ብዬ አላምንም። . . . እስከ ዕለተ ሞቴ ድረስ የማምነው ይህ ለውጥ የንቃተ ህሊናው ከፍ ማለቱን ነው። በዛን ወቅት አሊ ያስፈለገው አቋም ነበር። ህብረተሰቡ የሚያስፈልገው ለውጥ ነበር።"

ካስየስ ክሌይ ሶሊ ሊስተንን አሸንፎ ሻምፕዮና በሆነ በሳምንቱ ወደ ሐርለምን በመሄድ የማልከም ኤክስ ቢሮ በሚገኝበት በሆቴል ቴሬሳ አረፈ። ወዲያው ከማልከም ጋር ሆነው የተባበሩት መንግሥታትን በመጎብኘት ከልዩ ልዩ የአፍሪቃ አምባሳደሮች ጋር በመገናኘት ፎቶግራፍ ተነሱ። በዛኑ ዓመት በMarch 6 የጥቁር እስላሞች መሪ የነበረው ኤላጃ መሀመድ የዓለም ከባድ ሚዛን ቦክስ ሻምፕዮን ካስየስ ክሌይ ስሙን ለመቀየር መዘጋጀቱን ካበሰረ በኋላ "በአላህ እስካመነ ድረስ፣ እኔን እስከተከተለኝ ድረስ መሀመድ አሊ ተብሎ እንዲጠራ ፈቅጃለሁ" በማለት አወጀ።

ከካስየስ ክሌይ ወደ መሀመድ አሊ የተቀየረው መጠሪያ ወዲያውኑ ተቀባይነት አላገኘም ነበር። ምንም እንኳን ስሙ መቀየሩን በአደባባይ ቢናገርም የኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ አዲሱን የቦክስ ሻምፕዮን ለብዙ ወራቶች ይጠራ የነበረው 'ካስየስ ክሌይ' በሚለው ስም ነበር። ሀይማኖቱንም በመቀየሩ በነጮች ብቻ ሳይሆን በብዙ ጥቁሮች ይነቀፍ ነበር። ሊውቪል ኪንታክ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ክርስቲያን ጥቁሮች አሊ "ዘሩን አሰዳቢ ብቻ ሳይሆን ለአገሩና ለመላው ዓለም ውርደት ያከናነበ ሰው ነው" ብለውት ነበር። መሀመድ አሊ ግን ከቡጢ ዓለም መድረክ ብቻ ሳይሆን የህይወት/የፖለቲካ ትግሉን በሰፊው ተያያዘው። ማልከም ኤክስ ያቀረበለትን ምክር በመቀበል በMay, 1964 ዓ/ም አሊ ወደ አፍሪቃ ተጓዘ። ወደ ጋና በመዝለቅ ከኒክሩማ ጋር ሲገናኝ፣ ካይሮ ውስጥ ከፕሬዚዳንት ጋማል አብደል ናስር ጋር ተገናኘ። በአፍሪቃው ጉዞ ላይ አሊ በደረሰበትና በጎበኘበት ቦታዎች ላይ ብዙ አፍሪቃውያኖች ሊያዩት ከመምጣታቸው በላይ አዲሱን መጠሪያውን/ስሙን በድግግሞሽና በህብረት "አሊ! አሊ! አሊ! አሊ! . . ." በመጥራት የድሮ የፈረንጅ ስሙን ላንዴም ለሁሌም ቀበሩት። ይህ በዚህ እንዳለ ሆኖ የቀድሞው ሻምፕዮና የፍሎይድ ፓተርሰን ህይወት መመሳቀል ጀምሮ ነበር "እንደ ካቶሊክነቴ" ይህንን ሻምፕዮና ከእስላሙ አሊ እጅ ማውጣት ያለብኝ "የአሜሪካ ግዴታዬ" ነው እያለ ይናገር የነበረው ፓተርሰን ቤተሰቦቹ ላይ ነጮቹ ያወርዱት የነበረው የዘረኝነት ስድብና ግልምጫ ስላስቸገረው ከነበረበት የነጮች ሰፈር ቤቱን ሸጦ ለመውጣት ተገደደ። ሆኖም "ጥቁር እስላም ሻምፕዮን መሆኑ ለአሜሪካ ውርደት ነው" ማለቱ አሊን ስላናደደው ምላሹን በግጥም አቀረበ።

I am going to put him flat on his back,
so that he will start acting black,
because when he was champ he didn't do as he should,
he tried to force his way into an all white neighbourhood.

አሊ ፓተርሰንን ከመግጠሙ በፊት ለብዙ ሳምንታት ያህል የስድብ ውርጅብኝ እያዥጎደጎደ የተጋጣሚውን ሞራል ይደበድብ ነበር። ቀኑ ደርሶ በተጋጠሙበት ሰዓት መሀመድ አሊ ቦክስን ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ትግሉንም በዛ ሪንግ ውስጥ እየደነሰ ማሳየት ጀመረ። አንዳንዶቹ እንደሚሉት ግጥሚያው ለአሥራ ሁለት ዙር እንዲቀጥል በማድረግ ፓተርሰንን በቡጢ እየቀጠቀጠ ፋታ እንዲያገኝም ወደ ኋላ እያፈገፈገ መልሶ እንደገና ቡጢውን እያሳረፈበት "ና! ና የእኔ አሜሪካ!" . . . "ና! ና! ና! ነጭ አሜሪካ!" እያለ የፓተርሰንን ሰውነትና ሞራል ብትንትኑን ማውጣቱ ይታወሳል።

መሀመድ አሊ ከሚታወቅባቸው ስራዎች ውስጥ የቬትናምን ጦርነት በመቃወም 'ሂጂ አልዋጋም' በማለቱ ያራገበው የፖለቲካ ስራ ነው። አንዳንድ አሜሪካኖች ጆ ሊውስ አገሩን በጦር ሜዳ ላይ እንዳገለገለ ሁሉ መሀመድ አሊም ተመዝግቦ ማገልገል አለበት ይሉ ስለነበር

Keep asking me,
no matter how long
on the war in Vietnam,
I song this song
I ain't got no quarrel
with the Viet cong. በማለት መልሶላቸዋል። የኬንታኪ (የተወለደው እዛ ነው) ምክር ቤት ያሳመሰገኑትን ያህል "አገር ወዳድ ኬንታኪያንን አዋርዷል" አሉ የአሊናይ መንግሥት፣ የማያሚ፣ የፒትስበርግ ከተሞችና የተለያዩ የፖለቲካና የቦክስ ባለስልጣኖች የመሀመድ አሊ ግጥሚያን ህዝቡ መመልከት እንዲያቆም ቅስቀሳ አደረጉ። በጥቂት ቀናቶች ውስጥ በየሲኒማ ቤቱ በclosed circuit TV ግጥሚያ እንዲያሳዩ የተፈቀደላቸው ሶስት መቶ ቲያትር ቤቶች በራቸውን ቆለፉ። አሊን ለመግጠም ተዘጋጅቶ የነበረው (Ernie Terell) ኧርኒ ቴሬል ዕድሉ ሳይሳካለት ቀረ። ሆኖም በ1976 ዓ/ም በሂውስተን ከተማ አሊና ቴሬል ለመጋጠም ተስማምተው ዝግጅት እንደጀመሩ ጋዜጠኞች እየተከታተሉ ለሚጠይቋቸው ጥያቄዎች መልስ በሚሰጡበት ወቅት ቴሬል መሀመድ አሊን በድሮ ስሙ ክሌይ እያለ ይጠራው ነበር። በግጥሚያው ወቅት ንዴት በተሞላበት ስሜት ቡጢውን ቴሬል ግንባር ላይ እያሳረፈ "ስሜ ማነው?! "Uncle Tom ... What is my name?" እያለ እየደጋገመ ቡጢና ጥያቄ ያወርድበት እንደነበረ ግጥሚያውን የተከታተሉ ሁሉ ይናገራሉ። ጋዜጠኞች ግጥሚያውን "ሆን ተብሎ በጭካኔ የተሞላ የብልግና ግጥሚያ፣ የስፖርት ጠባይ የጎደለው ግጥሚያ" ወዘተ እያሉ መሀመድ አሊን ለማጥላላት ዘገባ አቅርበው ነበር። መሀመድ አሊን በቦክስ ሪንግ ውስጥ "ጨካኝ ባለጌ" እያሉ ቢጠሩትም ቅሉ እነዚሁ ሰዎች ቬትናም ድረስ ሄዶ የበለጠና የከፋ ጭካኔ ውስጥ መሳተፍ አለበት ከማለት አልተቆጠቡም ነበር። ከነበረው ውጣ ውረድ በኋላ የአሜሪካ መንግሥት መሀመድ አሊን ጦርነት ውስጥ ለማሳተፍ ሳይሆን የወታደሮችን ሞራል ከፍ እንዲያደርግ ብቻ መፈለጉን ቢያስታውቅም መሀመድ አሊ በማንኛውም መልክ ቬትናም ለመሄድ አለመፈለጉን ፍርጥም አድርጎ አሳወቀ። ዝነኛው ፓል ሮብሰንና ዱቦይል ጦርነቱን በመቃወም የተሰደቡበትንና ለስደት የተዳረጉበትን የፖለቲካ እምነት እነሆ በተደጋጋሚ መሀመድ አሊ በግልፅ ሊያሳየው ቻለ።


በ1966 ዓ/ም የአሜሪካው የስለላ ድርጅት ኤፍ ቢ አይ አሊን መከታተል ጀመረ። በ1967 በMarch ወር ላይ ማርቲን ሉተር ኪንግ ከመሀመድ አሊ ጋር በግል ተገናኝቶ የሻምፒዮኑን አቋም እንደሚደግፍ ገለጠለት። ወዲያውኑ ከአንድ ሳምንት በኋላ ማርቲን ሉተር ኪንግ ራሱ የቬትናምን ጦርነት እንደሚቃወም በሪቨር ሳይድ ቤተክርስቲያን (ኒውዮርክ) ውስጥ በሰጠው ንግግር ላይ አስታወቀ። ይህ በሆነ በሶስተኛው ሳምንት አሊ በታዘዘው ሂውስተን ለሚገኘው የወታደር ጣቢያ ሄዶ አመለከተ። የምዝገባውን ኃላፊ ሳጅን (Sergeant) በተሰጠው የስም ዝርዝር መሠረት መሀመድ አሊን "ካስየስ ክሌይ" እያለ ቢጠራ የሚመልስለት ሰው አጣ። በተደጋጋሚ ሶስት ጊዜ ቢጣራም መሀመድ አሊ የማይመልስ ሆነ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ በጽሁፍ የሚያዝ ኦፊሲያል ሐተታ ማለትም ጦርነቱን ለመካፈል ሃይማኖቱ እንደማይፈቅድለት የሚያሳውቅ ቃሉን በመስጠትና ፈርማውን በማስቀመጥ መሀመድ አሊ አቋሙን ገለጠ።

"Feb. 25, 1964 የተቀዳጀሁት "የዓለም ከባድ ሚዛን ሻምፒዮን ተብዬ መጠራቴ ያኮራኛል። ይህን መጠሪያ የያዘ ሰው ከልቡ የሚያምንበትን ነገር በቦክስ ሪንግ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በውጪው ዓለምም ቢሆን አቋሙ መሆኑን የማሳወቅ ወኔ ያስፈልገዋል።" ከዚህ በኋላ መሀመድ አሊ አስር ሺ ብር ቅጣትና አምስት ዓመት እስራት ተፈረደበት። ይህንን ፍርድ ላለመቀበል ሶስት ዓመት የፈጀ 'የይግባኝ' ትግል እንደጀመረ የሻምፒዮናነቱን ማዕረግ ተነጥቆ ኑሮውን የሚያከሂደው በልዩ ልዩ ኮሌጆች እየሄደ ንግግር በማድረግ በሚያገኘው ገቢ ብቻ ነበር። በዛን ወቅት ልዩ ልዩ የኮሌጅ ተማሪዎች የአሊን እምነት እየደገፉ ሲሄዱ አሊም በንግግሩ ውስጥ የሚያስተላልፈው መልዕክት እየከረረና እየጠነከረ ሄደ። Damn the Money. Damn the heavyweight chamionship. I will die before I sell out my people for the White man's. ይህ መሀመድ አሊ የጀመረው የፖለቲካ ትግልቀስ በቀስ ተቀባይነት

እያገኘ በመሄድ የጥቁር ሰራተኞችን ንቃተ ህሊና እያሳደገው ሄደ። በ1967-8 ዓ/ም በሰሳሳ ቀናት የነጮች ኮሌጆች አትሌቲክስ ክለብ ውስጥ የነበሩ ጥቁር ስፖርተኞች ልዩ ልዩ የጥቁር-ነክ ጥያቄዎችን አቀረቡ። ጥቁር አሰልጣኞች፣ ጥቁር ቺር ሊደሮች፣ ጥቁር ሃች . . . ማለትም ጥቁሮች በብዛት በሚገኙበት ቡድኖች ውስጥ የጥቁሮች መሪነት መኖር ይገባዋል የሚሉ ጥያቄዎች ነበሩ። በዛው የትምህርት ዓመት ልዩ ልዩ ስፖርተኞች ተሰብስበው Olympic Project for Human Right (OPHR) የሚል ድርጅት አቋቋሙ። ይህ ድርጅት በመጀመሪያው ያቀረበው ጥያቄ የመሀመድ አሊ ሻምፕዮናነት እንዲመለስለት የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የአሜሪካንን የኦሎምፒክ ቡድን የሚመራው Avery Brudage የተባለው ሰው "ዘረኛ" በመሆኑ ከስራው መወገድ አለበት ይላል። ሶስተኛው ጥያቄ ደግሞ ዘረኞቹ የደቡብ አፍሪቃና የሮዲዥያ ቡድኖች ከአለም አቀፍ ስፖርት ውድድር መታገድ ይገባቸዋል የሚል የጥቁር ህዝቦችን በደል ዓለምአቀፋዊ መድረክ ላይ ያስቀመጠ ጥያቄ ነበር። የOPHR አባሎች ትግላቸውን ይበልጥ ለማፋፋም የኦሎምፒክ መድረክ የጥቁር ህዝብን ትግል ይበልጥ ሊያሳውቁበት መመካከር ቀጠሉ። ሁለት የOPHR ደጋፊ አትሌቶች የኦሎምፒኩን የሽልማት መድረክ (podium) ለዚህ አላማቸው ሊጠቀሙበት ተስማምተው በ1968 ዓ/ም በሜክሲኮ ከተማ በተካሄደ ኦሎምፒክ ላይ የሁለት መቶ ሜትር ሩጫ እሽቅድምድም ላይ አንዱ (ቶሚ ስሚዝ) የወርቅ ሜዳልያ) ሌላው (ጆን ካርሎስ) ሶስተኛ በመውጣት የብሮንዝ ሜዳሊያ ሊሸልሙ መድረክ ላይ ወጥተው ሜዳሊያቸውን እንዳነገቱ የአሜሪካ ብሔራዊ መዝሙር በአሜሪካ ባንዲራ ታጅቦ መዘመር ሲጀምር ሁለቱ አሸናፊዎች ቀደም ሲል ለሁለት የተካፈሉትን ጥቁር የእጅ ጓንት አንዱ የቀኙን ሌላው የግራውን ያጠለቁበትን እጃቸውን ወደ ላይ ከፍ በማድረግ የጥቁርነት Black Power ምልክት በማሳየት ከአሜሪካ ጋር ያላቸውን ቅሬታ ለአለም ህዝብ ገለጡ። ቶሚ ስሚዝና ጆን ካርሎስ ይህንን የጥቁርነት ምልክት Black Power መጠቀም አልነበረባችሁም በማለት ተቀምጠውበት ከነበረው ከኦሎምፒክ መንደር እንዲወጡ ተደረገ። ፖለቲካ ውስጥ የሚያገባን ነገር የለም የሚለው የኦሎምፒክ ድርጅት ምን ያህል ፖለቲከኛ እንደነበረ ከዚህ ድርጊቱ መገመት ይቻላል። ቶሚ ስሚዝ እና ጆን ካርሎስ የመሀመድ አሊን አርአያነት በመከተል የህዝባቸውን በደል ለመቃወም የስፖርት መድረኩን ወደ ትግል መድረክ ቀየሩት። በ1969 አሊ ከጥቁር እስላሞች ጋር ቅራኔ እያሳደረ ሄደ። በተለይ ቦክሰኝነቱን እንደማይተውና ለወደፊቱም የመጫወት እቅድ እንዳለው መግለፁ ከኢላጃ መሀመድ ጋር ሊያስማማው አልቻለም ነበር። ምንም እንኳን በቦክሱም ሆነ በውጪው ዓለም ላይ ለሚያካሂደው ትግል አንዳችም ዕርዳታ ከእስላሞቹ ባያገኝም ቅሉ እስላሞቹ (Black Muslims) መሀመድ አሊን ለመቆጣጠር ፍላጎቱ ነበራቸው።


ፕሬዚዳንት ኬኔዲ እንደተገደሉ ማልከም ኤክስ "The Chickens come home to roost" የሚል ቃል ለጋዜጠኞች በመናገሩ ከድርጅቱ ስራዎች ለተወሰነ ጊዜ እንዲወገድና አንዳችም ቃል በአደባባይ እንዳይናገር በኢላጃ መሀመድ ተፈርዶበት ነበር። በተመሳሳይ መንገድ መሀመድ አሊ ቦክሰኝነቱን እንደሚቀጥልበት በቴሌቭዥን ላይ መግለፁን በመቃወም ከእስላሞች ድርጅት ለዘጠኝ ወር ታግዶ ነበር። በማከታተልም ኢላጃ መሀመድ "መሀመድ አሊ የስፖርት ደም ያለው ሰው ነው። ቁርአን አታድርጉ በማለት የሚያስተምረንን ስራ መሀመድ አሊ የማድረግ ፍላጎት እንዳለው ተናግሯል።" በማለት ትችት ካቀረቡ በኋላ በመጨረሻ ላይ ትችቱን የደመደመው "ከአሁን ወዲህ የምንጠራው ካስየስ በሚለው ስም ነው" በሚል አነጋገር መሀመድ አሊ ብዙ የታገለለትን ስም መልሶ ለመውሰድ ሞክሮ ነበር።

ወደ ቦክስ ዓለም ከተመለሰ በኋላ የመሀመድ አሊ የመጀመሪያው ግጥሚያ ከጆ ፍሬዘር ጋር ነበር። የቦክስ ግጥሚያ ላይ እየበለፀገ የመጣው የቡጢ ታክቲክ ከ"ጥቁርነት" ጋር አብሮ የሚሄድ ስፖርት መሆኑ በተደጋጋሚ ያረጋገጠው የመሀመድ አሊ በቦክስ ሪንግ ውስጥና በውጪው ዓለም ያካሄደው የቡጢና የፖለቲካ/ሃይማኖት ትግል ነበር።
ፍሬዘር ሻምፒዮና አይደለም። ከእርሱ ጋር መነጋገር የሚፈልግ ሰው የለም እኔን ካሸነፈ ኒክሰን ይደውልለት ይሆናል። ኒክሰን ለእኔ የሚደውል አይመስለኝም። 98% የጥቁር ህዝብ የእኔ ደጋፊ ነው ከእኔ ትግል ጋር የተዛመዱ ናቸው። በየመንገዱ ላይ በየቀኑ የሚታገሉት የእኔን ዓይነት ትግል ነው። ሳሸንፍ ያሸንፋሉ። ከተሸነፍኩ ይሸነፋሉ። ፍሬዘር እኔን ያሸንፋል የሚል ጥቁር Uncle Tom ነው" በማለት መሀመድ አሊ ለተናገረው ቃል አፀፋውን በመመለስ ፍሬዘር እንዲህ ብሎ ነበር።
እኔን Uncle Tom ብሎ መጥራት፣ እኔን የነጮች ሻምፒዮን ብሎ መጥራት ህዝብ እንዳይደግፈኝ የታቀደ ሸፍጥ ነው። አሊ ራሱን እንጂ ጥቁር ህዝብን አይረዳም፤ የጥቁር ህዝብ መሪም አይደለም።"
ከተደጋጋሚ ግጥሚያዎች በኋላ አሊ ሻምፒዮናነቱን ከፍሬዘር ላይ ከወሰደ በኋላ የሚቀጥለው የሻምፕዮን ግጥሚያ የተካሄደው በዛየር ኪንሻሳ (አፍሪቃ) ውስጥ ከጆርጅ ፎርማን ጋር ነበር። በውጪው ዓለምና በዛየር ውስጥም የበለጠ ተቀባይነት ለማግኘትና ዛየርን የቱሪስት መናኸሪያ በማድረግ የውጪ ምንዛሪ ለመሰብሰብ የሞቡቱ መንግስት ግጥሚያው ዛየር ውስጥ መደረጉን ፈቀደ። ከግጥሚያው በፊት እንዲሰራበት የተደረጉት ማስታወቂያዎች በጉልህ ያሳዩ የነበረው የኪንሻሳ ከተማን ሰማይ ጠቀሶችን፣ በንፅህና የተጠበቁ አውራ መንገዶችንና ትላልቅ የመንግስት አውታሮችን ብቻ ሳይሆን፤ የውጪ ኢንቨስትመንትን ለመሳብም የዛየር የንጥር ሀብቶች ማለትም አልማዞችና ነሐሶችን ያዘሉ ማስታወቂያዎች ይታዩ ነበር። አሊ "The Rumble in . . . (ወደ ገጽ 10 ይዞራል)



## ያለፈው ሰንጠረዥ መልስ

# ሰንጠረዥና ጨዋታ



### ወደ ጎን

1. አዲስ ዓመት
5. ጤናው ታወከ
8. ተግባሩ
9. መፈጸም
10. ተባይ
12. ላሊበላ (አውራጃው)
14. ሸተተ
15. ጊዜ
17. አሳንሶ ማየት
19. ዘመን
21. አንዱ ለአንዱ መስጠት
23. የተቀቀለ ጥራጥሬ
24. የውስጥ የሰውነት ክፍል
25. ________ ያለ ሜዳ
28. አንቀላፋ
29. ነጠቀ
30. ሲያበጣብጣቸው
33. በመስታወት የሚታይ
34. ያዝ አድርግ
37. ሴቶች ይሉታል
38. በፍጥነት ትሄዳለህ

### ወደ ታች

1. ደንቃራ
2. የሚያም
3. ቤት ውስጥ ቀና ሲሉ የሚታይ
4. የቤት ወለል (ሳንቃ)
5. ቀለበት ተደረገለት
6. ጭቃውን ግድግዳ ላይ ____
7. ማዳመጥ
9. መከልከል
11. ምሽቱን
13. ለመንገደኛ የሚያስፈልግ
16. ሁሌ ጥሬ
18. ቀዳዳ ታብጅ
20. ውትወታ
22. ልንዋረድ
25. ችግሬን ባዋይህ
26. ትግራይ ውስጥ የኢህአፓ
28. ምግብ አልስማማ ብሎ ሲወጣ
31. ይፎክታል
32. ደግ
36. የተፈጨ አተር

መልሶቻችሁን ላኩልን።

# የላንዳፍታ መጽሔት ደምበኛ ይሁኑ

ለ6 ተከታታይ እትሞች
(Six Consecutive Issues)

| | |
|---|---|
| U.S. | $16.00 |
| Canada | $22.00 |
| Europe | $30.00 |
| Asia | $38.00 |
| Institutions | $40.00 |

**የሚላክሎት በመጀመሪያ ደረጃ ፓስታ አገልግሎት ነው።**
**በአካባቢዎ ገበያ ላይ ከመዋሉ በፊት ይደርስዎታል።**

## የላንዳፍታ መጽሔት የደምበኝነት ቅጽ
## LANDAFTA SUBSCRIPTION FORM

NAME ________________________________

ADDRESS ________________________________

CITY ______________ STATE ______ ZIP ______________

PHONE (______) ______________

<u>ያለፉትን እትሞች</u> ማዘዝ ከፈለጉ ይህንኑ ይጥቀሱ
ክፍያው ከነመላኪያው ለእያንዳንዱ እትም $ 2.50 ነው።

ለጓደኛዎ በሽልማት መልክ ለመላክ ከፈለጉ ከዚህ በታች ያለውን ይሙሉ።
Please, send my gift subscription to the following person.

NAME ________________________________

ADDRESS ________________________________

CITY ______________ STATE ______ ZIP ______________

PHONE (______) ______________

እባክዎን ክፍያዎን በመኒ ኦርደር ወይም በቸክ በአድራሻችን ይላኩ።
*Please, send money order or check payable to LANDAFTA.*

LANDAFTA
P.O.BOX 49301
ATLANTA, GA 30359

እንቁጣጣሽ በያመቱ ያምጣሽ

# አባይ ምግብ ቤት
# Abbay Restaurant

እንኳን ለአዲሱ ዓመት በሰላምና በጤና አደረሳችሁ ይላል።



ከእሁድ እስከ ሐሙስ ከ 11:30 a.m. እስከ 11:00 p.m.
ዓርብና ቅዳሜ ከ11:00 a.m. እስከ 12:00 midnight (ራት)
የመዝናኛ ፕሮግራም እስከ 2:00 a.m.

ለሠርግ፣ ለቀለበት፤ ለክርስትና፤ ለልደትና
ለመሳሰሉት በልዩ ትዕዛዝ እናዘጋጃለን።



የተለያዩ ባህላዊ ምግቦቻችንን ይወዳሉ።
ብቅ ይበሉና እናስተናግድዎት።

በዕረፍት ቀናት ምሽት
የመዝናኛ ፕሮግራሞች ይኖሩናል።
ደስ ሲላችሁ እኛንም ደስ ይለናል፤
ስለዚህም በመስተንግዶአችን እናስደስትዎታለን።

## AUTHENTIC ETHIOPIAN RESTAURANT

Have a spicy authentic Ethiopian dinner
and stay for the cultural entertainment on weekends.

3375 Buford Highway # 1050
Atlanta, GA
(404) 321-5808



# MRA'G TRAVEL
## ሚራዥ የጉዞ ወኪል

*International - Business - Leisure - Cruise*

ለአለም አቀፍና
ለአገር ወሰጥ ጉዞዎ አለንልዎ!

Excellent Service!
Special Fare!
Group Fare!



ገነት ፈቀደ
ፕሬዚዳንት
Genet Fekede
*President*

አስተማማኝ ጉዞ ወደ

አዲስ አበባ
አስመራ
ጆሀንስ በርግ
ቴላቪቭ
ኢየሩሳሌም
ፍራንክፈርት
ለንደን

92 Piedmont Ave N.E
Atlanta, GA. 30303
(404)577-4404
Fax (404)222-9305



# ካሊፎርኒያ ማርት በአትላንታ
# CALIFORNIA MART IN ATLANTA

2080 CHESHIRE BRIDGE ROAD
ATLANTA, GA 30324
(404)320-6747 - (404)320-9082

**ቁርስ** ፉል፤ ግንፍልፍል፤ ያበሻ ዳቦ፤ አምባሻ

**ምሣና እራት** ክትፎ፤ ጥብስ፤ ጎረድ ጎረድ፤ የጥብስ ፍርፍር፤ የበግ አልጫ ፍትፍት

በተጨማሪ እንጀራና ሥጋ እንሸጣለን።

ORDER FOOD
TO GO!!

## የተለያዩ የምግብ ሸቀጦች መደብር

ESPRESSO
CAPPUCCINO

በርበሬ
ሚጥሚጣ
ሽሮ
ቅንጬ
ምስር
ጤፍ
ቡና

እጣን
የተነጠረ ቅቤ
አዋዜ
ጌሾ
የወጥ መከለሻ
ቡላ ዱቄት
ልዩ ልዩ ቅመማ ቅመሞች

ይደውሉልን ወይም ይጎብኙን!!

Mail Order Available
Please, call for Arrangements